**ማውጫ**

1. መግቢያ፡-........................................................................................................................................1

ክፍል አንድ...................................................................1

1. የእቅዱ ዋና ዋና መነሻ ሁኔታዎች...................................................................................................1

1.1 የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄ የሚገኝበት ሁኔታ..................................................................................1

1.2 የአመራሮችና አባላት ሁኔታ፣..............................................................................................................4

1.2.1 የአመራር ሁኔታ፣......................................................................................................................4

1.2.2 የብአዴን አባላት ሁኔታ....................................................................................................................8

1. 3 የሊግ አደረጃጀቶች ሁኔታ...................................................................................................................11

1.4 የምክር ቤቶች፣የተከለሊህዴንና ሌሎች አደረጃጀቶች ሁኔታ..........................................................11

1.5 የመንግሥት መዋቅር ሰራተኞች ሁኔታ ..........................................................................................12

1.6 የህዝብ ሁኔታ........................................................................................................................................13

1.6.1 የከተማው ህብረተሰብ ሁኔታ ...........................................................................................................13

1.6.2 የአርሶ አደሩ ሁኔታ ......................................................................................................................14

1.7 የህዝብ አደረጃጀቶች ሁኔታ ...........................................................................................................15

1.8 የተቃዋሚ ኃይሎች ሁኔታ ........................................................................................................... 16

1.9 የዓመቱን የልማትና የዴሞክራሲ ተግባራት በተደራጀ የልማት ሰራዊት የመፈፀም አስፈላጊነት..........17

1.10 የብአዴን 12ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ፤የስትራቴጅክ እቅድ ዝግጅት እና የአካባቢ ምርጫ የሚካሄድ መሆኑን እንደ እቅድ መነሻ.....18

1.1 የድርጅታዊ ጉባኤ ተግባራት፣..................................................................................................................18

1.2 የብአዴን የመካከለኛ ጊዜ እቅድ ማዘጋጀት ስራ፣...........................................................................18

1.3 የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ምርጫ ዝግጅት...........................................................................18

1.11 ከሁኔታ ትንተናው የሚወሰዱ ድምዳሜዎችና አንደምታዎች ....19

ክፍል ሁለት....20

የ2010 የፖለቲካና የድርጅት ስራዎች ዓላማዎች፣ ግቦችና ተግባራት አፈፃፀም....20

1. የእቅድ ዓላማዎች....20

2 ቁልፍ ተግባር ....21

3. የእቅዱ ግቦችና ተግባራት ....21

4. የ2010 ዓ.ም የፖለቲካና ድርጅት ስራ ተግባራትና የምዕራፎች ክፍፍል.... 62

5. የ2010 ዓ.ም የፖለቲካና ድርጅት ስራ እቅድ መሰረታዊ የአፈፃፀም አቅጣጫዎች....44

6. በ2010 እቅድ አፈፃፀም የሚያጋጥሙ ችግሮችና መፍትሄዎች.... 45

7. የእቅዱ ፈፃሚ አካላት.... 47

8. ተግባራት የሚፈፀሙበት ጊዜ ሰሌዳ.... 47

# የ2010 በጀት ዓመት የፖለቲካና ድርጅት ሥራ እቅድ

(ተግባርንና ውጤታማነትን ማዕከል ያደረገ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ግንባታ)

(ረቂቅ)

**ነሐሴ/2009 ዓ.ም**

ባህርዳር

## ተግባርንና ውጤታማነትን ማዕከል ያደረገ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ግንባታ

**1 መግቢያ፡-**

በህዝቡ የግፊት ኃይል የተቀሰቀሰው የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄ በአንድ አመት እንቅስቃሴው ድርጅቱ ውስጥ አንዣቦ ከነበረው የዝቅጠት አደጋ አውጥቶ ትክክለኛ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ጎዳና አስገብቶታል። ድርጅቱ ቆሞበት ከነበረበት መስቀለኛ መንገድ በማሻገር ትክክለኛውን የለውጥ ጎዳና እንዲይዝ አስችሎታል። ንቅናቄው በመስመሩ ዙብ የሚቆሙ ኮር ኃይሎችን መፍጠርና ማበርከት ጀምሯል። በአመራሩ መካከልና በአመራሩና /በአባላት እንዲሁም በህዝቡ መካከል ተፈጥሮ የነበረው የእምነት መሰበር ተመልሶ መጠገን ጀምሯል። ሙስናና በአጠቃላይ ኪራይ ሰብሳቢነትን አደጋ ተገንዝቦ ትግል የማካሄድ ጅምር እንቅስቃሴ ይታያል። ህዝባዊ አድነትን የሚጎዱ የፀረ-ዴሞክራሲና የጥፋት አስተሳሰቦች እየቀነሱ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ መጎልበት ጀምሯል። የህዝቡን አንገብጋቢ ችግሮች ለይቶ የመፍታት ጅምር ጥረቶች በመታየት ላይ ናቸው።

እነዚህ ጅምር ሁኔታዎች ግን የተኃድሶ ንቅናቄውን ወደ ማይቀለበስበት ደረጃ አላደረሱትም አሁንም የአስተሳሰብና የአፈፃፀም ችግሮች በርካታ ናቸው። የስልጣን አተያይና አጠቃቀም ጋር የተያዙ ችግሮችና በጥልቅ ተኃድሶ ንቅናቄ የተለዩት ችግሮች ሙሉ በሙሉ ሊቀለበሱ የሚችሉት ተግባርንና ውጤታማነትን ማዕከል ያደረገ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ግንባታ በቀጣይነት ማረጋገጥ ሲችል እንደሆነ ግምገማዎች ያረጋግጣሉ። የጥልቅ ተኃድሶ ቀጣይነት ይጠይቃል። የህዝቡ ቅሬታ ምንጭ የሆኑ ዝቅተኛ ምርታማነት፣የአገልግሎት ጥራትና ተደራሽነት ችግሮች ገና መሰረታዊ ለውጥ አልመጣባቸውም። ለዴሞክራሲያዊ አንድነት እንቅፋት የሆኑ ኃላ ቀርና የጥፋት ፖለቲካ አስተሳሰቦች ተወግደው ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነትና ዴሞክራሲያዊ አንድነት ማረጋገጥ ይጠይቃል።

የ2010 እቅድ ከላይ የተጠቀሱትንና በሁኔታ ተተንትነው የተለዩትን ችግሮችና ማነቆዎች ለመፍታት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። የፖለቲካና የድርጅት ስራ የንቅናቄ እቅዱ በሁለት ክፍሎች ተዋቅሯል። የመጀመሪያው ክፍል የሁኔታ ግምገማ፤የግምገማው ድምዳሜዎችና አንደምታዎችን ይዟል። የእቅድ ሁለተኛው ክፍል ተግባርና ውጤታማነትን ማዕከል ያደረገ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ግንባታ አላማና ግቦችን፣ተግባራትንና የአፈፃፀም አቅጣጫዎችን እንዲሁም የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍትሔዎችን ይመለከታል። የተግባራቱን ፈፃሚ አካላት ጠቅሷል። ይህ እቅድ መሪ የፖለቲካና ድርጅት ስራ እቅድ ሆኖ በዘርፎችና በወቅታዊ ተግባራት ላይ ራሳቸውን የቻሉ እቅዶች እየተዘጋጁ ተግባራዊ እንደሚሆን ታሳቢ አድርጓል። እቅዱ መነሻ ሆኖ በተቋማትና በየደረጃው ከአካባቢ ሁኔታ ጋር እየተገነዘበ ተግባራዊ እንደማይሆን ይጠበቃል።

## ክፍል አንድ

### 1. የእቅዱ ዋና ዋና መነሻ ሁኔታዎች

### 1.1 የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄ የሚገኝበት ሁኔታ

የአመራር ኃላፊነትና ስልጣን የህዝቡ ኑሮ መለወጫ መሳሪያ መሆኑ እየቀረ ስልጣንና ኃላፊነትን አተያይና አጠቃቀም እየተዛባ ከመሄዱ የተነሳ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ አጋማሽ አንስቶ ህዝባዊ ቁጣ መቀስቀሱ ይታወሳል። ይህው ህዝባዊ ቁጣ ኢህአዴግ በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄ እንዲያካሂዱ ማስገደዱ ግልፅ ነው። የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄው ሁለት ወሳኝ ጉዳዮችን ማዕከል ያደረገ ነበር። እነሱም የድርጅቱ አመራርና አባላት ከፍተኛ የአስተሳሰብ ዝቅጠት ውስጥ በመግባታቸው፤የልማታዊ

ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ እየተዳከመ የኪራይ ሰብሳቢነትና የጥፋት አስተሳሰብ ሰፍኗል። ይህው የአስተሳሰብ ዝቅጠት የወዳጅና ጠላት ጎራ ተቀላቅለው እንዲታዩ አድርጓል የሚል ነበር። ሁለተኛው መሰረታዊ ችግር በተግባር ተንቀሳቅሶ የህዝቡን አንገብጋቢ ችግር የሚፈታ ተግባራዊ ለውጥ ያለማምጣት ችግሮች ጋር የተያያዙ ነበሩ። ሁለቱም መሰረታዊ የአስተሳሰብና በተግባር ለውጥ ያለማምጣት ችግሮች ተደምረው ድርጅቱንም ሆነ አገሪቱን መስቀለኛ መንገድ ላይ እንድትቆም አስገዷል የሚል መሰረታዊ ግምገማ ነበር።

የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄ መሰረታዊ አላማ፣የድርጅቱን አመራርና አባላት ከገቡበት የአስተሳሰብ ዝቅጠት በማውጣት ቀድሞ ወደ ነበረን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ የአስተሳሰብ የመመለስና በህዝባዊ ባህሪያችን ላይ ተመስርቶ የህዝቡን አንገብጋቢ ችግሮች የሚፈታ አመራር የማረጋገጥ አላማን የያዘ ነበር። በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄው የት ላይ ደርሶል? በወቅቱ የተለዩት የአስተሳሰብና የአፈፃፀም ችግሮችስ? ከተሀድሶ ንቅናቄ በኃላ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛሉ?

በአመራሩና በአባላት ፖለቲካና ሪዮታአለማዊ ግልፅነት ለመፍጠር መዋቅሩ ከጎራ መደባለቅ ወጥቶ የአስተሳሰብ ግልፅነት ለማስያዝ ሰፊ ንቅናቄ ተካሂዷል። የአስተሳሰብ ግልፅነት የሚያሲዙ የተለያዩ ሰነዶች እየተዘጋጁ በየደረጃውና በተቋማት አመራርና አባላት በሲቪል ሰርቪስና በህዝቡ ዘንድ የአስተሳሰብ ትግልና ግልፅነት የማስያዝ ተግባራት ተከናውነዋል። ከአንድ አመት የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄ በኃላ በድርጅቱ ውስጥ አንዣቦ የነበረውን የጥፋት ፖለቲካ ተቀይሮ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ አቅጣጫ ይዟል። ጎራው ተደባልቆ የነበረው የወገንና የጠላት አስተሳሰብ በአሁኑ ወቅት የወገንና የጠላት ጎራ ተለይቶ ትግል መካሄድ ተጀምሯል። ለመስመሩ ዘብ የሚቆምና የሚታገል ኃይል ተፈጥሯል። በተካሄዱት ድርጅታዊ ኮንፈረንሶች ተከትሎ በተካሄዱት የአካል ግምገማና የግለሂስ እንዲሁም የተሻሻሉትን መርጦ መልሶ በማደራጀት ብሎም ወደ አመራር ስልጠና በማስገባት በተካሄደው የአቅም ግንባታ ስራዎች በአስተሳሰብ ደረጃ ድርጅታችንን ከመስቀለኛ መንገድ አውጥቶ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ጎዳና እንዲይዝ አስችሏል።

የተሀድሶ ንቅናቄው ለይቶ ያስቀመጠው ሁለተኛው ችግር በሙስና የሚገለፀው የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባር የለውጥ ጉዞውን እያደናቀፈ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዚህ ችግር ዙሪያ መሰረታዊ ለውጥ የማምጣት ጉዳይ ነበር። አመቱን ሙሉ የተካሄዱ የንቅናቄ መድረኮች የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ አደገኝነትና መፍትሔዎች ላይ ግንዛቤና ንቃት ጨምሯል። በአመራሩ መካከልም ሆነ በአመራሩና በህዝቡ ውስጥ ትግልና መደፋፈር እድገት እየታየበት መጥቷል። ከሙስና አንፃር ጥቆማ የቀረበባቸውና እንዲጣሩ ውሳኔ የተላለፈባቸው ጉዳዮች በወሳኝነት ተጣርተው ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ተሰጥቷል። በማጣራት ሂደቱ እንደተረጋገጠው ጥፋት ፈፅመው የተገኙት አመራሮች መሬት ሽሚያ ላይ ያተኮሩ ነበሩ። በተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ፣ ጥቅማጥቅም የማግኘት ሁኔታም ታይቷል። ሌላው ከቤት መሸጥና መግዛት ጋር ተያይዞ የግብር መሰወር አዝማሚያዎችም ታይተዋል። ሌሎች በቅጥር፣ በዝውውርና በመሰል ተግባራት የስጋ ዘመዶችንና የሚቀርቡትን የመጥቀም ጉዳዮችም በችግሮቹ ውስጥ የተገኙ ናቸው። ይህ የመተጋገል ጅማሮ በውስጠ ድርጅትም ሆነ በህብረተሰቡ መካከል መተማመንን በማጎልበት በኩል አወንታዊ አዝማሚያ በመፍጠር ላይ ይገኛል።

የተሀድሶው ንቅናቄው በትኩረት ከለያቸው ጉዳዮች ውስጥ ሶስተኛው የውስጠ ድርጅት ዲሞክራሲያዊ አንድነት የማስፈንና የማስቀጠል ጉዳይ ነበር። በተካሄደው ንቅናቄ የውስጠ ድርጅት ሁኔታው አሁንም ከፀረ-ዲሞክራሲና አድርባይነት ሙሉ በሙሉ የፀዳ ሆኗል ማለት ባይቻልም ብዙ መሻሻሎችና ለውጦች እየታዩበት መጥቷል። በድርጅቱ ስራ አስፈፃሚ እንዲሁም ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ዴሞክራሲያዊ አንድነት እድገትና መሻሻል ታይቷበታል። በአመራሩ መካከል ወደ ታችና

ወደ ጎን መሰረታዊ መርሆዎች አስቀምጦ በመርሆዎቹ መሰረት ትግል እያካሄደና እየወሰነ ተግባራዊ በማድረግ እረገድ መሰረታዊ መሻሻል በመታየት ላይ ነው። መርህ የለሽ ትስስርና ተቧድኖ መጠቃቀም ሆነ መጠቃቃት አሁንም ቀጣይ ስራ የሚጠይቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የመቀነስ አዝማሚያ ይታይበታል።

የተሀድሶ ንቅናቄ በተጀመረበት ወቅት ከተለዩት መሰረታዊ ችግሮች መካከል ዴሞክራሲያዊ አንድነታችንን የሚፈታተኑ የትምክህት፣የሀይማኖት ሽፋን ያደረገ አክራሪነት ጎጠኝነት ችግሮች እንደሆኑ ግልፅ ነው። ችግሮችን በአስተሳሰብም ሆነ በተግባር ለመፍታት በተካሄደው ትግል ከዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነትና ዴሞክራሲያዊ አንድነት ውጭ ያሉ አማራጮችን አንድነት እንደማያመጡና ቆምንለት ለምንለው ህዝብም ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያስከትል በተሻለ ሁኔታ መገንዘብ ጀምሯል። አመራሩ የትምህርት አስተሰሳሰብ ነው ብሎ መናገር ይፈራ ከነበረበት ሁኔታ ወጥቶ መድረኮች ፊት ለፊት መታገል የጀመረና መድፈር እያሳየ ያለው ኃይል እየጨመረ መጥቷል። ምንም እንኳ ከፍትሐዊ የመሰረተ ልማት ተጠቃሚነት ጋር የተያያዙ አስተሳሰቦችና ከዚህ ጋር ግንኙነት ያላቸው የትምክህት ዝንባሌዎች ገና የሚፈለገው ግልፅነትና መተማመን የተያዘባቸው ባይሆኑም በአብዛኛዎቹ ግልፅነት ያልታየባቸው ጉዳዮች ጠንካራ ትግልና የአስተሳሰብ ግልፅነት ተይዞባቸዋል። ጎጠኝነትና ሀይማኖትን ሽፋን ያደረጉ የአክራሪነት አስተሳሰቦችም ቢያንስ ቢያንስ ጎራ የለየ ትግል የሚካሄድባቸው ሆነዋል።

ገና ብዙ ስራ የሚጠበቅ ቢሆንም፣ ህዝቡ አንገብጋቢ ችግሮች ናቸው ያላቸውን የዝቅተኛ ምርታማነት ጉዳዮች፣ የስራ አጥነት፣ የኑሮ ውድነት፣ አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን በቅርብ የማግኘትና መደበኛ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት ዝግጁነትና ተጨባጭነት ያላቸው በጅምር ላይ የሚገኙ መሻሻሎችና ውጤቶች ተመዝግበዋል። የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ፤የአርሶ አደር ስልጠናና የግብአት አቅርቦት ስራዎች ተሰርተዋል። የአምራች ኢንድስትሪ መስኮችን ምርታማነትና መስፋፋት ለማሻሻል በጥቃቅንና አነስተኛ በመካከለኛ አምራቾች የውይይት፣የመሬትና ሌሎች አቅርቦቶችን ለመደገፍ ጥረቶች ተካሂደዋል። ከአገልግሎት ጥያቄዎች አኳያ ዞን፣ወረዳና ቀበሌዎችን ቅርበት ያለው አስተዳደር አገልግሎት ሊሰጡ በሚችሉበት ደረጃ ለማደራጀት ተሞክሯል። ከመሬት ህገ-ወጥ ወረራና ሌሎች የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በአካባቢው ለይቶ ለመፍታት ጥረቶች ተካሂደዋል። ተሀድሶው በአስተሳሰብና በተግባር ካስመዘገባቸው ለውጦች ባሻገር፣ ለቀጣይ አቅም የሚሆኑ የአመራሮችንና የአሰራር አደረጃጀቶችን ከክልል አንስቶ እስከ ህዋስና ልማት ቡድን ድረስ ለማጠናከር ጥረቶች ተካሂደዋል።

ከላይ የተጠቀሱት የተሀድሶው ውጤቶችና አወንታዊ አዝማሚያዎች ሲሆኑ፣ በአንፃሩ ቀጣይ ስራ የሚጠይቁ ተግባራትና አሉታዊ አዝማሚያዎችም በርካታ ናቸው። የቆዩ የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች በሚፈለገው ጥራትና ፍጥነት እየተፈቱ አለመሆናቸው እንዲሁም ጥልቅ ተሀድሶው ህዝቡ ውስጥ የቀሰቀሰው ተጨማሪ የለውጥ ፍላጎት ተደምሮ፣ አሁንም በርካታ የአስተሳሰብም ሆነ የተግባር ችግሮች ለውጥ ይፈልጋሉ። "ምርጥ ምርጥ ሀሳቦች እየቀረቡ ብንወያይም በተጨባጭ ተግባር የተደገፈ ለውጥ ካላየን ምን ዋጋ አለው?" የሚል ጥያቄ እንዲነሳና ከመጣው ለውጥ ባሻገር የማየት ሁኔታ ተጠናክሮ ቀጥሏል። ከአስተሳሰብ አኳያ የድርጅቱ አባላትና ህዝቡም እንዲፈቱ የጠየቋቸው የወሰንም ሆነ ሌሎች ጥያቄዎች በወቅቱ ባለመፈታታቸው፣ አሁንም ተደጋግመው የሚነሱ የግልጽነት ጥያቄዎች አሉ። ጥቂት የማይባሉ አመራሮችና ምሁራን አባላት በጥልቀት ገብተውበት ከነበረው የአስተሳሰብ ዝቅጠት አሁንም ሙሉ በሙሉ መውጣት ያልቻሉበት ሁኔታ ይስተዋላል። "አሁንም ፍትሀዊ ልማትና ፍትሀዊ ተጠቃሚነት አልመጣም" የሚል የምሬትና ችግሮችን ውጫዊ የማድረግ አስተሳሰቦች በቅጡ አልተሰበሩም። በተሟላ መልኩ ተጠርገው ያልተወገዱትን የአስተሳሰብ ችግሮችን እንዲሁም በተግባር ያልተፈቱ

የህዝብ ጥያቄዎችን መሰረት በማድረግ የጥፋት ኃይሎች የአመፅ ተግባሮችን ለማቀጣጠል ይሰራሉ። እነዚህ ተደምረው የለውጥ ንቅናቄዎቸን ለማደናቀፍ ጥረት ሲያካሂዱ ይስተዋላል።

በብአዴን-ኢህአዴግ ውስጥ የተጀመረው የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄ ተጠናክሮ፣ በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ተግባራዊ ለውጥ እያጎለበትን የተዛቡ አስተሳሰቦችን የሚሰብር ስራ ካልተካሄደ በስተቀር፣ ቁጥራቸው ጥቂት በማይባሉ አመራሮችና የሙህር አባላት ከድርጅቱ ውጭ የሚገኙ ሊሂቃን የተዛባ አስተሳሰብ የሚጋሩና "አማራ ተጠቃሚ አልሆነም፤ብአዴን በብቃት እየታገለ አይደለም፣የህዋሕት የበላይነት አለ በሚል" በአስቸጋሪ የአስተሳሰብ በሽታ ውስጥ እንደተያዙ እንዲቆዩ አስገድዷል።

የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ ትግል ቀጣይ እንጂ የአንድ ወቅት ብቻ ሊሆን የሚችል እንዳልሆነ የሚታወቅ ቢሆንም፣ ወቅቱ የሚጠይቀውን ለወጥ ለማምጣት የፀረ-ሙስና ትግሉ ውስብስብነትና የቁርጠኝነት ማነስ አሁንም ተግባሩ ከጅምር አልፎ እንዳይሄድ ተጽዕኖው ቀላል አልነበረም። በሂደቱም መጠቃቃትና መሸፋፈን መስተዋላቸው አልቀረም። የወሰን ጥያቄ በወቅቱ የተፈታ አለመሆኑና አሁንም ከሙብራትና ከመንገድ ልማት ጥያቄዎች ጋር ተያይዞ ማማረርና ልማትና ተጠቃሚነት እንደሌለ አድርጎ መግለጽ እንዲሁም የትምክህት አስተሳሰብ በሚፈለገው ደረጃ አልተሰበረም። የህዝብ አንገብጋቢ ችግሮች ተብለው የተለዩት፣ የአፈታት ሂደታቸው በጅምር ላይ የሚገኝ በመሆኑ የሚፈለገው ህዝባዊ እርካታ አልመጣበትም።

የመልሶ ማደራጀትና አደረጃጀቶችን እስከ ህዋስና ልማት ቡድን ድረስ ለማጠናከር የተሰሩ ስራዎች ቢኖሩም፣ ጅምርና በተለይም የታችኞቹ የመሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ አደረጃጀቶች መሰረታዊ ለውጥ ያልመጣባቸው ሆነው ይገኛሉ።

የተጀመረውን የአመራር ስልጠና በማስፋትና ተደራሽነቱን በማሳደግ እንዲሁም ተግባርን ማዕከል ያደረገ የኮር አመራሮችና የአባላት ግንባታ አማካኝነት የለውጥ ሰራዊት መገንባት ይጠይቃል። ወደ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ተግባር በማስገባት፣ በሁሉም መስኮች የለውጥ ማዕበል ማቀጣጠል፣ይጠይቃል። በሁሉም አቅጣጫ ለውጥ ካልመጣ በስተቀር የተጀመረው ለውጥ የመቀልበስ አደጋ ሊያጋጥመው ይችላል። ይህንን አደጋ በብቃት ለመዋጋት የአስተሳሰብና የተግባር ለውጥን በሁሉም አቅጣጫ ማፋፋም አማራጭ የለውም።

## 1.2 የአመራሮችና አባላት ሁኔታ፣

### 1.2.1 የአመራር ሁኔታ፣

#### ሀ/ የማዕከላዊ ኮሚቴ ሁኔታ፣

አመራሩ ራሱን እያደሰ የድርጅቱን መዋቅር ለማደስ ተንቀሳቅሷል። ማዕከላዊ ኮሚቴው ተሀድሶው በተጀመረበት ወቅት ከነበረበት የጎራ መደበላለቅ አስተሳሰብ ወጥቶ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ይዞ መታገል ጀምሯል። በሙስና የሚገለፀው ኪራይ ሰብሳቢነት ጎልቶ ያልተገኘበት ከመሆኑም በላይ ሌሎችንም ለመታገል በጅምር የሚታይ ተነሳሽነት አሳይቷል። በአመራሩ መካከል ዴሞክራሲያዊ አንድነት መሻሻልና እድገት ይታይበታል። ዴሞክራሲያዊ አንድነትን የሚፈታተኑ የትምክህት አስተሳሰብና ተግባራት ያደረሱትን ጥፋት ለማረምና ለማስተካከል ጥረት በማካሄድ ላይ ነው። በመዋቅሩ የሚታዩ የትምክህትና ተጓዳኝ ችግሮችን መታገል ጀምሯል። ህዝቡ ያነሳቸው አንገብጋቢ የምርታማነት፤የስራ አጥነትና ከኑሮ ውድነት እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች ለመፍታት እንቅስቃሴዎች አካሂዷል። ምንም እንኳ ህዝቡ ከሚጠብቀው አኳያ ተፈላጊው ደረጃ ባይደርስም የተመዘገቡ መሻሻሎች ለቀጣይ አቅም የሚሆኑ ናቸው።

ማዕከላዊ ኮሚቴው የተጠቀሱትን አወንታዊ አዝማሚያዎች የያዘ ቢሆንም አሁንም ከቆዩት የአስተሳሰብ ግልፅነት መጓደል ሙሉ በሙሉ ግልፅነትና እምነት እንዲሁም ቁርጠኝነት ያልያዘባቸው ጉደዮች አሉ። በመስመሩ ላይ ጥረት ያለ አስተሳሰብ፣ጥልቅ ምንነትና ቁርጠኝነት ይዞ ችግሮችን በመፍታት ረገድ ችግሮች አሉበት። ከስልጣን አተያይና አጠቃቀም ጋር የተለያዩና ግለሂስ የወሰዱባቸው ችግሮች ሙሉ በሙሉ ተላቋል ማለት አይቻልም። የፀረ-ሙስና ትግሉ በመድረክ የሚገለፀው በተግባር ትግል ማካሄድ ላይ ወጣ ገባነት እና ቁርጠኝነት ማነስ ችግር አሁንም ሙሉ በሙሉ አልተሻገራቸውም። ዴሞክራሲያዊ ትግሉና የአመራር አንድነት ግንባታ ሂደቱን በጅምር ያለና በሚፈለገው ደረጃ አልደረሰም። “ ከመሰረተ ልማት (መንገድ፣መብራትና ሌሎችም) መስኮች ጋር አያይዞ ፍትሀዊ ተጠቃሚነት አልተረጋገጠም ” የሚሉ ከትምክህት ጋር ግንኙነት ያላቸው አስተሳሰቦችና ዝንባሌዎች ይታዩበታል። የፍትሐዊ ተጠቃሚነት ችግሮች አሉ ብሎ በለያቸው መስኮች በውስጠ ድርጅት ትግል ለመፍታት ከመንቀሳቀስ ይልቅ መድረኮችን ሳይለይ “ እዩልኝ ስሙልኝ ” አይነት ትግል ማካሄድ ይታይበታል። የዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነትና የዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባታ ሂደቱ ደካማ ነው። የህዝብን አንገብጋቢ ችግሮች በመፍታት ረገድ በፍጥነትና በጥራት ከመፍታት አኳያ ዳተኝነት ይታይበታል። አመራሩ በአወንታ የተጠቀሱትን መነሻ አቅሞች ይዞ ድክመቶቹ ላይ በመረባረብ የህዳሴ ጉዞው አመራር ለመሆን ብርቱ ጥረት ይጠይቀዋል።

**ለ/ የከፍተኛ አመራር ሁኔታ**

አመራሩ በጥልቅ ተሀድሶና በግለሂስ ሂስ ያለፈ ነው። የተሻለ አስተሳሰብ እንዳለውና የስራ ዲስፕሊኑ ጥሩ እንደሆነ ተገምግሞ በመልሶ ማደራጀቱ አልፎ አመራር የሆነ ነው። የሚበዛው አመራር የከፍተኛ አመራር ስልጠና ወስዷል። በሙስና የሚገለፀው ኪራይ ሰብሳቢነት ላይ የማጣራት ሥራ ተካሂዶ እስካሁን የጎላ ችግር አልተገኘበትም። የህዝቡን አንገብጋቢ የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመፍታት መነሳሳትና ዝግጁነትም ይታይበታል።

የተጠቀሱት አወንታዊ አዝማሚያዎች የሚታዩበት አመራር ቢሆንም፣ በአስተሳሰብ ደረጃ ዴሞክራሲያዊ አንድነትን የሚፈታተኑ አስተሳሰቦችንና ተግባራትን ከራሱ ነፃ አድርጎ ሌሎችን በመታገል በኩል አሁንም ሙሉ በሙሉ የተሻገራቸው አይደሉም። ከሙስና ጋር በተያያዘ ጥቆማ ከቀረበባቸው መካከል 48 በመቶዎቹ ከችግሩ ጋር በተያያዙ ጥፋቶች ተገኝተውባቸዋል። የፀረ-ሙስና ትግሉ ወጥነት ያለውና ጠንካራ አይደለም። በቀጣይ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበትና የበለጠ ህዝባዊ መተማመንን ማሳደግ ይጠይቀዋል። ዴሞክራሲያዊነትን በማጎልበት ህይወት ያለው ትግል በማካሄድ ረገድ ገና ብዙ ስራ ይጠይቀዋል። የህዝብን አንገብጋቢ የልማትና የመልካም አስተዳደር እንዲሁም የስራ አጥነት ችግሮች በመፍታት ረገድ የጥራት፣ የተደራሽነትና የውጤታማነት ችግሮቹ ሰፋ ያሉ ናቸው። ህዝቡ በሚጠብቀው ደረጃ ውጤታማ ስራ በመስራት ረገድ፣ የዳተኝነትና የቁርጠኝነት እንዲሁም የአቅም ማነስ ችግሮች ይታዩበታል። ከፍትሀዊ ልማትና ተጠቃሚነት ጋር ተያይዞ ከራሱ የሚጠበቀውን ተልዕኮ በብቃት ሳይወጣ፣ አሻግሮ የማየትና የማማረር ችግሮች ይታዩበታል። በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች አስተሳሰቦችንም ፊት ለፊት አይታገልም። የታችኞቹን አደረጃጀቶች በማጠናከርና የተቋም ግንባታ ማካሄድ ረገድ፣ አሁንም መሰረታዊ ችግሮች አሉበት። በስልጠና ያላለፉና እንዲሁም እንደየ አግባቡ በስልጠና ማለፍ ያለባቸው አመራሮች ያሉ መሆናቸውም መጠቀስ የሚገባው አሉታዊ ሁኔታ ነው።

**ለ/ የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት መዋቅር አመራር ሁኔታ**

በጽ/ቤቱ ከክልል እስከ ወረዳ ባሉት አደረጃጀቶች አንድ ሺህ የሚደርሱ አመራሮች ተመድበው ይሰራሉ። በነዚሁ አደረጃጀቶች አራት መቶ ድጋፍ ሰጭዎች አሉ። በጽ/ቤቱ የተመደቡ አመራሮች በተሀድሶ አልፈው በመልሶ ማደራጀት የቀጠሉና በአዲስ መልክ የተመደቡ ናቸው። በስራው መስክ ከ3 ዓመትና በላይ የሰሩ 25 በመቶ ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ ከዚህ ያጠረ የአገልግሎት ዘመን ያላቸው ናቸው። በ2009 ዓ.ም የጽ/ቤቱ ማዕከላዊ ተልዕኮ ላይ አተኩሮ መንቀሳቀስ ጀምሯል። በዓመቱ የተሀድሶ ንቅናቄውን በማቀድ፣ በማስተባበርና በመምራት ከፍተኛ ሚና ነበረው። በአስተሳሰብና በአደረጃጀት ላይ አተኩሮ ግንባታ ማካሄድም ጀምሯል። በክልሉ ለተፈጠረው የፖለቲካ መሻሻል ድርሻውን በመወጣትም ላይ ነው።

የተጠቀሱት ጥንካሬዎች ያሉ ቢሆንም፣ ሊስተካከሉ የሚገባቸው ትልልቅ ድክመቶች የሚታዩበት ነው። የብአዴን አደረጃጀቶችን የማጠናከር ኃላፊነት በየደረጃውና በተቋማቱ የሚገኙ ጠቅላላ የድርጅት አመራሮችና አባላት ቢሆንም፣ ማዕከላዊ ተልዕኮው የብአዴን ጽ/ቤት መዋቅር መሆኑ ግልጽ ነው። ከክልል እስከ ቀበሌ የሚገኘው የብአዴን ጽ/ቤት መዋቅር፣ በአባላት የሚስተዋሉ አወንታዊና አሉታዊ አዝማሚያዎችን እየገመገመ፣አወንታዊ ዝንባሌዎችን በማጠናከር አሉታዊ አዝማሚያዎችን የሚመክትና የሚያስተካክል የአስተሳሰብ ስራን አደረጃጀቶችን ማዕከል አድርጎ መስራት ይጠበቅበታል። ይህ ተግባር ከትክክለኛ የሁኔታ ገምገማ በመነሳት፣ የመወያያ ሰነድ ዝግጅትና የማስፈፀሚያ እቅድ እንዲሁም ዑደቱን የጠበቀ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ስራ በቀጣይነትና በታዳጊነት ከመስራት ጋር በእጅጉ ይያያዛል። ተግባሩ ሰነድ ከማዘጋጀትና ከመሰማራት ባሻገር፣ ጠንካራ የአስተሳሰብ ትግልና የአደረጃጀት ግንባታን በማካሄድ ሊሳካ የሚችል ነው።

ይህ ተልዕኮ በቃልም ሆነ በጽሁፍ እንደሚገለፀው ቀላል አይደለም። ከባድ ተልዕኮ ነው። ተልዕኮው የሚጠይቀው ዝግጅነት፣ እውቀትና ክህሎት እንዲሁም ቁርጠኝነት በስራው ውስጥ ካለፉትና ካሉት በላይ የሚገነዘበው አለ ለማለት ያስቸግራል። ይህንን የመሰለ ተግባር  ለዓመታት መስራት ትልቅ ቁርጠኝነትን ይጠይቃል። በጽ/ቤቱ ውስጥ ያለው መዋቅር የሚያረፍድበት እንጂ ውሎ ሊያድርበት የማይፈልግ ሲሆን ይስተዋላል። መሰልቸት፣ መዳከምና ሌሎች አማራጮችን ማማተር በስፋት ይስተዋላል። ቁርጠኝነት ማጣትና ጀምሮ መተው ይታያል። የራሱን መደበኛ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ስራ ከመስራት ይልቅ፣ ወደ ህዝቡ በመሄድ የህዝቡን ስራ መንብኘት እንዲሁም ስብሰባን እያሳደዱ በየመንግስታዊ ስብሰባዎች መገኘት፣ አድካሚ ባልሆኑና ላይ በላይ እየሄዱ የመኖር ሁኔታ ከተሀድሶ ወዲህም አልተወገደም። ዋና ተልዕኮን ለቀን ለምን ቀጥታ በማይመለከተን ጉዳዮች እንገባለን ሲባል “ተጠራን እንጂ እኛ ምን እናድርግ”? በሚል ውጫዊ ምክንያቶችን የመጥቀስ ዝንባሌ ይታያል። በስራው ውስጥም ቆይቶ የውጤታማነት ችግሮች በራሳቸው ሊፈቱ የሚገባቸው ናቸው። የተጠቀሱትም ሆነ የሌሎች ችግሮች መነሻ መሰረቱ፣ ተልዕኮው የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል ያለመዘጋጀትና ከውግንና ማነስ ጋር የተያያዘ ነው። በመሆኑም ችግሮቹን ከስር መሰረታቸው የሚፈታ ግምገማ በማካሄድና በማስተካከል ቀጣይ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት መረባረብ ይጠይቃል።

አመራሩ ፖለቲካዊ አዝማሚያዎችን በጥልቀት እየተነተኑ የመምራት ጉድለት ከፍተኛ ነው። የአመራር ጥበብና የክህሎት ችግሮች ቀላል አይደሉም። የለውጥ አስተሳሰቦችን በማመንጨትና በተግባር ተጣብቆ ውጤት በማምጣት ላይ መሰረታዊ ድክመቶች አሉበት። በመወያያ ሰነዶች ዝግጅትና እቅድን ከባቢያዊ አድርጎ በመምራት በኩል ጠባቂነት ይታይበታል። በጠንካራ አባላት ልየታና ምልመላ፣ በጠንካራ አመራር ልየታና ምልመላ እንዲሁም በቀጣይ ግንባታ፣ጥራቱን የጠበቀ የአመራርና የአባላት ማህደር አያያዝ ላይ መሰረታዊ ድክመት ያለበት ነው። በአዲሱ ዓመት እነዚህን ችግሮች የሚፈታ ንቅናቄ ይጠበቃል።

**ሐ/ የመካከለኛ አመራሩ ሁኔታ**

መካከለኛ አመራሩ በጥልቅ ተሀድሶ ያለፈና ግለሂስና ሂስ አካሂዶ በመልሶ ማደራጀቱ በአመራርነት እንዲቀጥል ይሁንታን ያገኘ ነው። የሚበዛው አመራር የመካከለኛ አመራር ስልጠና ወስዷል። ለህዝቡ ቅርበት ያለው መዋቅር እንደመሆኑ፣ የህዝቡን አንገብጋቢ ችግሮች የበለጠ የሚረዳ ነው፤ ችግሮቹን ለመፍታት በመንቀሳቀስም ላይ ይገኛል። አብዛኛው አመራር ታታሪነት ይታይበታል። የፀረ-ሙስና ትግሉም ላይ በወሳኝነት የመታገልና ለውጥ የማምጣት ተነሳሽነትን አሳይቷል። በ2009 ዓ.ም ሁለተኛው መንፈቅ ዓመት ላይ፣ በልማትና በመልካም አስተዳደር መስኮች በተለይም ደግሞ ስራ ያልያዙ ወገኖችን ስራ ለማስያዝ የተለያዩ ጥረቶችን አካሂዶ ተሞክሮዎችን አግኝቷል።

መካከለኛ አመራሩ የተጠቀሱት ጥንካሬዎች ያሉት ቢሆንም፣ የህዝቡ ቅሬታ መነሻ መሰረት የሆኑትን የልማትና የመልካም አስተዳደር በተለይም ስራ ያልያዙትን ወገኞች ስራ በማስያዝ ረገድ የጥራት፣ የተደራሽነትና የውጤታማነት ችግሩ ሰፊ ነው። ህዝቡ የሚጠብቀውን የአገልግሎት ፍላጎት የሚያሟላ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት በማምጣት በኩል ገና ብዙ ስራ አለበት። በስልጠናና በተሀድሶ መድረኮች የፈጠራቸው ግንዛቤዎችና የአስተሳሰብ ግልጽነት ቢኖርም፣ አሁንም ከፍትሀዊ ተጠቃሚነትና ችግሮችን ወደ ውስጥ ከመመልከት ይልቅ፣ አሻግሮ የማየትና ውጫዊ የማድረግ ዝንባሌዎች አልተገወዱም። ከተግባር ጋር በተያያዙ ግምገማዎችና በልሳናት አማካኝነት ጠንካራ የአስተሳብ ግንባታ ይጠይቃል። በፀረ- ሙስና ንቅናቄ የማጣራት ሂደት እንደታየው፣ ጥቆማ ከቀረበባቸው እስከ 50 በመቶ የሚሆኑት በተለያየ ደረጃ የሚገለፁ ከመሬት፣ ከሀሰተኛ የትምህርት መረጃና ከአበል አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ችግሮች ታይተውባቸዋል። እነዚህን የመሳሰሉ ችግሮችንም በብቃት በመታገል በኩል፣ መርህ የጎደለው የትግል አግባብ ቀላል ባልሆነ ደረጃ ይታይበታል። ዴሞክራሲያዊ አንድነታችንን የሚፈታተኑ የትምክህት፣ የጠባብነትና የጎጠኝነት አስተሳሰቦችም ተጠርገው አልተወገዱም። ከስልጣን አተያይና አጠቃቀም እንዲሁም ከክህሎት ማነስ ጋር የሚያያዝ ሆኖ የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኛውን ሙያዊ አቅም በብቃትና በውጤታማነት የማሰማራትና ሙያዊ አቅሙን ወደ ስራ የማስገባት ተነሳሽነት ይጎለዋል። የታችኞቹን አደረጃጀቶች በማጠናከርና በመደገፍ ረገድም ለውጥ ማምጣት ይጠይቃል። በተለይ በከተሞች የተሰማራው አመራር የህዝብ መድረኮችን መርቶ ፊት ለፊት ተጋፍጦ መውጣት ላይ ድፍረት ይጎለዋል። በጥቅሉ መካከለኛ አመራሩ የቁርጠኝነት፣ የውጤታማነትና የተደራጀ አመራር የመስጠት አቅምና ዝግጅት የሚያመጣ ስራ ይጠይቃል።

**መ/ የታችኛው አመራር ሁኔታ፡-**

የታችኛው አመራር የምንላቸው የገጠርና የከተማ ቀበሌ አመራሮችን እንደሆነ ይታወቃል። ይህ የአመራር እርከን ተልዕኮዎችን ቆጥረን ባስያዝነው ልክ፣ ህዝቡን እያስተባበረ በርካታ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራትን እያከናወነ እንደመጣ ይታወቃል።

አመራሩ የጥልቅ ተሀድሶ በተቀሰቀሰበት ሁኔታ የራሱንና በተዋረድ ያሉ ችግሮችን በማየት በተሀድሶው አልፏል። የአመራር ማጥራትና በአዲስ መልክ የመቀየር ስራው ከወረዳ ወረዳ ልዩነት ያለው ቢሆንም፣ የከፋ ችግር ያለባቸው አመራሮች በህዝቡም ግፊት ጭምር ተደግፎ የማጽዳት ስራ ተሰርቷል። በተደጋጋሚ በተፈጠሩ መድረኮች እንደታየው አመራሩ ራሱን ግንባር ቀደም የለውጥ ተሰላፊ አድርጎ ሌሎችንም በማንቀሳቀስ በኩል የአብዛኛው መገለጫ ታታሪነት ነው። በበጋና በክረምት ስራዎች በገጠር የሚገኙ አመራሮች ለአባላቱና ለጠቅላላ አርሶ አደሩ ምሳሌ የሚሆኑ ስራዎችን ሰርተዋል። በከተሞችም ጥቃቅንና አነስተኛ እንቀሳቃሾችን በማስተባበር በከተሞች በሚከናወኑ የመሰረተ ልማት ስራዎች እንዲሁም

ለአገልግሎት አሰጣጥ መሻሻል ጥረት የሚያደርጉ አመራሮች በርካታዎች ናቸው። በገጠርም ሆነ በከተማ ቀበሌዎች ሙስናን በመታገልና በማረም በኩል መልካም እንቅስቃሴ በአብዛኛው ታይቷል።

የተጠቀሱት ጥንካሬዎች ያሉ ቢሆንም፣ከነባራዊ ሁኔታውና ከግንባታ ማነስ ጋር ተያይ በአመራሩ ዘንድ ህዝብን በአግባቡ ባለመያዝ የሚገለፅ ፀረ-ዴሞክራሲ ተግባራት ይፈፀማል። አመራሩ የቀበሌውን ሁኔታ አቀናጅቶ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት በሚያስችል የአደረጃጀት ቁመና ላይ አይደለም። በተለይም በገጠር ቀበሌዎች የተዘረጋው የሲቪል ሰርቪስ የልማት ተግባራት፣ አሁን ያለውን አደረጃጀት በአግባቡ የሚያሰማራው ሆኖ አይታይም። ቀበሌን በቅጡ መምራት የሚያስችል ወጥነት ያለው የአስተሳሰብ ግልጽነት፣ የማቀድና የመፈፀም ክህሎት እንዲሁም የአደረጃጀት ፋይዳ ላይ የተሟላ እምነት አልያዘም፤ ስልጠና አላገኘም። የፀረ-ሙስና ትግሉም ከአካባቢ አካባቢ የሚለያይና ወጣ ገባነት የሚታይበት ነው። የታችኞቹ አደረጃጀቶች መሰረታዊ ድርጅትና ህዋሳት እንዲሁም የልማት ቡድንና የአንድ ለአምስት አደረጃጀቶች ጥንካሬ፣ እንደ ቀበሌ አመራሮቹ የጥንካሬ ደረጃ ልዩነቱ ሰፊ ነው። በቋሚነት የአስተሳሰብ ግንባታ ለማካሄድ የትጋትና የዝግጁነት ችግሮች ይስተዋሉበታል።

በአጠቃላይ ይህ መዋቅር ህዝቡ ውስጥ የሚሰሩ ተግባራዊ ለውጦች የሚፈፀሙበት የአመራር እርከን ስለሆነ፣ በተግባር ለውጥ ማምጣት የሚያስችል የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ግንባታ ስልጠና የግድ የሚልበት ሁኔታ መታየት ይኖርበታል።

**1.2.2 የብአዴን አባላት ሁኔታ**

ብአዴን ከመንግስት ሰራተኞች፣ ከአርሶ አደሮችና ከጥቃቅንና ከአነስተኛ አንቀሳቃሾች፣ ከላብ አደሮችና ከተማሪዎች የተውጣጡ 1.6 ሚሊዮን የሚደርሱ አባላት አሉት። ከነዚህ መካከል ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት አርሶ አደር አባላት ሲሆኑ፣ ከጠቅላላው 69 በመቶ ይደርሳሉ። የሴቶች ተዋጽኦንም ስንመለከት ከጠቅላላ አባላቱ 21 በመቶ ይደርሳሉ።

አባላቱ በጥልቅ የተሀድሶ ንቅናቄ መድረኮችና በልሳናት አማካኝነት ተደጋጋሚ ውይይቶች ሲያካሂዱ የከረሙ ከመሆናቸውም በላይ፣ መድረኮችን ተከትሎ በግለሂስና ሂስ እንዲያልፉ ተደርጓል። ከአመራር ምልመላና ከኃላፊነት አሰጣጥ ሂደት አንስቶ፣ በዋና ዋና ድርጅታዊና መንግስታዊ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራት ግንባር ቀደም በሚሆኑበት ደረጃ ተሳትፎ ነበራቸው። የአባላቱን ሁኔታ ዘርዘር አድርጎ ለማየት እንዲረዳ የአርሶ አደር፣ የመንግስት ሰራተኞችና የአንቀሳቃሾች አባላት ሁኔታ በሚል ከፋፍለን እንደሚከተለው እንመልከት።

**ሀ/ የሲቪል ሰርቪስ አባላት (በተቋማት የሚሰሩና የመምህራን) ሁኔታ**

የሲቪል ሰርቪስና የመምህራን አባላት 172 ሽህ የሚደርሱ ሲሆን፣ አባላቱን ከገቡበት የአስተሳሰብ ዝቅጠት ለማውጣት በተሰራው ተከታታይ ስራ መሰረት በአብዛኛው ግልጽነትን ፈጥረዋል። የድርጅቱን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ጨምሮ፣ በልዩ ልዩ የአስተሳሰብ ግንባታ መድረኮች የተዛቡ አስተሳሰቦች እንዲስተካከሉ ሆነዋል። በሙስና የሚገለፀውን ኪራይ ሰብሳቢነት በመታገል በአብዛኛው ሚናቸው አወንታዊ ነበር። ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብንና ተግባርን በመታገል ዴሞክራሲያዊ ትግል እንዲካሄድ ሚና ነበራቸው። የህዝቡን አንገብጋቢ ችግሮች አጉልተው በማንሳትና በተወሰነ ደረጃ ራሳቸውም የለውጡ አካል በመሆን ጥሩ ጅምር ይታያል። ከቦታ ቦታ ልዩነት ቢኖራቸውም፣ በአደረጃጀታቸው የጠነከሩ የመሰረታዊና የህዋስ አደረጃጀቶች አሉ። በተግባርም አብዛኛዎቹ ግንባር ቀደም የሚባሉ ናቸው።

የተጠቀሱት ጥንካሬዎች ያሉም ቢሆን፣ ከሲቪል ሰርቪስና ከመምህራን አባላት ከሚጠበቀው የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ጥንካሬ አልተረጋገጠም። አባላቱ ለማህበራዊ ሚዲያ እንዲሁም ለወሬና ለአሉባልታ በእጅጉ የተጋለጡና የተዛቡ አስተሳሰቦች ሰለባ ሆነው የሰነበቱ ከመሆናቸውም በላይ፣ አሁንም ከችግሩ በሚገባው ደረጃ አልወጡም። ከድርጅቱ አጥር ውጭ ያሉ የተዛባ አስተሳሰብ ያላቸው ኃይሎች የሚታገሱ ሳይሆን ስሜት የሚጋሩ በርካቶች ናቸው። የራሳቸውን ችግር በጥልቀት ሳይመለከቱ አሻግረው መውቀስ የሚቀናቸው ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም። “ፍትሀዊ ተጠቃሚነት አልተረጋገጠም” በሚል አብዝተው የሚጮሁና የሚያማርሩ፣ነገር ግን የራሳቸውን ተልዕኮ በብቃት የማይወጡ ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም። በሙያቸው ህዝባዊ አገልግሎት በመስጠት እርካታን እየተጎናፀፉ ለሌሎች ምሳሌ በመሆን ረገድ መሰረታዊ ችግሮቹ እንዳሉ ናቸው። ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ ትግል፣ አድርባይነትና ፀረ-ዴሞክራሲ ይታያል። የትምክህት፣ የጎጠኝነት፣ የጠባብነት፣ የሃይማኖት አክራሪነትና መሰል አዳሐሪ ዝንባሌዎች ቀላል ባልሆነ ደረጃ ይታዩባቸዋል። ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት ዴሞክራሲያዊ አንድነት አስተሳሰብ ችግሮች ይታይሉ። “ወርሐዊ ክፍያ በዛብን” በሚልና በሌሎች የአስተሳሰብ መሸርሸር ችግሮች የተነሳ ከድርጅት የመውጣት ዝንባሌ ይስተዋልባቸዋል።

በድምሩ ይህ ኃይል የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አመራር መፈልፈያ ቋት ከመሆኑም በላይ፣ በራሱ የለውጥ ኃይል ሆኖ መንቀሳቀስ ከቻለ ተዓምር የሚሰራ ኃይል መሆኑን ታሳቢ ያደረገ፣ የተጠናከረ የአስተሳሰብና የተግባር (Delivery) ለውጥና ውጤት በሚያመጣበት ሁኔታ አደራጅቶ ለማነቃነቅ ከባድ ርብርብ ይጠይቃል።

### ለ. የአንቀሳቀሾችና የፋብሪካ ሰራተኞች አባላት ሁኔታ

በገጠርም ሆነ በከተሞች የሚገኙ አንቀሳቃሾችና የፋብሪካ ሰራተኞች አባላት ቁጥር በድምር -----ይደርሳል። አባላቱ በተሀድሶ መድረኮች አልፈዋል። የራሳቸውንና የሌላውንም ድክመት አይተዋል። ችግሮቹን ከተገነዘቡ በኋላ በየተሰማሩበት መስክ ውጤታማ ሆነው ለሌሎችም ምሳሌ የሆኑ አባላት በርካታዎች ናቸው። የሙስና ተግባራትን በማጋለጥ ፍትሃዊ አሰራር እንዲሰፍን የሚካሄዱት ጅምር ትግል አለ።

የተጠቀሱት ጥንካሬዎች ያሉ ቢሆንም፣ ከሲቪል ሰርቪስ አባላት ቀጥሎ ለማህበራዊ ሚዲያና ለሌሎች የጥፋት ቅስቀሳዎች ሰለባና የተጋለጡም ናቸው። የራሳቸውን ችግሮች ከማየት ይልቅ፣ ቀድሞ የሌሎችን ችግሮች ማየት ይቀናቸዋል። በአብዛኛው ጠባቂነት ጉልህ ችግር ሆኖ እንደቀጠለ ነው። ለዴሞክራሲያዊ አንድነት እንቅፋት የሆኑ አስተሳሰቦችንና ተግባራትን ታግሎ በማስተካከል ረገድ መሻሻሎች ቢታዩም፣ ገና መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጣ ስራ ይጠይቃል። አባላቱ በተደራጁበት የስራ ስምሪት መስክ ውጤታማ ሆነው በሰርቶ ማሳየት የሌሎች ምሳሌ በመሆን ረገድ፣ አብዛኛዎቹ በዛ ደረጃ ላይ የደረሱ አይደሉም። አልፎ አልፎ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ አቅም እያገኙ ሲሄዱ፣ ድርጅቱን የመልቀቅ ሁኔታ የሚታይባቸው አሉ። የህዋስና የመሰረታዊ ድርጅት አደረጃጀቶቻቸው ወጣ ገባነት ያለባቸውና በአብዛኛው ደካማዎች ናቸው።

የጥቃቅን አንቀሳቃሾችን ውጤታማነትና ግንባር ቀደምነት በማሳደግ፣ ለሌሎች ምሳሌ በሚሆኑበት የብቃት ደረጃ ላይ ለማድረስና አደረጃጀቶችን የማጠናከሩና የመገንባቱ ከባድ ርብርብ ይጠይቀናል።

### ሐ/ የአርሶ አደር አባላት ሁኔታ

አርሶ አደር አባላት በተሀድሶ ንቅናቄ መድረኮች ተከታታይ ተሳትፎና ውይይት አካሂደዋል። በመጀመሪያ አሻግሮ የማየት ሁኔታ ቢኖርም በሂደት ራሳቸውን በማየት በግለሂስና ሂስ አልፈዋል፤ የግል ኑሯቸውን የማሻሻልና ለሌሎችም ምሳሌ የመሆን

ንቅናቄም አካሂደዋል። ከበጋ እስከ ክረምት ሰፋፊ ተግባራትን አከናውነዋል፤ አብዛኛዎቹም ታታሪዎች ናቸው። በየአካባቢው የሚስተዋሉ የልማትና የመልካም አስተዳደር እንዲሁም የሙስና ችግሮችን በአብዛኛው ይታገላሉ።

የተጠቀሱት ጥንካሬዎች ይኑሩ እንጂ፣ አባላቱ በልሳናትና በተግባራዊ የልምድ ልውውጥ መድረኮች እንዲሁም በግምገማዎች ፖለቲካዊ አቅማቸውን እያሳደጉ በመሄድ በኩል ጉልህ ችግሮች ይስተዋሉባቸዋል። የፀረ-ዴሞክራሲ ተግባራትን ይሸከማሉ፤ በሚፈለገው ደረጃ በመታገል ላይም ችግሮች አሉ። መሰረታዊ ድርጅትንና ህዋሳትን በማጠናከር፣ በነዚህ አደረጃጀቶች አማካኝነት የህዝብ አደረጃጀቶች የልማት ቡድንና አንድ ለአምስት አደረጃጀቶችን እንዲጠናከሩ በትጋት የመንቀሳቀስ የግንዛቤ ውስንነትና ተነሳሽነት ያንሳቸዋል። አብዛኛዎቹ አባላት ታታሪና ግንባር ቀደም ቢሆኑም፣ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ መሰረታዊ የህይወት ለውጥ ያላመጡ እንዲሁም ለሌሎች ምሳሌ ያልሆኑ አባላት አሁንም ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም።

በጥቅሉ አርሶ አደር አባላቱን በብቃት ማነቃነቅ ከተቻለ፣ በገጠር ተጽዕኖ የመፍጠር አቅማቸው ከፍተኛ ነው። በመሆኑም በግምገማ የተለዩ ውስንነቶችንና ድክመቶችን በማስወገድ በ2010 ዓ.ም ግንባር ቀደምና ውጤታማ በሚሆኑበት እንዲሁም የተደራጀ ንቅናቄ በሚያካሂዱበት ደረጃ ማብቃት ይጠይቃል።

### 1.3 የሊግ አደረጃቶች ሁኔታ

#### ሀ) የሴቶች ሊግ ሁኔታ

የሴቶች ሊግ 311 ሽህ የሚሆኑ አባላት አሉት። የአመራሮችና አባላቱ በእናት ድርጅታቸው መድረኮችና በራሳቸው ልዩ ሁኔታ ባደራጃቸው መድረኮች የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄ አካሔደዋል። ግለሂስና ሂስ እንዲሁም የመልሶ ማደራጀት ስራ ሰርተዋል። በመደበኛ  የልማትና የመልካም አስተዳደር እንዲሁም በሰላም ማስፈን ሥራዎች ላይ የራሳቸውን ተልዕኮ እየፈፀሙ፣ለሌሎችም ምሳሌ የመሆን ተግባራት በአብዛኛው አከናውነዋል። በመካከለኛና በከፍተኛ አመራር የስልጠና መድረኮች ተሳትፈዋል፤ የሙስናና የፀረ- ዴሞክራሲ አፈፃፀሞችን በመታገል ረገድ በአወንታ የሚወሰድ እንቅስቃሴ ነበራቸው።

የተጠቀሱት መልካም ተግባራት የነበሩ ቢሆንም፣ ከአመራሮቹ አንስቶ እስከ አባላት አደረጃጀቶችን በአግባቡ ያለማጠናከር ችግሮች አሁንም ጐልተው ይታያሉ። በአደረጃጀቶች አወንታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ሴት አመራሮች እየመጡ ነው ማለት አይቻልም። ወደ አመራር የሚመጡትም ወደ ሌሎች የመንግስት ኃላፊነቶች መሸጋገሪያ አድርገው ይመለከቷቸዋል እንጂ፣ የሴቶችን አደረጃጀቶች ለማጠናከር ቁርጠኝነትንና መነሳሳትን ሲሰንቁ አይታዩም። የልማትና የመልካም አስተዳደር እንዲሁም የስራ አጥነት ችግሮችን የመፍታት ንቅናቄ ላይ ግንባር ቀደምና ምሳሌ ሆኖ ተልዕኮን ያለመወጣት ሁኔታ  አሁንም  ችግር ሆኖ  እንደቀጠለ ነው። አደረጃጀቶቹ  አልተጠናከሩም፤ ወደታች በወረድን ቁጥር ደግሞ የበለጠ ተዳክመው የሚገኙበት ሁኔታ ሰፊ ነው።

በዚህ ዓመት በአወንታ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች በመያዝና እጥረቶችን በማስተካከል፣ አደረጃጀቱ በራሱ ጠንክሮ የጠንካራ ሴት አመራሮች ምንጭ በሚሆንበት ደረጃ ማብቃት ይጠይቃል ።

### ለ) የወጣቶች ሊግ ሁኔታ

የወጣቶች ሊግ 484 ሽህ አባላትን ያቀፈ ሲሆን፣ በእናት ድርጅታቸው የጥልቅ ተሃድሶ መድረኮች ተሳትፈዋል። ከራሳቸው ሁኔታ ጋር የተቃኘ የማወያያ ጽሁፍ ተዘጋጅቶ በራሳቸው ውይይት ከማካሔዳቸውም በላይ፣ በግለሂስና ሂስ ከዚያም የመልሶ ማደራጀት አልፈዋል። ወደ ተግባር ምዕራፍ በተገባበት ሁኔታ ከሊግ አባላት መካከል ስራ ያላቸው ውጤታማ የሚሆኑበትን፣ ስራ ያልያዙት ደግሞ በተለያዩ የስራ መስኮች የሚሰማሩበትን ሁኔታ ቀይሰው ተንቀሳቅሰው አባላቱን ወደ ስራ አሰማርተዋል። ለሌሎች ወጣቶችም ምሳሌ የሚሆኑ ተግባራትን ለመፈፀም ተንቀሳቅሰው ጥሩ ስራዎችን አከናውነዋል። የተዛቡ አሰራሮችንና ፀረ-ዴሞክራሲ ተግባራትን የመታገል ጅምር እንቅስቃሴ ይታያል፤ በአመራር የስልጠና መድረኮችም ተሳትፈዋል።

የተጠቀሱት አወንታዊ ሁኔታዎች ቢኖሩም፤ የፀረ-ህዝብ አስተሳሰቦችን በተለያየ ደረጃ በመጋራት እና ከችግሩ ነፃ ቢሆኑም እንኳ፣ በብቃት ያለመታገል ችግሮች አሉ። ግንባር ቀደምም ያለመሆን ችግሮች ያሉባቸውም ብዙዎች ናቸው። አባላቱ የራሳቸውን ኑሮ በማሻሻልና ለሌሎች ምሳሌ በመሆን ረገድ በሚፈለገው ደረጃ አይደሉም። አልፎ አልፎ በአጉል ሱሶች የሚጠቁ እንዲሁም ይህን ማህበራዊ ጠንቅ በብቃት የሚታገሉ ሲሆን ይታያል።

ከድርጅትና ከመንግስት የመጠበቅ እንዲሁም አደረጃጀቶችን ወደ ሌሎች ኃላፊነቶች መሸጋገሪያ አድርጎ የመመልከት ዝንባሌ ይታያል። ህዝባዊ አንድነትን የሚጐዱ ጐጂ አስተሳሰቦችን የመጋራቱ ዝንባሌ ቀጣይ ስራ ይጠይቃል። የታችኞቹ አደረጃጀቶች ጥንካሬ የሌላቸውና የተዳከሙም ናቸው።

በቀጣይ መልካም ሁኔታዎችን በማጐልበት የአባላቱን ተግባራዊ ለውጥ ማዕከል ያደረገ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ግንባታ ማካሔድ በትኩረት ሊሰራበት የሚገባው ጉዳይ ነው።

### 1.4 የምክር ቤቶች፣የተከለኢህዴንና ሌሎች አደረጃጀቶች ሁኔታ

### ሀ. የምክር ቤቶች ሁኔታ፣

የተወካዮችና የክልሉ እንዲሁም የወረዳና የቀበሌ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች የድርጅት አባላት በመሆናቸው፣በአባላት ሁኔታ ትንተና ላይ ተጠቅሰዋል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ ምክር ቤት የህዝቡን የልማትና የዴሞክራሲ እንዲሁም የመልካም አስተዳደር አጀንዳዎች ለይተው በመታገልና ለውጥ በማምጣት ረገድ ችግሮች አሉባቸው። የምክር ቤት አባላቱ ተልዕኳቸውን በአግባቡ ካለመረዳት አንስቶ፣ የተረዱትም ቢሆን በብቃት የህዝቡን ችግሮች በአግባቡ አደራጅተው እያቀረቡና እየሞገቱ አልሔዱም። ምክር ቤቶቹንና አባላቱን በቀሪ የስራ ዘመናቸው ተልዕኳቸውን በአግባቡ በመወጣት እንዲሁም የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ሁኔታ ላይ ማብቃት ይጠይቃል።

ምክር ቤቶችን ከማጠናከር ጐን ለጐን፣ በ2010 የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤቶች ምርጫ የሚካሔድ በመሆኑ፣ ይህንኑ ችግር ሊያቀል በሚችል አግባብ የተሻለ ብቃት ያላቸውንና ስብጥሩን የጠበቀ የእጩ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ እንደመነሻ ሁኔታ መታየት አለበት።

### ለ. የተከለ ኢህዴን አባላትና አደረጃጀት ሁኔታ

ማህበሩ በቅርብ ተቋቋመ ቢሆንም፣ የአባላቱን ድጋፍ አግኝቶ በአጭር ጊዜ መስፋትና መጠናከር ጀምሯል። በቅርብ ጉባዔ አካሂዶ አደረጃጀቱን የሚያጠናክሩ ውሳኔዎችን አሳልፏል።

የተጠቀሱት መልካም አዝማሚያዎች ያሉ ቢሆንም፣ አባላቱ ውስጥ እያበቡ የመጡ የጠባቂነትና የተረጅነት አዝማሚያዎች ቀላል አይደሉም። ማህበሩ ከመንግስት ድጎማም ሆነ ከድርጅት የሚያገኘው ገንዘብና ለአባላቱ የሚሰጠው ድጋፍ፣ መነሻ እንጂ በቋሚነት መጦሪያ ሊሆን አይችልም። ከዚህ በተጨማሪ ድጋፍ ማግኘት ያለባቸውና የሌለባቸውም እኩል ተሰልፈው የሚያግባብቡበት ሁኔታ ይታያል።

እነዚህን የአስተሳሰብ መዛነፎችና በአደረጃጀት ዙሪያ ያሉ ችግሮች በመፍታት፣ ማህበሩ የአባላት መረዳጃ ማህበርነቱን አጠናክሮ አባላቱም በራስ መቻል መርሆ አቅማቸውን እያጎለበቱ የሄዱበት ሁኔታ መረጋገጥ ይኖርበታል። የመረዳጃ ማህበሩ አንድ የብአዴን አቅም ሆኖ፣ ብአዴንና ማህበሩ ተደጋግፈው የሚሰሩበትና በድምሩ የአባላቱ ብቻ ሳይሆን የመላ ህዝቡ የለውጥ አብነትና አለኝታ ሆነው እንዲሰሩ ማስቻል ይጠይቃል።

**ሐ/ ተመላሽ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ሁኔታ**

ተመላሽ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ለአገራቸው ከፍተኛ ከሚባሉት አስተዋጽኦዎች መካከል አንዱን ያደረጉ፣ ክብርና ሞገስም የሚገባቸው ናቸው። እነዚህ ኃይሎች ግዳጃቸውን ጨርሰው ከተመለሱም በኋላ በልዩ ልዩ አግባብ ለአገራቸው አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ናቸው። ክልሉም አቅም በሚፈቅደው ሁሉ ተደራጅተው የራሳቸውን ኑሮ እንዲያሻሽሉና በያሉባቸው አካባቢዎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ልማት ላይ የበኩላቸውን እንዲያደርጉ ጥረቶች በመካሄድ ላይ ናቸው። የተጠቀሰው አወንታዊ ሁኔታ እንዳለ ሆኖ፣ በተመላሽ ሰራዊት አባላት በኩል ሰፋ ያለ ጠባቂነት ይስተዋላል። በአመራሩ በኩል ደግሞ ችግሮቻቸውን ታግሎ በማስተካከል አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ከመደገፍ ይልቅ፣ ያዝ ለቀቅ ያሉ ድጋፎች ይካሄዳሉ። በ2010 ዓ.ም የእቅድ ዘመን የሰራዊት አባላቱ ራሳቸውን ጠቅመው አካባቢያቸውን በሚጠቅሙበት ሁኔታ የታቀደ ስምሪትና ድጋፍ ማካሄድ ይጠበቃል።

**1.5 የመንግሥት መዋቅር ሰራተኞች ሁኔታ**

በየደረጃውና በየተቋማቱ የሚገኘው የመንግስት መዋቅር ሁኔታ ሲገመገም፣ አመራሩ በአመራር የሁኔታ ግምገማ ውስጥ ተካትቶ ስለተጠቀሰ በዚህ ርዕስ ስር ደግሞ መተንተን አላስፈለገም። የመንግስት መዋቅር ሲባል በዋነኛነት ሲቪል ሰርቪሱን በኮሌጆችና በዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም በጠቅላላ ትምህርት ተቋማት የሚሰሩ (መምህራንን) ጨምሮ የተመለከተ ነው። በክልሉ የሚገኘው ጠቅላላ ሲቪል ሰርቪስ ቁጥር ከ 350 ሺህ ይልቃል። ከነዚህ መካከል በትምህርት ዝግጅታቸው ዲግሪና ከዛ በላይ የሆኑ 26 በመቶ የሚሆኑ ናቸው። ሌሎች በዲፕሎማና ከዛ በታች በሚገኙ የትምህርት ደረጃዎች ላይ የሚገኙ ናቸው። በተጨማሪ በክልሉ የተቋቋሙ የፌደራል ዩኒቨርስቲዎች ቁጥሩ ጥቂት የማይባል የተማረ የሰው ሀይል አቅም ያለ ሲሆን ይህን በልማታዊ አቅጣጫ መምራት ከተቻለ አቅም ሊሆን የሚችል ነው።

በየተቋማትና በየደረጃው የሚገኙ ሰራተኞች ባለፉት ዓመታት በመተዘገቡት ሁሉን አቀፍ ህይወታዊ ለውጦች፣ የበኩላቸውን አስተጽኦ አበርክተዋል። በሂደቱም በሙያዊ ብቃታቸው የተሻሻሉና ህዝብ የማገልገል ዝግጅነት ያላቸው ጥቂት የማይባሉ ባለሙያዎቸ ተፈጥረዋል። በተካሄደው የተሀድሶ መድረክ የተሳተፉ ሲሆን፣ በአመራሩ በኩል የሚታዩትን ችግሮች ከመገምገማቸውም በላይ የራሳቸውን ድክመት ተመልክተው ግለሂስና ሂስ አካሂደዋል። የስራው ጥራት የራሱ ውስንነት

ቢኖርበትም በመድረኮቹ ራሳቸውን አይተውና ተነሳሽነት ይዘው ወደ ስራ እንዲገቡ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ በአፈፃፀም ደረጃ የሚታዩ ውስንነቶች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ የተለያዩ የማሻሻያ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ቢፒአር፣ ቢኤስሲ፣ ካይዘንና የስራ ልምድና የትምህርት ዝግጅትን እንዲሁም አፈፃፀምን ማዕከል ያደረገ ምደባ (JAG) የመሳሰሉ የአሰራር ሂደቶችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡

የተጠቀሱት አወንታዊ ጉዳዮች ያሉ ቢሆንም፣ ከላይ በመንግስታዊ መዋቅር ተቀጥሮ የሚሰራው ግዙፍ ኃይል የያዘውን መነሻ አቅም በተግባር ሰርቶ መማር እያጎለበቱ የለውጥ ንቅናቄውን ወደ ፊት በማራመድ ረገድ መሰረታዊ ለውጥ የሚጠይቁ የአስተሳሰብ፣ የተግባርና የአደረጃጀት ግንባታ ስራዎች ይጠይቃሉ፡፡ ለተለያዩ ፀረ-ህዝብና አልቧልታ አስተሳሰቦች የተጋለጡ ናቸው፡፡ ይህን የሚቀይርና የራሱ የተሟላ አቋም የሚያስይዝ የአስተሳሰብ ግንባታ አልተካሄደም፡፡ ሙያዊ አገልግሎት መስጠት የክብሩና የእርካታው ምንጭ ከሚሆንበት ደረጃ ላይ አልደረሰም፡፡ ህዝባዊ አገልግሎት በመስጠት ርካታን የመጎናፀፍ ዝግጁነትና ቁርጠኝነት በሚፈለገው ደረጃ ላይ አልደረሰም፡፡ ችግሮችን ወደ ውስጥ ከመመልከት ይልቅ ውጫዊ ያደርጋሉ፡፡ ብዙ የለውጥ ፕሮግራሞች የተጀማመሩ ቢሆንም ተሟልተው እየተፈፀሙ አይደለም፡፡ ከፕሮግራሙ ከአፈፃፀም ድክመት የተነሳ የማጣጣልና የለውጥ አቅም አድርጎ ያለመመልከት ሁኔታ ይታያል፡፡ ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት ከዚህ የሚነሳ ዴሞክራሲያዊ አንድነት አስተሳሰብና አቅጣጫ አልያዘም፡፡ ህዝባዊ አንድነትን የሚጎዱ የትምክህት፣ የጠባብነት፣ የጎጠኝነት እንዲሁም የኃይማኖት አክራሪነትና መሰል ኋላቀር ዝንባሌዎች ቀላል ባልሆነ ደረጃ ይስተዋሉባቸዋል፡፡ በየተቋሙም ሆነ በየደረጃው ለስራ በሚሆን ደረጃ የተደራጁ ቢሆንም፣ አደረጃጀቱ ጠንካራነቱና ውጤታማነቱ እየተገመገመ እየተመራ አይሄድም፡፡

በአጠቃላይ በመዋቅሩ የሚገኙትንና በትምህርት ተቋማት የሚገኙ ሰራተኛንና አመራሮችን የአስተሳሰብና የአደረጃጀት አቅም በአጫጭር የስራ ላይ ስልጠናዎች በዋነኛነት ደግሞ በሰርቶ መማር ዕለታዊ የግምገማ ስርዓት እየገነቡ ማሰማራት በትኩረት መሰራት ያለበት ተግባር ነው፡፡

### 1.6 የህዝብ ሁኔታ

የህዝብን ሁኔታ በመተንተን የ2010 እቅድ መነሻ በሚሆንበት ደረጃ ማዘጋጀት እንደሚጠይቅ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም ግምገማችን የገጠርና የከተማ የህዝብ አደረጃጀቶችንና የጠቅላላ ህዝቡን ሁኔታ ለዓመታዊ እቅድ መነሻ በሚሆን አግባብ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### 1.6.1 የከተማው ህብረተሰብ ሁኔታ

የከተማው ህብረተሰብ ሁኔታ ሲባል፤ በንግድና አገልግሎት መስክ የተሰማራውን፣ ተቆጥሮ የሚሰራውንና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች የሚወክለውን ጥንካሬና ውስንነት መነሻ በማድረግ የሚካሄድ የሁኔታ ግምገማ ነው፡፡

ይህ የህብረተሰብ ክፍል ቁጥሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ሲሆን፣ በቅርብ የተቋቋሙትን ከተሞች ጨምሮ ሲታሰብ እስከ 18 በመቶ የሚደርሰውን የክልሉን ህዝብ የሚሸፍን ነው፡፡

የከተማው ህብረተሰብ በብዙ አደረጃጀቶች ታቅፎ ባይንቀሳቀስና ጠንካራ አደረጃጀቶች ባይኖሩትም፤ የሴቶችና ወጣቶች ማህበራት፣ የንግድና ሸማቾች ማኅበራት፣ የኪነጥበብና የሙያ እንዲሁም ህብረት ስራ ማህበራት ቁጥራቸው ብዙ ያልሆኑ

አባላትን ይዘው የሚንቀሳቀሱ አደረጃጀቶች አሏቸው። የሚበዛው ህብረተሰብ በአደረጃጀት ውስጥ ያልታቀፈ፣ ሁሉም አይነት አስተሳሰቦችና ዝንባሌዎች በግራና በቀኝ እየተነሱ በአብዛኛው ግራ ሲያጋቡት የሚኖር ነው።

የከተማው ህብረተሰብ በተሀድሶ መድረኮች በውይይት ተሳትፏል። በተደራሽነትና በጥራት በኩል የነበሩ ችግሮች ቢኖርም፣ በመድረኮቹ መሳተፍ የቻለው መሪዎቹን የመገምገም እድል ያገኘ ከመሆኑም በላይ፣ ከህዝቡ የሚጠበቀውን እንዲመለከት አስችሎታል። ህዝቡ ሰላሙ እንዲናጋ የማይፈልግ ከመሆኑም በላይ፣ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ተግባራቱ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በጽናት ድጋፉን እየገለፀ ይገኛል። የተደራጀ አመራር ማግኘት በቻለበት አካባቢ፣ በልዩ ልዩ የከተማ ልማትና አገልግሎት ስራዎች የበኩሉን ተሳትፎ እያደረገ ያለ ህዝብ ነው። የተበላሹ አሰራሮችን የሚጠላና በአካባቢውና በአገሩ ጉዳይ ላይ ንቁ ተሳትፎ እያካሄደ ያለ ህዝብ መሆኑ፣ ለተጀመረው የለውጥ ንቅናቄ ለ2010 እቅድ አፈፃፀም መልካም ሁኔታ ተደርጎ ይታያል።

የተጠቀሱት አወንታዊ ሁኔታዎች ያሉም ቢሆን፣ ከተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን አውታሮች በሚሰማው እንዲሁም በቤተሰቡና በጎረቤቱ በሚገለፁ ትክክለኛ በሆኑና ትክክለኛ ባልሆኑ መረጃዎች ግራ መጋባት የሚስተዋልበት ነው። ጥርት ያለና ከሚያደናግር ሁኔታ የፀዳ የመረጃ ምንጭና የተደላደለ አቋም የማስያዝ ሁኔታ አልተፈጠረለትም። የጥፋት ኃይሎችን አስተሳሰብ የመሸከም አዝማሚያዎች ቀላል ባልሆነ ደረጃ ይታያል። ባህርዳር ከተማ የተሀድሶ ንቅናቄ ውሕደቱ የሚፈለገውን የህዝብ ተሳትፎና የአመራር ማስተካከል ያካሄደ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ ጎላ ያለ የጥፋት አስተሳሰብና ተግባራት ይስተዋላል። ከአቤቱታ እቅድ ጋር አያይዞ ግምገማ በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የለውጥ ንቅናቄውን ማፋጠን ይጠይቃል። የምርታማነት ማሻሻልና የገቢ ምንጭ እድገት በሚፈለገው ደረጃ እየመጣ ባለመሆኑ፣ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያለው አብዛኛው ህዝብ በኑሮ ውድነትና በመጠለያ እጦት በችግር ላይ የሚገኝ ህብረተሰብ ነው። ይህ ሁኔታ በተረጋጋ የለውጥ ንቅናቄ ውስጥ እንዳይገባ ተጽዕኖ አድርሶበታል። በልማትና በመልካም አስተዳደር የለውጥ ንቅናቄ ውስጥ ሚናውን አሳንሶ፣ ከመንግስትና ከሌሎች አካላት ጠባቂነቱ ጎልቶ ይታያል። ጠንካራ የብዙኃንና የሙያ ማህበራት ካለመፈጠራቸው የተነሳ፣ ፍላጎቶቹን አሰባስበው ዘላቂ ለውጥ የሚያመጡና ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫን የሚያስይዙ አደረጃጀቶችም የሉትም። ያሉትም የተደራሽነትና የብቃት ከፍተኛ ችግሮች ናቸው።

በአጠቃላይ የከተማውን ህዝብ የለውጥ ኃይል አድርጎ ህዝቡ የሚፈልገውን ሰላም፣ልማት፣ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ለማፋጠን ጠንካራ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ግንባታ ስራ ይጠይቃል። ከልማት ኃይሎችና ካሉት ትንንሽ አደረጃጀቶች ጋርም ቢሆን በጋራ በመስራት፣ የህዝቡን የለውጥ ንቅናቄ ማፋጠን ይገባል።

### 1.6.2 የአርሶ አደሩ ሁኔታ

በአማራ ክልል፤አርሶ አደሩ የሚገኝበትን ሁኔታ በምንገመግምበት ወቅት፣ ከክልሉ ኑዋሪ ህዝብ መካከል ከ82-83 በመቶ ስለሚሆነው ህዝብ እንደሆነ ግልጽ ነው።

አርሶ አደሩ በተቀሰቀሰው የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄ ውስጥ ያለፈና የራሱን ገንቢ አስተዋጽኦ ያበረከተ ነው። መድረኮቹ በተከፈቱበት ወቅት ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በተሻለ ጥቅሞቹን የሚያስጠብቁ ሚዛናዊ አቋሞች ይዞ ታግሏል። ምንም እንኳ በወሬና በአሉባልታ የመደናገርና በተወሰነ ደረጃ የራሱን ሚና ቀድሞ ያለማየት ችግሮች የነበሩበት ቢሆንም፣ መድረኮቹ የራሱን ችግሮች እየተመለከተ እንዲሄድ በተመሩበት ሁኔታ የራሱን ጥንካሬዎችና ድክመቶች ገምግሞ የወልና የግል ልማታዊ ሂደቱን የሚያፋጥኑ ንቅናቄዎችን በመካሄድ ላይ ይገኛል። ህገ-ወጥ ተግባራትን በየወቅቱና በተረዳው ደረጃ በመታገል ላይ

ነው። በግልና በውል ልማቶች ላይ ተሳትፎው እያደገ መጥቷል። የተሻሻሉ፣ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም ረገድ፣ ከታካችነት ጋር የተያያዙ ችግሮች ያሉም ቢሆን ወሳኙ መገለጫ የለውጥ አስተሳሰቦችንና ተግባራትን በተረዳበት መጠን ለመቀበልና ለመተግበር ዝግጁነቱ እድገት ይታይበታል። የልማት ቡድንንና የአንድ ለአምስት አደረጃጀቶችን ተጠቅሞ፣ ውጤት በማምጣት ረገድ የወቅታዊነት ወይም በመደበኛነት የተደራጀ እንቅስቃሴ የማካሄድ ጉድለቶች ያሉም ቢሆን፣ የተደራጀ የለውጥ ንቅናቄ የማካሄድ ልምድ እየተሻሻለ መጥቷል።

የተጠቀሱት ጥንካሬዎች ያሉ ቢሆንም፣ የልጆቹና የአካባቢው ልጆች በወቅቱና በጠበቀው አኳኋን ወደ ስራ አለመግባታቸው እንዲሁም ሌሎች ተጨባጭ ችግሮችና አሉባልታዎች የሚያሳድሩበት ተጽዕኖ የሚደርስበት ግራ መጋባት ቀላል አይደለም። አርሶ አደሩ ከራሱ ምርጥ ተሞክሮ፣ በአካባቢው ከሚገኙ ስኬታማ ልምዶች እንዲሁም ከባለሙያ ምክር ተነስቶ፣ በትልቁ አቅዶ በትልቁ በመፈፀም ትርጉም ያለው ህይወታዊ ለውጥ በማምጣት ረገድ መሰረታዊ የእይታም ሆነ የአልችልም ባይነት ሁኔታው በሚፈለገው ደረጃ አልተሰበረም። የህገ-ወጥነትን፣ ሙስናንና የፀረ-ሰላም እንቅስቀሴን በታዩበት ደረጃ፣ በወቅቱና በጽናት መታገል ላይ አሁንም ችግሮች አሉ። የልማት ቡድንንም ሆነ የአንድ ለአምስት አደረጃጀቶችን የልማት አቅም አድርጎ በመገንዘብ ረገድ አሁንም ቀጣይ በተግባር የተደገፈ ግንባታ ይሻል።

በጥቅሉ መሰረታዊ ህይወታዊ ለውጥ የሚያመጣና በትልቁ አቅዶ በትልቁ ለመፈፀም የሚያስችል የአስተሳሰብ፣ የተግባርና የአደረጃጀት ንቅናቄን ማጠናከር ጉዳይ በትኩረት ሊሰራበት ይገባል።

### 1.7 የህዝብ አደረጃጀቶች ሁኔታ

### ሀ) የሴቶች አደረጃጀትና የልማት ሁኔታ

የጥንካሬ ደረጃው ብዙ የሚቀር ቢሆንም እስከ ግማሽ ሚሊዮን የሚደርሱ የሴቶች ማህበር አባላት አሉ። ማህበሩ በገጠርና በከተሞች እንዲሁም የተለያየ የትምህርት ደረጃ ያላቸውና የአርሶ አደር ሴቶችን ያቀፈ ነው። ቁጥራቸው አነስተኛም ቢሆን የነጋዴ ሴቶችና ሌሎች የሴቶች አደረጃጀቶችም አሉ።

ሴቶች ከጠቅላላ ህዝቡ ጋር እንዲሁም በአደረጃጀታቸው አማካኝነት በጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄ መድረኮች ተሳትፈዋል። በመድረኮቹ በአፈፃጸም የሚታዩ ችግሮችን አንስተዋል፤ እንዲስተካከል ትግል አካሂደዋል። በራሳቸው ደረጃ የሚታዩ ችግሮችን ለማስተካከልም ጥረት አካሂደዋል። በዓመቱ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራት ላይ በገጠርም ሆነ በከተሞች ተሳትፏቸው ጥሩ ነበር። በገጠር ጤናን ማዕከል ባደረጉት የልማት ቡድን አደረጃጀቶች የተደራጀ እንቅስቃሴ ነበራቸው። ከህገ-ወጥ የመሬት ወረራ ጋር ተያይዞ የሚደርስባቸውን ጥቃት ተደራጅተው ታግለዋል፤ ከገቢያቸው የቁጠባ ንቅናቄም አካሂደዋል።

የተጠቀሱት ተግባራት የነበሩ ቢሆንም፣ በጠቅላላ ህዝቡ ውስጥ የተጠቀሱት የአስተሳሰብ ግራ መገባቶች በሴቶችም የሚታዩ ናቸው። ምንም እንኳ የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ዋነኛ ኃይል ቢሆኑም፣ እንደ ህብረተሰቡ የሚታዩባቸው አሉታዊ ዝንባሌዎች በተለያየ ደረጃ ተስተውለዋል። የማህበር አደረጃጀቶቻቸው በጠንካራ አመራሮችና በአባላት ተሳትፎ ከፍተኛ ችግር የሚታዩባቸው ናቸው። የስራ አደረጃጀቶችም የተጠናከሩ ናቸው ማለት አይቻልም። የማህበራትና የአደረጃጀቶች መሪዎችም ማህበሩንና የአመራር ሚናቸውን ወደ ሌሎች ኃላፊነቶች መሸጋገሪያ እንጂ፣ እንደ ሁነኛ የመታገያ መድረክ

አያዩዋቸውም። በመሆኑም ማህበራቱ ተጠናክረው የለውጥ ኃይል እንዲሆኑ፣ የማህበራቱ ነፃነት ተጠብቆ በጋራ ጉዳዮች ላይ ተመካክሮ መስራት ይጠይቃል።

### ለ) የወጣቶች የተደራጀ ንቅናቄ ሁኔታ

በብአዴን የለውጥ አመራር እርካታ በማጣት፣ በቁጣ ቀድመው የወጡት ወጣቶች የህብረተሰብ ክፍል እንደሆኑ ይታወቃል። ድርጅቱ የጥልቅ ተሀድሶ መጀመሩን በሰማበት ወቅት ተስፋ በማሳደር፣ በአብዛኛው በመድረኮች እየተሳተፈ ችግሮችን ፊት ለፊት አንስቷል። ቁጥራቸው ከጠቅላላ ወጣቱ ቁጥር አንፃር ሲታይ አነስተኛ ቢሆንም፣ በራሳቸው አደረጃጀትም ተወያይተዋል። ወጣቱን ስራ ለማስያዝ በተደረገው እንቅስቃሴ የተሻለ ሙከራ ባካሄዱ አካባቢዎች ተስፋ የማሳደርና የግል ጥረቱንም የማካሄድ ሁኔታ አለ።

የተጠቀሱት መልካም አዝማሚያዎች ያሉ ቢሆንም፣ በመሰረቱ ሊፈቱ የሚገባቸው ችግሮች አሉ። ከሁሉም በፊት ለወጣቶች ኑሮ መሻሻል ወሳኞች ራሳቸው ሆነው ሲያበቃ፣ የቤተሰብና የመንግስት ድጋፍ ደግሞ የየራሳቸው የማይተካ ድርሻ እንዳላቸው በአግባቡ ለይቶ የማስረዳት መሰረታዊ ችግሮች አሉ። ወጣቶችም የራሳቸውን ጥረት አጉልተው ማየት ሲገባቸው፣ ሁሉንም ነገር መንግስት እንዲፈታላቸው የመጠበቅ ሁኔታ አሁንም ሰፊ ነው። የፀረ-ህዝብ ኃይል በተለያየ አግባብ አነሳስቶ መሳሪያ ሊያደርጋቸው እንደሚችል አሟልቶ ያለመገንዘብና በቀላሉ ለጥፋት የመጋለጥ ሁኔታም ይታያል። ለህገ-ወጥ ሰዎች ዝውውርና ለአልባሌ ሁኔታ የመጋለጥ አዝማሚያ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በአደረጃጀት የታቀፉ ወጣቶችም ቁጥራቸው አነስተኛ ከመሆኑም ባሻገር፣ “ማህበሩ የመታገያ መሳሪያ ይሆናል” የሚል እምነት አላሳደሩም። አመራሩም እንዲሁ; የተጠቀሱትን መልካም አዝማሚያዎች አነስተኛም ቢሆኑ እነሱ ላይ በመቆም በዋነኛነት በተግባራዊ ለውጥ ላይ ተመስርቶ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ግንባታ ማካሄድ ይጠይቃል።

### 1.8 የተቃዋሚ ኃይሎች ሁኔታ

በአገራችን ያሉ ተቃዋሚዎች በሁለት ተከፍለው የሚታዩ ናቸው። በአንድ በኩል ህጋዊና ሰላማዊ መንገዱን ተከትለው፣ ህገ-መንግስቱንና ስርዓቱን አክብረው በህጉ መሰረት ተቃውሟቸውን ማቅረብና በዚሁ አማካኝነት ድጋፍ አግኝተው ወደ ስልጣን ለመውጣት የሚንቀሳቀሱ ናቸው። በሁለተኛ ደረጃ የሚታዩት የአገራችን ተቃዋሚ ኃይሎች ህገ-መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይልና በአመጽ በማስወገድ ወደ ስልጣን መውጣት የሚፈልጉ ናቸው።

የሁለቱም አይነት ተቃዋሚዎች ዋነኛ መንጠልጠያና አቅም መፍጠሪያ ግብዓት፣ የልማትና ዴሞክራሲ ኃይሎች እንዲሁም የመንግስት የአፈፃፀም ድክመቶችና ከነዚህ የሚነሱት የህዝብ ቅሬታዎች ናቸው።

### ሀ) ህጋዊና ሰላማዊ የትግል ስልትን የመረጡ ኃይሎች ሁኔታ

የነዚህ ኃይሎች ጥንካሬ ሰላማዊና ህጋዊ የትግል ስልትን መምረጣቸው ነው። እነዚህ ኃይሎች ይህንኑ አቋማቸውን አጠናክረው ከቀጠሉ ፍላጎቱን የሚወክሉለት ተከታይ ህዝብ ያላቸው ከመኖሩም በላይ፣ በአገሪቱ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የበኩላቸውን ድርሻ ሊጫወቱ የሚችሉ ናቸው። በ2010 በሚካሄደው የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ሲሳተፉና የድርሻቸውን ሊያበረክቱ ይችላሉ።

የተጠቀሰው ጥንካሬ ያለ ቢሆንም፣ ተቃዋሚዎቹ ጥርት ያለና የማይናወጥ ዴሞክራሲያዊ የትግል ስርዓት ስለሚጎድላቸው የአመጽ ኃይሎቹ ከሩቅ ሆነው እንደፈለጉ የሚያሾሯቸውና ሊያሰማሯቸው የሚችሉ መሆኑ ዋነኛው ድክመታቸው ነው።

ጥንካሬያቸውን መሰረት በማድረግ ከህጋዊና ሰላማዊ ተቃዋሚዎች ጋር በሚያግባቡን ጉዳዮች ላይ የብአዴን መዋቅር የሚመለከታቸው አካላት በመሆን በጋራ መስራትን ይጠይቃል።

### ለ) የአመጽ ኃይሎች ሁኔታ

የአመጽ ኃይሎቹ ህዝብ በመንግስት ላይ ቅሬታ በሚያስነሳበት ነባራዊ ሁኔታ ላይ በመመስረትና ይህንኑ እየተመገቡ፣ የበለጠ አቅም ያላቸው መስለው የሚታዩ የአመጽ ኃይሎች ናቸው፡፡ እነዚህ ኃይሎች፤"በፌደራል ስርዓቱ አማራን አልተጠቀመም። ስርዓቱ አድሏዊ ነው። የትግራይ ብሔር የላቀ ተጠቃሚ ሆኗል። ይህ የሆነው ደግሞ ብአዴን በአግባቡ ስለማይታገል ነው።" የሚል መልዕክት ቀርፀው በሁሉም የህዝብ ግንኙነት መስኮች ሰፊ ዘመቻ ከፍተው እየሰሩ ሲሆን ሂደታቸውም ሆነ መድረሻቸው በአመፅ ስርዓቱን መቀየር ነው። በመሆኑም መነሻቸው ጥፋት ስለሆነ፣ ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ምንም አይነት አስተዋፅኦ የሌላቸው የጥፋት ኃይሎች ናቸው። የጥፋት ኃይሎቹን ማዳከምና መሰረትም ማሳጣት የሚቻለው፣ የልማትና ዴሞክራሲ ኃይሎች ከአስተሳሰብና ከአፈፃፀም ጋር የተያያዙ ድክመታቸውን አስተካክለው የህዝቡን ችግር ሲፈቱ ነው። ከዚህ አልፈው የሚመጡ ተናጠል የጥፋት ሙከራዎች፣ህዝቡን በማሳተፍ አስተዳደራዊና ህጋዊ ርምጃዎችን በመውሰድ ሊስተካከሉ የሚችሉ ይሆናሉ።

### 1.9 የዓመቱን የልማትና የዴሞክራሲ ተግባራት በተደራጀ የልማት ሰራዊት የመፈፀም አስፈላጊነት

2010 ዓ.ም ውጤታማ የልማትና የዴሞክራሲ ተግባራት የላቀ አፈፃፀም የሚታይባቸው እንዲሆኑ ይጠበቃል። ይህ ዓመት በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሦስተኛ ዓመት የዕቅድ ግቦች የሚከናወኑበት ብቻ ሳይሆን፣ ባለፉት ሁለት ዓመታት ሳይከናወኑ የቀሩ የዕቅድ ግቦችም ተሸጋግረው በተለጠጠ የዕቅድ አፈፃፀም ሁኔታ የሚከናወኑበት እንዲሆን ይጠበቃል።

ከግብርና ልማት አኳያ በሰብል ልማት፣ በተፈጥሮ ሀብት ልማትና በእንስሳት ሀብት ልማት ከፍተኛ ምርታማነትን ለማስመዝገብ በጋና ክረምት ከፍተኛ ርብርብ የሚካሔድበት ይሆናል። በኢንዱስትሪ ልማት መስክ የጥቃቅንና አነስተኛ ልማት እንዲሁም፣ የመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ምርታማነት በሚሻሻልበትና በጅምር ደረጃ ያሉ ግንባታቸው በሚፋጠንበት ሁኔታ ላይ የተደራጀ ንቅናቄ ይካሔዳል። በትምህርትና በጤና ልማት የጥራትና የተደራሽነት ስራዎች ተጠናክረው የሚከናወኑበት ዓመት ይሆናል። በመልካም አስተዳደር መስክ በዓመቱ መከናወን ያለባቸው ተቆጥረው ተይዘው፣ ከህዝቡ ጋር በመወያየት ሊፈቱ እንደሚገባ ስምምነት የተያዘባቸው የሚከናወኑበት ይሆናል።

የወረዳና የቀበሌ እንዲሁም የማሟያ ምርጫዎች ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና በህዝባዊ ተሳትፎ አመኔታን በተረጋገጠበት አግባብ ይካሔዳሉ። የተጠቀሱትን ተግባራት በጥራት ለማከናወንና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን ቀምሮና እነዚህን ምርጥ ተሞክሮዎችም መነሻ መሠረት (bench mark) በማድረግ በከፍተኛ ደረጃ ይጠይቃል። ከሁሉም በላይ ተግባራዊ የአፈፃፀም ለውጥ የሚታይበት ዓመት እንዲሆን ብርቱ ጥረት ይጠይቃል።

የተጠቀሱትን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ተግባራት ለማከናወን፣ የልማት ኃይሎች የተደራጀ ንቅናቄ ወሳኝነት አለው። የተደራጀ የልማት ሰራዊቱ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው፣ የብአዴን አመራሮችና አባላት ግንባር ቀደም ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ይዘው የአመራር ሚናቸውን ሲያረጋግጡ ነው። የጥፋትና የአመፅ እንቅስቃሴዎች ተወግደው ሰላማዊ ሁኔታ ሲሰፍን ብቻ ነው። በመሆኑም የሁሉንም አቅሞች ተግባርንና ተግባርን ማዕከል ባደረገ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ግንባታ

ላይ መረባረብ ይጠይቃል። ከዚህ የለውጥ ንቅናቄ በሚያደናቅፉን ማንኛውም አይነት እንቅስቃሴዎች ላይ ጠንካራ ትግልና ማስተካከያ ሊካሔድ የሚገባ ይሆናል።

## 1.10 የብአዴን 12ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ፤የስትራቴጅክ እቅድ ዝግጅት እና የአካባቢ ምርጫ የሚካሄድ መሆኑን እንደ እቅድ መነሻ

### 1 የድርጅታዊ ጉባኤ ተግባራት፣

የካቲት 2010 ዓ.ም የብአዴን 12ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ይካሄዳል። ጉባኤው ከ11ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ በኃላ ባለፉት ሁለት ተኩል አመታት የተከናወኑ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ተግባራት እንዲሁም የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን አፈፃፀምን በመገምገም ትምህርት የሚቀስምበት ይሆናል። 12ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ያለፉትን አመታት አፈፃፀም ከመገምገምና ትምህርት ከመቅሰም ባሻገር የተጀመረው በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄ ተጠናክሮ በሚቀጥልበት ሁኔታ በመምከር ዝርዝር አቅጣጫዎች የሚወሰንበት ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ጉባኤው አፈፃፀም ግምገማ ሆነ ከቀጣይ የትኩረት ጉዳዮች አንፃር ሒደቱ በብቃት ተመርቶ ወሳኝ አቅጣጫዎችን ሊያስቀምጥ የሚችለው ጠንካራ ቅድመ ዝግጅትና ከቅድመ ዝግጅቱ መከናወን የሚገባቸው ተግባራት ሲከናወኑ ብቻ ነው። የጉባኤው ቅድመ ዝግጅት የአመራሩንና የአባላትን አስተሳሰብ አድማስና በተግባር ውጤታማነትን ማረጋገጥ በሚችልበት አግባብ መከናወን ይኖርበታል። የጉባኤ ዝግጅትም ሆነ የጉባኤው ሂደት ህዝቡ በንቃት የሚሳተፉበትና ኃሳቦቹ የጉባኤ ሪፖርት አካል ሆኖ ተግባራዊ የሚሆንበት ጥብቅ አሰራር ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቃል። የጉባኤ ዝግጅቱም ሆነ ጉባኤው የተሳካ እንዲሆን የድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ በሚያስቀምጠው አቅጣጫ መሰረት ራሱን የቻለ የማስፈፀሚያ እቅድና አዘጋጅ ኮሚቴ ይዋቀራል። አዘጋጅ ኮሚቴው ማዕከላዊ ኮሚቴ የሚያስቀምጠውን አቅጣጫ መሰረት በማድረግ የረቂቅ ሪፖርትና ሌሎች አጀንዳዎችን ረቂቅ ሰነዶችን እያዘጋጀ በየ ደረጃው የሚመክርበት ይሆናል።

### 2 የብአዴን የመካከለኛ ጊዜ እቅድ ማዘጋጀት ስራ፣

ብአዴን-ኢህአዴግ የነደፉትን የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር በብቃትና በውጤታማነት ከመፈፀም አንፃር ፓርቲና የፓርቲ አደረጃጀት የአፈፃፀሙ ሽከርካሪት ማዕከል እደሆነ ግልፅ ነው። የክልሎችም ሆነ የአገራችን የለውጥ አሽከርካሪነት ማዕከል የሆነው ድርጅታችን ከአመቱ እቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም በሻገር በመካከለኛ ጊዜ የአመራርና የአባላት ግንባታ እቅድ አዘጋጅቶ መንቀሳቀስ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ተበራክተዋል። በአጠቃላይ የአመራር መተካካት ሂደት ውስጥ በቆየውና አዲስ አመራር በሚረከበው ሀይል መካከል መደበኛ ሂደቱን ጠብቆ የለውጥ አመራር ለማረጋገጥ ቢያንስ ቢያንስ የመካከለኛ ጊዜ እቅድ ነድፎ መንቀሳቀስ ይጠይቃል። የህዳሴ ጉዞ ዋነኛ የአመራር ቋት በድርጅት የሚታቀፍ ግንባር ቀደሞች ደግሞ በተግባር ተለክተው የሚያልፉትን ሊመለመሉ የሚችሉትን በተደራጀ የለውጥ ንቅናቄ ውስጥ ግንባር ቀደም ሆነው ከሚወጡ ምሁራን ፣ላብአደሮች፣አንቀሳቃሾችና አርሶ አደሮች ነው። ይህ ተግባር በታቀደ መልኩ የአመራርና የአባላትን የምልመላና ግንባታ ተግባር የሚጠይቅ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም እንደ አንድ እቅድ መነሻ ተወስዷል።

### 3 የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ምርጫ ዝግጅት

በአገራችን ህገ መንግስትና የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት 2010 ዓ.ም የወረዳና የቀበሌ ምርጫ ይካሄዳል። ብአዴን አንደ አንድ ተፎካካሪ ፓርቲ ብቻ ሳይሆን እንደ አንድ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ታጋይና መሪ፤

ምርጫው ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሁም ህዝባዊ አመኔታ የታፈረ ብቻ ሳይሆን ብቁ እጩ ተወዳዳሪዎችን አቅርቦ በሚወዳደርበት ሁኔታ ጠንካራ ዝግጅት ይጠይቃል።

የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ምርጫ ራሱን የቻለ ዝርዝር እቅድ የሚዘጋጅለት፤ በዚህ መነሻ ሁኔታ መታለፍ የሌለባቸው ጉዳዮች ህዝባዊ አገልግሎት ለመስጠት የተዘጋጁና ህዝብ የመምራት ብቃት ያላቸውን እንዲሁም የታዳጊ ህብረተሰባዊ ተሳትፎአቸውን የጠበቁ እጩዎችም የማዘጋጀት ጉዳይ በትኩረት ይሰራል። ህዝቡ ከመራጮች ምዝገባ አንስቶ እጩዎችን በመተቸትና ጠቃሚ ኃሳቦችን በማመንጨትም ሆነ በማስተካከል ሁኔታ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖረው የላቀ ትኩረት ይሰጣል።

## 1.11 ከሁኔታ ትንተናው የሚወሰዱ ድምዳሜዎችና አንደምታዎች

### ሀ) የሚወሰዱ ድምዳሜዎች፣

በተካሄደው የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄ አመራሩ በወሳኝነት ከጎራ መደባለቅ ወጥቶ ለመስመሩ ዘብ የሚቆም ሀይል ተፈጥሯል። በድርጅቱና በህዝቡ፣በአመራሩና በአባላት መካከል ተፈጥሮ የነበረው ጥርጣሬና አለመተማመን ቀጣይ ስራ የሚጠይቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በጅምር ደረጃ የሚታይ መተማመን ተፈጥሯል። ከስልጣን አተያይና አጠቃቀም ጋር ተያይዞ በአመራሩ ዘንድ የነበሩ ችግሮች በተከታታይ በተካሄዱት ትግሎች የመቀነስ አዝማሚያ አሳይቷል። ዴሞክራሲያዊ የአመራር ሁኔታው መድረስ በሚገባው ደረጃ ባይደርስም በዴሞክራሲያዊ አንድነቱ እየተሻሻለ መጥቷል። የትምክህት አስተሳሰብና ተግባር የሚያስከትለውን አደጋ የተረዱና ለዴሞክራሲያዊ አንድነት የሚታገሉ ሀይሎች እየተበራከቱ መጥተዋል። የህዝብን አንገብጋቢ ችግሮች ቀጣይ ይዞ መፍታት ጅምር እንቅስቃሴ ታይተዋል። በጅመሩ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ቀጣይ ሊዳብር የሚችል ተግባራዊ አቅሞች ተፈጥረዋል። እነዚህ የለውጥ እንቅስቃሴዎች በአብዛኛው ህብረተሰብ ዘንድ የለውጥ ተስፋ አሳድረዋል።

የተጠቀሱት አወንታዊ ድምዳሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በአመራሩ፣በአባላትና በህብረተሰቡ ውስጥ የተሟላ ድምዳሜ ያልተያዘባቸው ቀጣይ ትግል የሚጠይቁ ዝንባሌዎች በርካታ ናቸው። በአመራሩ ውስጥ ከስልጣን አተያይና አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የተለዩ ችግሮች በጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄው ትግል የተካሄደባቸው ቢሆንም ችግሮቹ ከስር መሰረታቸው አልተነቀለም በፌደራል ስርዓቱ "የአማራ ህዝብ ፍትሀዊ ተጠቃሚነት አልተረጋገጠም የዚህ መሰረቱ ስርአቱ አድሎ ያለበት መሆኑና ብአዴን ይህን ብቃት የሚታገል አለመሆኑ ነው።" የሚለው አመለካከት በተለያየ ደረጃ ትግል ተካሄደበት ስፋቱ የጠበበ ቢሆንም ከስር መሰረቱ ተነቅሎ አልተወገደም። ችግሮቹን ውጫዊ ከማድረግ ወጥቶ የለውጥ ማዕከላዊ ኃይል ራሱ መሆኑን ተገንዝቦ መሔድ ላይ በተለያየ ደረጃ የሚገለፁ ችግሮችን ውጫዊ የማድረግ ዝንባሌዎች ቀጣይ ስራው ስራ ይጠይቃሉ። በዚህ ረገድ ከሙህራንና ከንግዱ ማህበረሰብ የጋር ተቀራርቦ በመሰረታዊ ጉዳዮች ዙሪያ በቂ መግባባት አልተደረሰም። ፀረ-ዴሞክራሲና መርሃ አልባ ጉድንት ለመታጋል ጥረቶች የተካሄደ ቢሆንም አሁንም መሰረታዊ ችግሮች ሆነው የቀጠሉና አባላት የሚማሩባቸው ናቸው። የፀረ-ሙስና ትግሉም ሆነ ጠቅላላ የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ ተግባር አሁንም ትኩረት የሚሹ ናቸው። ህብረተሰቡ ለሁለንተናዊ ለውጥ መነሳሳቱ አወንታዊ ቢሆንም የራሱን ወሳኝ ድርሻ በቅጡ ተረድቶ ከጠባቂነትና ሰበብ ፋለጋ ወጥቶ የወሳኝ የለውጥ ሀይል በሚሆንበት ደረጃ አልደረሰም። ከዚህም በላይ የቆየ የልማትና መልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ በአጥጋቢ ሁኔታ ባልተፈቱበት እንዲሁም የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄው አዳዲስ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችንና ፍላጎቶችን ይዞ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ህብረተሰቡ ከመጡት መሻሻሎች በላይ

መሰረታዊ ለውጥ ይጠብቃል። በድምሩ አወንታዊና አሉታዊ አዝማሚያዎቹ ተደምረው ሲታዩ የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄ ድርጅቱንም ሆነ ጠቅላላ ስርዓቱ ከጥፋት የታደገው ቢሆንም በጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄ የተለያዩ ችግሮች ከመሰረቱ ተፈትተው የለውጥ ንቅናቄው የማይቀለበስበት ደረጃ አልደረሰም።

### ለ, የድምዳሜዎቹ አንደምታዎች

አሁንም የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄን አጠናክሮ መቀጠል ይጠይቃል። የተሀድሶ ንቅናቄው ለይቶ ያስቀመጣቸው የአስተሳሰብና የአፈፃፀም ችግሮቻችን እየተፈቱ ውጤታማነት በሚረጋገጥበት ሁኔታ አጠናክሮ መቀጠል ይጠይቃል። በ2009 ዓ.ም የተሰሩ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ለውጦች ሳይባክኑ፤በአግባቡና በውጤታማነት መጠቀም። የተፈጠረውን አቅም አቅበን የተሟላ የእቅድ ዝግጅትና የተግባቦት ስራ በማካሄድ የላቀ አፈፃፀም ማረጋገጥ የግድ ይላል።

በየደረጃውና በተቋማት ኮር አመራር መገንባትና በዚህ አመራር አማካኝነት የተደራጀ የለውጥ ሰራዊት መገንባትና ተግባራዊ ለውጥ ማረጋገጥ የግድ ይላል። የአመራር መዋቅሩን ከማጠናከር ባልተናነሰ የመሰረታዊ ድርጅትና ህዋስ አደረጃጀቶች ማጠናከር በውጡ ትልልቅና መሰረታዊ፤ፈጣንና ህብረተሰቡን የመቀየር አቅም ያለው መሆን ይኖርበታል። ከለውጥ ንቅናቄው ህብረተሰቡ የላቀ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ከጠባቂነትና ችግሮችን ውጫዊ ከማድረግ ታላቅቆ የተገኙትን እቅዶች መነሻ በማድረግ የግልና የወል ህይወቱን የሚቀይር  እቅድ አዘጋጅቶ ወሳኝ ርብርብ ሲያካሄድ መሆኑን ታሳቢ ያደረገ የአስተሳሰብና የተግባር ዝግጁነትና ውጤታማነት ማረጋገጥ ይጠይቃል። በተግባር  ውጤታማነት ተረጋግጦ ህብረተሰቡ የለውጥ ምህዋር ውስጥ ካልገባ ሰላማዊ ሁኔታን ማረጋገጥ አደጋች ይሆናል። በመሆኑም ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ወሳኝ ርብርብ መካሄድ አለበት። ከዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባታ ጋር ተያይዞ ለሚታዩ የአስተሳሰብ ችግሮች የዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት፤በዚሁ አማካኝነት አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ግንባታ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ መደበኛና ወቅታዊ ስራዎች ይጠይቃሉ። በተግባር ውጤታማነት ከማረጋገጥ አኳያ ሞዴል አፈፃፀሞችን፤ምርጥ ፈፃሚዎችን ተሞክሮ በመቀመርና ማስፋት የግድ ይላል። ምርጥ ተሞክሮና ሞዴሎችን ስራ ማስፋፋት በአባላት ግንባር ተነቃናቂነት የሚፈፀም ሊሆን ይገባል። የድርጅትና የመንግስት መዋቅር ተግባራዊ ለውጥ መሬት የሚነካው በታችኞቹ አደረጃጀቶች በመሆኑ በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ ተመስርቶ የመሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ እንዲሁም የልማት ቡድንና የአንድ ለአምስት አደረጃጀቶችን በቀጣይነት ማጠናከርና ማብቃት ይጠበቃል። የልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ተግባር በውጤታማነት ሊከናወኑ የሚችሉ የጥፋት አስተሳሰቦችና ተግባራት ሲደፍቁ እንደሆነ ግልፅ ነው። የጥፋት መከራዎችንና የአመፅ ቅስቀሳዎችን ማጋለጥና ህዝቡ በተደራጀ አግባብ መታገል በሚችልበት ሁኔታ ማዘጋጀት ይጠይቃል።

## ክፍል ሁለት

### የ2010 የፖለቲካና የድርጅት ስራዎች ዓላማዎች፣ ግቦችና ተግባራት አፈፃፀም

#### 1. የእቅድ ዓላማዎች

የተሀድሶ ንቅናቄውን አጠናክሮ መቀጠል። በተግባር ለውጥ የሚያመጣና ውጤታማ የድርጅት አቅም መገንባት፣ ለድርጅቱ ዓላማና ተልዕኮ የሚዋደቅ ኮር የአመራሮችና የአባላት መዋቅርን መገንባት፣ ብሎም የሲቪል ሰርቪስ መዋቅሩንና የህዝብ

አደረጃጀቶችን ማጠናከር። በተደራጀ የልማት ሰራዊት አማካኝነትም የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱን መፈፀምና የህዝቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ።

**2 ቁልፍ ተግባር**

ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብንና ተግባርን ማዕከል ያደረገ ውጤታማ የልማት ሰራዊት መገንባት። የቁልፍ ተግባሩ ዋነኛ ገጽታ የድርጅት መዋቅሩን፣ በዓላማው ላይ እምነት ያሳደረ፣ በመምራት አቅሙ በተግባሩ ውጤታማ የሆነ፣ ግንባር ቀደም እንዲሁም ድርጅቱንና ስርዓቱን ከጥቃት የሚከላከል ኃይል እንዲሆን በሚያስችል ደረጃ መገንባት።

### 3. የእቅዱ ግቦችና ተግባራት

**ግብ 1 የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት የአመራር መዋቅር ኮር የለውጥና የውጤታማነት ማዕከል ይሆናል።**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

**ሀ/ የተመደበበትን ተልዕኮ በብቃትና በውጤታማነት መምራትና ኮር የለውጥ አስተሳሰብ ማዕከል መገንባት።**

- ✓ አመራሩ ጽ/ቤቱ ውስጥ ቆይቶ የተመደበበትን ተልዕኮ ለመወጣት ዝግጁነቱና ተነሳሽነቱ ዝቅተኛና ከራሱ ተልዕኮ ጋር ብቻ ተጣብቆ ከመፈፀም ይልቅ፣ ወደ ሌሎች ተቋማት የማማተር ሁኔታ እንደሚታይበት በሁኔታ ግምገማው ተረጋግጧል። አመራሩ የተመደበበት ኃላፊነት ቁልፍ የመታገያና የለውጥ ማራመጃ ማዕከል መሆኑን ተገንዝቦና ኮር ሆኖ ስራውን በፍቅርና በውጤታማነት መስራት በሚችልበት የአስተሳሰብና የዝግጁነት ደረጃ ላይ በማድረስ ተጨባጭ ለውጥ ማረጋገጥ።
- ✓ በ2009 ዓ.ም እቅድ አፈፃፀም አመራር በመስጠት፣ የድርጅትን መዋቅር መርቶ ውጤታማ በመሆን በኩል በነበሩ ጥንካሬዎችና ድክመቶች ላይ ተመስርቶ መነሳሳትንና ቁርጠኝነትን ማሳደግ።
- ✓ መዋቅሩ የርዕዮተ አለማዊና ፖለቲካዊ እንዲሁም የሰው ኃይል ምልመላና ግንባታ ማዕከል መሆኑን አምኖ፣ በ2010 ዓ.ም የልማትና የመልካም አስተዳደር እቅድ አፈፃፀምና በልሳናት አማካኝነት የግንባታ ሥራ ማካሄድና ውጤታማነቱን ማሳደግ። የስራ አመራር ማሰልጠኛ ማዕከልን በማጠናከርና በጋራ በመስራት የስልጠና ክፍተቶችን እየለዩ ቀጣይ ስልጠና ማጠናከር።
- ✓ የ2010 ዓመት የጽ/ቤቱ አመራር ተግባርን ማዕከል ያደረገ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ግንባታ ማዕከል ሆኖ በሚሰራበት ሁኔታ ይገነባል።
- ✓ የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄው ለይቶ ያስቀመጣቸው ከስልጣን አተያይና አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ችግሮች፣ የአስተሳሰብ ግልጽነት መጓደል፣ የኪራይ ሰብሳቢነት፣ የፀረ-ዴሞክራሲና የአድርባይነት፣ዴሞክራሲያዊ አንድነትን የሚገፉ የራስን ስራ ሳይሰሩ አሻግሮ የማማረር፣ ህዝብን የሚጠቅም ስራ ሳይሰሩ በንግግር የህዝብ ጠበቃ መስሎ የመታየትና መሰል የተዛቡ አስተሳሰቦችን በግንባር ቀደምነት እንዲታገል፣ የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የአስተሳሰብ ልዕልና የማስረጽና በቀጣይነት የማሳደግ ስራ ይሰራል። የዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነትና የዴሞክራሲያዊ አንድነት አስተሳሰብን እንዲሰርፅ አቅዶ ይሰራል። የትግሉን ፍሬዎች፣የአብሮነትና የዴሞክራሲያዊ አንድነትን የሚያጠናክሩ ለብሔራዊ መግባባት አስተዋፆ ያላቸው የኪነጥበብ ውጤቶች እንዲዘጋጁ ከባህል ቡድኑ ጋር ይሰራል።

- ✓ የልማት ኃይሎችን ተነሳሽነትና የተደራጀ ንቅናቄ በማሳደግ በግብርናና በኢንዱስትሪ ልማት፣ በመልካም አስተዳደርና በዴሞክራሲ ግንባታ ላይ አባላት ግንባር ቀደም ሆነው ምርታማነትን እንዲያሻሽሉና ውጤታማ እንቅስቃሴ እንዲያካሂዱ አመራር ይሰጣል።
- ✓ በዓመታዊ የለውጥ ንቅናቄ ውስጥ ድርጅቱንና ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱን ከአፍራሽ የጥቃት ቅስቀሳዎች የመመከትና የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የማስፋፋት ሥራ ይሰራል።
- ✓ በአባላት አማካኝነትና በቀጥታ በምሁራንና በጠቅላላ የህዝብ መድረኮች የህዝብ አደረጃጀቶችና መላ ህዝብ ውጤታማ እንዲሆኑ ብቁ አመራር በመስጠት ያረጋግጣል።

**ለ/ የጽ/ቤቱን ተልዕኮ በእውቀትና በተሟላ ክህሎት እንዲሁም በውጤታማነት የሚፈፅም ኮር የአመራር መዋቅር መገንባት**

- ✓ የ2010 ቁልፍና አበይት ተግባራት የፖለቲካና የድርጅት ስራዎች በተግባር ለውጥ የምናመጣባቸው ይሆናሉ። በእቅዱ አፈፃፀም አመራሩም ሆነ አባላት ኮር የለውጥ ኃይል፣ ግንባር ቀደም ሆነው የድርጅትና የልማት ተግባራትን ይፈጽማሉ። በአደረጃጀቶች አማካኝነት መላውን ህዝብ በእቅድ አፈፃፀም ዙሪያ ውጤታማ ንቅናቄ ያካሂዳሉ። ድርጅቱን ከጠላት አፍራሽ የጥቃትና የሰርጎ ገብነት እንቅስቃሴዎች ይጠብቃሉ።
- ✓ በእቅዱ ውጤት ለማምጣት፣ በ2009 ዓ.ም የአስተቃቀድ ጉድለቶች ላይ የቀረቡትና በየአካባቢው ያሉ መገለጫዎች ይቀርባሉ። አቅዶና ጀምሮ መተው፣ ውጤት አለማስመዝገብ፣ የራስ ተልዕኮ ላይ አለማተኮር፣ክትትልና ድጋፍ አለማካሄድ፣ የአፍራሽ ኃይሎችን አስተሳሰብና ተግባር ፊት ለፊት አለመታገል ችግሮች ቀርበው ትምህርት ይወሰድባቸዋል።
- ✓ ጥራት ያላቸውና ውጤታማ የእቅድ ተሞክሮዎች ተቀምረው ስራ ላይ እንዲውሉ ይሆናል። በየደረጃው የበላይ አካልን እቅድ መነሻ በማድረግ የ2010 እቅድ ያዘጋጃል። በየመድረኮቹ እየቀረበ ይተቻል። አንዱ ከሌላኛው በሚማርበትና በሰርቶ መማር በሚበለፅግበት አግባብ ይዘጋጃል።
- ✓ የድርጅቱ የመካከለኛ ዘመን (3 አመት) ስትራቴጅክ እቅድ አዘጋጅ ኮሚቴ በማደራጀት በየደረጃው ተተችቶ በማዕከላዊ ኮሚቴ ፀድቆ ተግባራዊ ይሆናል።
- ✓ የ2010 እቅድ ውጤት በሚያመጣ አግባብ መዘጋጀቱ ከተረጋገጠ፣ ቀጥሎ የሚመጣው ፈፃሚን በእቅድ ላይ ማዘጋጀት ይሆናል። በቂ ጊዜ ወስዶ በእቅድ አፈፃፀም ውጤታማ በሚያደርጉ አካሄዶች መግባባት ላይ ይደረሳል። በእቅዱ መግባባት ላይ መደረሱ ሲረጋገጥ ወደ ስራ ይገባል።
- ✓ በተግባር ምዕራፍ በገጠርና ከተማ ልማት ተግባራት የአመራሮችና የአባላት ውጤታማነት በየወቅቱ ይገመገማል። በመደበኛ የመልካም አስተዳደርና በዴሞክራሲ ተግባራት፣ በ2010 የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤት ምርጫ እንዲሁም በ12ኛ ድርጅታዊ ጉባዔ ተግባራት የግልና የወል ተልዕኮዎች ደረጃቸውን በጠበቁበት አግባብ መከናወናቸው ይረጋገጣል።
- ✓ ውጤታማነትን ስንከታተል መደበኛና ወቅታዊ ተግባራት በተቀመጠው ግብ መሰረት መከናወናቸውን ማረጋገጥ። በክትትልና በድጋፍ አመራሩ በራሱ ተልዕኮ ላይ አተኩሮ በመስራትና ሌሎችንም በመደገፍ፣ ከጠባቂነት ተላቆ ችግሮችን በመፍታት ተነሳሽነቱ ላይ ያተኮረ ይሆናል። አባላት ምን ያክል ታታሪና ውጤታማ እንዲሁም ለሌሎች ምሳሌ እንደሆኑ ይረጋገጣል። ድርጅቱንና ስርዓቱን ከአፍራሽ ኃይሎች ጥቃት የመመከትና በምትኩ፣ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ተግባር መያዙ እየተረጋገጠ ይሄዳል።

- ✓ በአፈፃፀም የሚታዩ ምርጥ ተሞክሮዎችን በተለይም፣ ከግልና ከወል ጥረት ውጤታማነትና የተደራጀ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙትን በአግባቡ መቀመርና ማስፋፋት፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋፋት ብቻ ሳይሆን በተግባር ውጤት ያሳዩትን መለየትና እውቅና መስጠት። አዳዲስ ግንባር ቀደሞችንና ታታሪዎችን በመመልመል ወደ ድርጅት ማስገባትና በቀጣይነት ማሳደግ። የአፈፃፀም ጉድለት ያሳዩትን የክህሎትና የአስተሳሰብ እንዲሁም የአፈፃፀም ችግሮችን የሚፈታ የተሞክሮ ልውውጥና የአቅም ግንባታ ስራ ማካሄድ።

## ሐ/ የጽ/ቤት አመራሩን አደረጃጀትና አሰራር ማጠናከር

- ✓ የጽ/ቤቱ ስራ አመራር ኮሚቴ፣ ተልዕኮውንና የ2010 እቅድ የአመራር ውጤታማነትንና የንቅናቄው ኮር እንዲሁም ግንባር ቀደምነትን ማዕከል አድርጎ በተቀመጠው አሰራር መሰረት ይገመግማል። ዝንባሌዎችን እየለየ በቀጣይነት የአመራር ሚናው ይረጋገጣል።
- ✓ አመራሩ ከጽ/ቤቱ ስራ አመራር አደረጃጀት አልፎ፣ በአስተባባሪ ኮሚቴና በጠቅላላ ስራ አመራር አደረጃጀቶች ከታታሪነትና ከውጤታማነት፣ ከአመራሮችና አባላት ግንባር ቀደም ንቅናቄ አንፃር እንዲሁም በአባላት አማካኝነት ምሁራን፣ የህዝብ አደረጃጀቶችና መላ ህዝቡ፣ ንቅናቄ ውስጥ መሆናቸውን ማዕከል ያደረገ ተሳትፎና ቀጣይ ስምሪት ይካሄዳል።
- ✓ የታችኞቹን አደረጃጀቶች የማጠናከርና ራሳቸውን ችለው እንዲንቀሳቀሱ የማስቻል ሥራ ይከናወናል። ማዕከላዊ ኮሚቴ በሚያስቀምጠው አቅጣጫ መሰረት 12ኛ ድርጅታችን ጉባኤ አሰራሩን ጠብቆ ያካሄዳል።
- ✓ በድርጅቱ የአሰራር መመሪያ መሰረት የመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንሶች ወቅታቸውን ጠብቀው ይካሄዳሉ። በህዋስ ደረጃ በልሳናት፣ በመደበኛ የስራ አፈፃፀም ግምገማና የልምድ ልውውጥ አማካኝነት ቀጣይ ግንባታ ብሎም የማጠናከር ስራ ይሰራል።
- ✓ የአመራርና የአባላት ማህደር አያያዛችን የጥራትና የወቅታዊነት እንዲሁም የወጥነት ችግሮች አሉበት። ይህን ችግር በሚፈታና ጥራቱንና ወቅታዊነቱን በሚያረጋግጥ አግባብ አጥርቶ መያዝ በትኩረት የሚከናወን ይሆናል።
- ✓ በየአደረጃጀቶቹ አማካኝነት የአዳዲስ ግንባር ቀደሞች ምልመላ፣ በፕሮግራሙና በህገ-ደንቡ መሰረት፣ የእጩና የሙሉ አባልነት ጊዜ መስፈርት እንዲፈፀም ክትትልና አመራር ይካሄዳል።
- ✓ የቀዩ የህዝብ አደረጃጀቶች የሴቶችና ወጣቶች ማህበራት፣ የሙያና ህብረት ስራ ማህበራት አደረጃጀቶች በጋራ ጉዳዮች ላይ የታቀደ ንቅናቄ ይካሄዳል። በአባላት ጥያቄና ተነሳሽነት አርሶ አደሩ በማህበር ተደራጅቶ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካ ጥቅሙን በሚያስጠብቅበት ሁኔታ ላይ የማህበሩ ነፃነት ተጠብቆ በጋራ ይሰራል።

## መ/ የማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ተዋረድ አደረጃጀቶችን በግብዓትና አቅርቦት ማጠናከር

- ✓ በ2010 የፖለቲካና የድርጅት ስራዎች እንዲሁም የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራት፣ የምርጫ 2010 እቅድና ሌሎች መወያያ ሰነዶች በጥራት እንዲሁም በሚፈለገው ወቅትና ጥራት ተዘጋጅተው ይቀርባሉ። በእቅዱና በሌሎች ሰነዶችም ላይ ግልጽነት የማስያዝ ተግባራት ይከናወናሉ።
- ✓ አብዮታዊ ዴሞክራሲ መጽሄትና ጋዜጣ እንዲሁም አዲስ ራዕይ መጽሄት ወቅታቸውንና ጥራታቸውን ጠብቀው ይቀርባሉ። በታቀደ ሁኔታ ውይይቶች እየተካሄዱና አቅም መፍጠራቸውም እየተረጋገጠ ይሄዳል።

- ✓ የድርጅቱን በጀትና የገንዘብ ስርዓት በአግባቡ ለማስተዳደር የሚያስፈልግ የሰው ኃይል ማሟላትን ያገናዘበ፣ ለታለመለት ዓላማ በትክክል መዋሉን እንዲሁም የንብረት አያያዝ ስርዓቱ የተጠበቀ መሆኑን የሚያረጋግጡ የግንዛቤና የቀጣይ ጊዜ ጠቃሚ ግብዓቶችን የማስያዝ ስራ ይሰራል፡፡

  በአጠቃላይ የጽ/ቤቱ የአመራር መዋቅር በጽ/ቤቱ ተልዕኮው ላይ ቅድሚያ ትኩረት በማድረግ፣ ቀጥሎ ደግሞ ከአስተባባሪ ኮሚቴውና ከጠቅላላ ስራ አመራር ኮሚቴው ጋር በጋራ በመንቀሳቀስ ኮር የለውጥ ኃይል ሆኖ፣ አባላት ውጤታማና ግንባር ቀደም ሆነው በአደረጃጀቶች አማካኝነት መላ ህዝቡን ማንቀሳቀስ የሚያስችለውን አመራር ይረጋገጣል፡፡

**ግብ 2 ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ተግባርን መርቶ ውጤት የሚያመጣ የተቋማት አመራር መገንባት፡፡**

**ተግባራት**

**ሀ/ የአመራሩን ኮር የለውጥ አመራር የመሆንና የታታሪነት እንዲሁም የውጤታማነት አስተሳሰብ መገንባት**

- ✓ በ2009 አፈፃፀም ግምገማና ከ2010 የቁልፍና አበይት ተግባራት ግቦች ኦረንቴሽን ጋር በተያያዘ መነሳሳትን፣ ቁርጠኝነትንና፣ የውጤታማነት እምነትን መፍጠር፡፡ ከአፈፃፀም ፍጥነትና ከጥራት እንዲሁም ከተደራሽነት ጋር የተያያዙ ችግሮች ላይ ጠንካራ መግባባትም ይፈጠራል፡፡ በ2009 ዓ.ም በነበረው አፈፃፀም ላይ የነበሩ የውጤታማነት፣የዳተኝነት፣ የጥራትና የተደራሽነት ችግሮች ላይ ግለሂስና ሂስ በማካሄድ የማስተካከል ስራ ይሰራል፡፡
- ✓ የቀበሌ የአመራር መዋቅር የመፈፀም አቅም በሚጠናከርበት ሁኔታ የማስተካከልና ስራውን መምራት የሚያስችል ስልጠና ይሰጣል፡፡
- ✓ የተሀድሶ ንቅናቄ ከተለኮሰበት ወቅት አንስቶ ስንታገላቸው የመጣን ግን ደግሞ ተነቅለው ያልተወገዱ፤ከስልጣን አተያይና አጠቃቀም ጋር ግንኙነት ያላቸው ችግሮች፣የትምክህት፣ የጠባብነት፣ የጎጠኝነት፣ የኃይማኖትን ሽፋን ያደረገ የአክራሪነት አዝማሚያዎች ተነቅለው በሚወገዱበት ሁኔታ መተማመን፡፡ በተለይም የራስን ተልዕኮ በአግባቡ ሳይወጡ አሻግሮ ማማረርና "ፍትሀዊ ተጠቃሚ አልሆንም፤ ይኸኛው አካባቢ ተጠቀመ፣ ይኸኛው ህዝብ ተጎዳ፤" የሚሉና የለውጥ አቅም የማይሆኑ የእድገትና የለውጥ እንቅፋት በራስ ውስጥ ሆነው እያሉ ሌሎችን ሰበብ ማድረግ የመሳሰሉ ዴሞክራሲያዊ ያልሆኑ የአስተሳሰብ ችግሮችን፣ ራስን ድክመቶች በማረም ሌሎቹን ፊት ለፊት በመታገልና በማስተካከል እንዲሁም ድርጅቱንና ስርዓቱን ከአፍራሽ አስተሳሰቦች በመጠበቅ በምትኩ የዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነትና ዴሞክራሲያዊ አንድነት አስተሳሰብን ልዕልናን መገንባት፡፡
- ✓ አመራሩ ከሚገኝበት ርከን ወደታች ያሉትን በተግባር ውጤታማ በሚሆኑበት ደረጃ ማብቃት፣ የአመራሩ ዋነኛ ተልዕኮው መሆኑን ይዞ እንዲሰራ ማስቻል፡፡ በመደበኛ ልሳናትና በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በቀጣይ የአስተሳሰብና የአፈፃጸም ውይይት በማካሄድ ግልጽነትንና በተግባር ውጤታማነትን ማስፋፋት፡፡
- ✓ የታችኛውን አመራር፣በመሰረታዊ መለያ እምነቶቻችን ፣በእቅድ አስተቃቀድና በተደራጁ ንቅናቄ ዙሪያ ስልጠና መስጠት፡፡

**ለ/ የአመራሩን የውጤታማነት ክህሎት ማሳደግ**

- ✓ በሁኔታ ግምገማው እንደተለየው አመራሩ በተግባር ውጤት የማምጣት (Delivery) ችግሮች አሉበት። የዚህ ዓመት እቅድ የህዝቡን የልማትና የመልካም አስተዳር ችግሮች በሚፈታ አኳኋን፣ በየደረጃውና በየተቋማቱ ለውጤት የሚያበቃ እቅድ መታቀዱ መረጋገጥ ይኖርበታል።
- ✓ እቅዱ ሲዘጋጅ አመራሩና ባለሙያዎች የተሳተፉበት መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል። እቅዱን አባላትና ህብረተሰቡ እንደየአግባቡ ሊያዳብሩት መቻሉ መረጋገጥ ይኖርበታል። የእቅዱን የበላይ አካላት አንብበው በውጤታማነት ዙሪያ ተጨማሪ ግብረ መልስና ግብዓት እንደሰጡበት ይጠበቃል።
- ✓ እቅዱ ከተዘጋጀ በኋላ አመራሩ ራሱ፣ ባለሙያው፣ ህዝቡ በቂ ጊዜ ወስደው መወያየትና መተማመንን መፍጠርን ይጠይቃል። በአፈፃፀም ሂደት ውጤታማ ከሆኑ አካባቢዎች ተሞክሮ በመቀመር እየዳበረ እንደሚሄድ ታሳቢ አድርጎ ሁሉም በሰርቶ መማር ውጤታማ ክህሎትን እያዳበረ የመሄድ ተነሳሽነትንና ቁርጠኝነትን መያዝ ይኖርበታል።
- ✓ ምርጥ የእቅድ አዘገጃጀትና ውጤታማ የአፈፃፀም ተሞክሮዎች እየተቀመሩ፣ በቀጣይ ትምህርት በሚሰጥ አግባብ ይስፋፋሉ። የክትትልና ድጋፍ ስርዓቱ የእቅዱን መሳካትና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመለየት እንዲሁም ምርጥ አፈፃፀም ያሳዩትን አመራሮች የሚለይ ብሎም  ደካማ አፈፃፀም ያሳዩትን አቅም በሚፈጥር የግምገማና የተሞክሮ ልውውጥ አግባብ ይከናወናል።

**ሐ/ የአመራሩን የአሰራርና የአደረጃጀት ውጤታማነት ማረጋገጥ**

- ✓ ዓመታዊ እቅዱን ለመፈፀም የተቀመጡ የግልና የጋራ አሰራሮች በአግባቡ ይፈፀማሉ። የጋራ ኮሚቴ፣የተቋም ስራ አመራር ኮሚቴ፣ በተቀመጠለት ጊዜ ሰሌዳ የእቅድ አፈፃጸም ውጤታማነቱን እየገመገመ ትምህርት የመውሰድና ምርጥ ተሞክሮዎችን የማስፋፋት ሥራ በጥብቅ ዲስፕሊን ይተገበራል።
- ✓ በስራ ስምሪቱ የአመራርና የባለሙያዎች ጥምረት መረጋገጥ መቻል ይኖርበታል። ባለሙያዎችን ያላሳተፈ የልማትና የመልካም አስተዳደር እቅድ ትግበራ ውጤታማነት፣ ሙያዊ መሆኑና አለመሆኑ አጠያያቂ እንደሆነ ታውቆ ጣምራ እንቅስቃሴ ይጠይቃል።
- ✓ ውጤት በማያመጡት ላይ የተጠያቂነት አሰራር በጥብቅ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቃል።
- ✓ በሙስና ዙሪያ ጥቆማ ቀርቦ ተጣርቶ  ባልተጠናቀቁ አመራሮች ላይ አጣርቶ ውሳኔ መስጠት።
- ✓ የልማትና የመልካም አስተዳደር እንዲሁም የዴሞክራሲ ግንባታ ተግባሮቻችን በተደራጀ የልማት ሰራዊት አማካኝነት መፈፀማቸውን ማረጋገጥ። በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ፋይዳውን አሳንሶ ማየት፣ ጀምሮ መተው፣ አደረጃጀቶችን ከአፍራሽ ቅስቀሳዎች አለመጠበቅና በውጤታማነት ወደ ስራ ያለማሰማራት የመሳሰሉ ሁኔታዎች በቀጣይ የአስተሳሰብ ግንባታ ማስተካከል።
- ✓ የመሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ አደረጃጀቶች ያለመጠናከር መነሻ ምክንያቱ የትኩረትና የቀጣይ ክትትል ችግር በመሆኑ፣ ችግሮቹን በሚፈታ አግባብ የተቀመጠውን አሰራር ጠብቆ በቀጣይነት አመራር ማረጋገጥ። በመሰረታዊ ድርጅትና በህዋሳት አደረጃጀቶች አማካኝነት መላ ህዝቡን በልማት ቡድንና በአንድ ለአምስት አደረጃጀቶች ማነቃነቅ።

**መ/ የአመራሩን የግብዓት አቅርቦትና ውጤታማ አጠቃቀም ማረጋገጥ**

- ✓ ከበላይ አካል የሚቀርቡት ግብዓቶች፣ እቅድና ምርጥ ተሞክሮዎች የተቀመሩባቸው ሰነዶች ናቸው። የመነሻ እቅዱንም ሆነ የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎች ከአካባቢው ሁኔታ ጋር የተዛመዱ መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ በተለይም አንገብጋቢ ብለን የለየናቸውን የውጤታማነት፣ የፍጥነት፣ የጥራትና የተደራሽነት ችግሮች በሚፈታ አግባብ ስራ ላይ ለማዋል ጥረት ይጠይቃል።
- ✓ ወቅታዊ ጉዳዮችን የተመለከቱ መጽሄቶችን ጋዜጦችንና ሌሎች ሰነዶችን በጥልቀትና በሚገባ ተመልክቶ እንዲሁም ከአካባቢው ሁኔታ ጋር አዛምዶ ለተግባራዊነቱ ጥረት ማካሄድ ይጠይቃል።
- ✓ ከበታች አካላት የሚመጡ ሪፖርቶችን በአግባቡ አንብቦና ተረድቶ፣ የሌሎች አካባቢዎችንም ልምድ አገናዝቦ ለውጤት የሚያበቃ ተግባራዊ ድጋፍ ይካሄዳል።
- ✓ በመንግስትና በድርጅት የሚቀርቡ የበጀትና የቁሳቁስ ድጋፎችን ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች በፀዳ ሁኔታ ለታለሙላቸው ተግባራት በውጤታማነት መጠቀምና ተግባራዊ ለውጥ ማምጣት፣
- ✓ በየደረጃውና በየተቋማት የምንገኝ የአመራር አባላት፣ ከላይ የተጠቀሱትንና አመራሩን ውጤታማነት የሚያሳድጉ ተግባራትን ከራሳችን ሁኔታ ጋር በማገናዘብ በተግባር ለውጥ እያመጣን፣ በሰርቶ መማር ተግባራትን ማዕከል ያደረገ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ግንባታን እንድናረጋግጥ ይጠበቃል።

**ግብ 3 አባላት በተግባር ውጤታማ፣ ምሳሌና ግንባር ቀደም እንዲሁም ድርጅቱንና ስርዓቱን ከአፍራሽ ኃይሎች ጥቃት የሚጠብቁ በሚሆኑበት የብቃት ደረጃ ላይ ማድረስ**

**ተግባራት**

**ሀ/ የአባላትን በተግባር ታታሪና ውጤታማ እንዲሁም አፍራሽ እንቅስቃሴዎችን የሚታገሉ በሚሆኑበት የአስተሳሰብ ደረጃ ላይ ማድረስ።**

- ✓ የሲቪል ሰርቪስ፣ የኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም የሌሎች ትምህርት ተቋማት (መምህራንን ጨምሮ)፣ አባላት ለህዝቡ በተግባር ሙያዊ አገልግሎት በማቅረብ ለሌሎች ምሳሌ በሚሆን ደረጃ ላይ እንዳልደረሱ በግምገማው ተለይቷል። በ2010 መነሻና የቀጣይ ግቦችና ተግባራት ላይ አባላት ውጤታማ ሆነው ለሌሎች ምሳሌ በሚሆኑበት ደረጃ ላይ ማድረስ።
- ✓ በእቅዱ የባለሙያዎችን ድርሻ ማዕከል በማድረግ፣ ከዝግጅት እስከ አፈፃፀም አግባብ ግልጽነትና መተማመን መድረስ። በሲቪል ሰርቪሱና በአመራሩ መካከል የሚታየውን የተቀናጀ እንቅስቃሴ ጉድለት የሚፈታ ግልጽ ውይይትና ግልጽ የስራ ክፍፍል ማካሄድ።
- ✓ በሲቪል ሰርቪስ አባላት ውስጥ አሁን ድረስ ያልተወገዱ የትምክህት፣ የጎጠኝነት፣ የጠባብነትና ኃይማኖትን ሽፋን ያደረጉ የአክራሪነት ዝንባሌዎች እንዳሉ በሁኔታ ግምገማችን ተመልክቷል። የራስን ተልዕኮ በብቃት ሳይወጡ ፍትሀዊ ልማትና አገልግሎት እንደሌለ አድርጎ አሻግሮ የማማረርና ችግሮችን ውጫዊ የማድረግ አስተሳሰቦች እንዳልተነቀሉ በሁኔታ ግምገማው ተለይቷል። በእቅዱ አፈፃፀም ግምገማና በቀጣይ የአፈፃፀም አረንቴሽን፣ በልሳናት ውይይቶች፣ በቀጣይነት ማስተካከልና ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብን ማጎልበት። በሙህራን አባላት ዘንድ አሁን የሚታየውን ለአብሮነት የማይበጅ ብሔርተኝነትን በማስተካከል በምትኩ የዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት አስተሳሰቦችንና መሰረታዊ

መርሆዎችና እሴቶች ላይ መተማመን፡፡ መዋቅሩ የራሱን በውጤታማነት አገልግሎት የመስጠት ችግሮች አይቶ ለለውጥ እንዲነሳሳ ማስቻል፡፡

- ❖ የጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሽ አባላት በየተሰማሩበት መስክ፣ ምርታማነትን በማሳደግ ውጤታማ ሆነው ለሌሎች አንቀሳቃሾች ምሳሌ በሚሆኑበት የታታሪነት ደረጃ ላይ ማድረስ፣
- ✓ አንቀሳቃሽ አባላት የሚታዩባቸው የጠባቂነትና የአልችልም ባይነት ሁኔታ ተወግዶ፣ በየተሰማሩበት መስክ ውጤታማ ሆነው ከደረጃ ወደ ደረጃ ይሸጋገራሉ፡፡ አንቀሳቃሾች ለስኬትም ሆነ ለውድቀት ዋናዎቹ ባለቤቶች ራሳቸው ሆነው ሳለ፣ ሌሎችን የማማረርና ችግሮችን ውጫዊ የማድረግ የአስተሳሰብ ችግሮችን ታግሎ ማስተካከል፡፡ ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነትና ዴሞክራሲያዊ አንድነት አስተሳሰብ ማሳደግ፡፡ ሌሎቹም በመልካም ስራቸው የሚቀበሏቸው እንዲሆኑ መስራት፡፡ ለዚህም እቅዱን አንቀሳቃሾቹ የተሳተፉበትና አዳብረው የራሳቸው አድርገው በሚንቀሳቀሱበት ደረጃ ማድረስ፡፡
- ✓ ከተዘጋጀው የወል እቅድ ባሻገር፣ አባላት የራሳቸውን ዕቅድ በድርጅትና በግል በአፈፃፀማቸው ውጤታማ በሚሆኑበት ደረጃ ያዘጋጃሉ፡፡ ምርጥ እቅዶችን በሞዴልነት በመውሰድም የማስፋፋት ስራ ይሰራል፡፡
- ✓ በልሳናትና በወቅታዊ ጽሁፎች እንዲሁም በስራ አፈፃፀም ግምገማ ላይ ተመስርቶ በቀጣይነት የግልጽነት፣ የታታሪነትና የውጤታማነት አቅም ይገነባል፡፡
- ❖ አርሶ አደሮች በትልቁ አቅደው በትልቁ በመፈፀም፣ የተሻሻሉ አሰራሮችንና ቴክኖሎጅዎችን ስራ ላይ በማዋል የራሳቸውን ኑሮ አሻሽለው ለሌሎች ምሳሌና ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል ዝግጅትና ቁርጠኝነት መገንባት፡፡ በትልቁ አቅዶ በትልቁ መፈፀም ሲባል ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግና የኑሮ መሻሻልን ማረጋገጥ ማለት ነው፡፡
- ✓ የ2010 እቅድ ዝግጅትም ሆነ በእቅድ ላይ የሚካሄደው የተግባቦት ስራ፣ አርሶ አደር አባላት ከቁጥቁጥ አስተሳሰብ ወጥተው በሰብል፣በእንስሳት ሀብት ልማትና በአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም በደን ልማት መስኮች ውጤታማ በሚሆኑበት ደረጃ መተማመን ይጠይቃል፡፡
- ✓ በ2009 ዓ.ም እቅድ አፈፃፀም ግምገማና በ2010 እቅድ ጭብጦቹ ላይ መተማመን ከተደረሰ በኋላ፣ አባላቱ የግል እቅዳቸውን እንዲያዘጋጁና በአካባቢው ስኬታማ የሆነን ግንባር ቀደም አርሶ አደር እቅድ መነሻ ያደረገ ይሆናል፡፡
- ✓ በቀጣይነት ተነሳሽነት፣ ዝግጁነት፣ ቁርጠኝነት እንዲሁም ለሌሎች ምሳሌ በሚሆኑበት ደረጃ፣መደበኛ የልሳናትና በወቅታዊ የልማትና መልካም አስተዳደር ተግባራት ላይ ማወያየትና ተነሳሽነትንና ተግባራዊ ለውጥን ማጎልበት፡፡ ድርጅታቸውንና ስርዓቱን ከፀረ-ህዝብ አፍራሽ ቅስቀሳና ጥቃት መከላከል አንዱ አባላት የጥንካሬ መለኪያ ሆኖ ይወሰዳል፡፡

**ለ/ የአባላትን የመፈፀም ክህሎትና እውቀት ብሎም ውጤታማነት ማሳደግ፣**

- ❖ የሲቪል ሰርቪስ አባላት የመፈፀም ክህሎት፣ እውቀትና የውጤታማነት ችግሮች በሁኔታ ግምገማው ተጠቅሰዋል፡፡ ስኬታማ አፈፃጸምና ውጤታማነት ያሳዩ፣ በአገልግሎት አሰጣጣቸው በህዝቡ የተመሰከርላቸውንና ሞዴሎችን መርጦ፣ በዚህ ደረጃ ሁሉም አባላት ውጤታማ የሚያደርጋቸውን እቅድ ያዘጋጃሉ፡፡
- ✓ በሰርቶ መማማር፣ በቀጣይነትም እየተሻሻለ በሚሄድበት ደረጃ ስምምነት ይዞ ከአመራሩ ጋር የተቀራረበና ህዝብን በጋራ የማገልገል ክህሎትና ዝግጅት ይረጋገጣል፡፡ በቀጣይነት በአፈፃፀም ግምገማና በምርጥ ተሞክሮዎች ልውውጥ የማቀድና የመፈፀም እውቀትና ክህሎትን ማሳደግ፣

- ✓ የአፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመቀመርና የተሻለ ብቃት ያላቸውን መለየት በሚያስችል አግባብ መፈፀም። የተገኙ ተሞክሮዎች በአግባቡ ተቀምረው የሲቪል ሰርቪስ አባላትን ሙያዊ ክህሎትና የመፈፀም አቅም እንዲያሻሽሉ ይደረጋል።
- ❖ የጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሾችን ምርታማነትና ውጤታማነት የሚያረጋግጥ የእቅድ ዝግጅት ክህሎት ማስያዝ። በመስኩ የተሳካላቸውን ምርጥ ተሞክሮዎች በመውሰድ በነዚሁ ሞዴል እቅድና የውጤታማነት ተሞክሮዎች ላይ ተመስርቶ፣ የሁሉም አንቀሳቃሾች የወልና የግል እቅድ ያዘጋጃሉ። በተዘጋጀው እቅድ ላይ የውድድር መንፈስ በሚፈጥር ሁኔታ መተማመን፣ በቀጣይም የተሻሉትን መርጦ የማስጎብኘትና ተሞክሮዎች መቀመር። መልሶ ማስፋፋት፣ በሰርቶ መማር አማካኝነትም ውጤታማነትንና ምርታማነትን ማሳደግ።
- ✓ ከጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሾችንና ከፋብሪካ ሰራተኞች አባላት በክትትልና ድጋፍ ስራችን ምርጥ የምርታማነትና የውጤታማነት ተሞክሮ ማዕከል በማድረግ፣ ምርጥ ፈፃሚዎችን ለመለየትና ሞዴልነታቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ማስቻል ነው።
- ❖ አርሶ አደር አባላት የሚያዘጋጁት እቅድ ትልቅ እቅድ አቅደው ትልቅ አፈፃፀም ያሳዩትን በሞዴልነት በመውሰድ ይሆናል።
- ✓ በእቅድ አዘገጃጀት ላይ መተማመን በመፍጠር፣ በሰርቶ መማር በሚሻሻልበት አግባብ የግልና የአካባቢውን የወል ልማት የተመለከተ እቅድ ያዘጋጃሉ።
- ✓ የተዘጋጀው እቅድ በሰርቶ መማርና በምርጥና ውጤታማ አፈፃፀም እየዳበረ የሚሄድ ይሆናል። የተሻሻሉ አሰራሮች የቀላል ትራክተሮች አጠቃቀም፣ ውሃን በቁጠባና በውጤታማነት አጠቃቀም፣ በቋሚ ሰብሎች የፍራፍሬ ልማትን ማካሄድና ሌሎችንም የግብርና ቢሮ ቅድሚያ ሰጥቶ ያቀዳቸውን ማዕከል በማድረግ የሚሰራ ይሆናል።
- ✓ ቀጣይነት ባለው የክትትልና ድጋፍ ሥራ በአርሶ አደር አባላት ውስጥ የሚካሄደውን ምርጥ አፈፃጸም መለየት፣ ውጤታማና ምርጥ የሆኑትን ተሞክሮዎች ቀምሮ በማስፋፋት ወደ ሁሉም ማድረስ ይሆናል።

**ሐ/ የአባላትን አደረጃጀትና አሰራር ውጤታማና ምርታማ በሚሆንበት አግባብ መምራት**

- ❖ የሲቪል ሰርቪስና የመምህራን አባላት የአስተሳሰብ ግንባታ የሚያካሂዱባቸው የህዋስና አደረጃጀቶች አሏቸው። ተግባራዊ ስምሪት የሚያካሂዱበት የልማት ቡድንና የአንድ ለአምስት አደረጃጀቶች አሏቸው። በእነዚህ አደረጃጀቶች የግልና የቡድን አፈፃፀም ውጤታማነትን የሚያረጋግጥ አሰራር ተግባራዊ ይሆናል።
- ✓ በአደረጃጀቱ የአፈፃፀም ግምገማ፣ የግለሂስና ሂስ እንዲሁም የደረጃ ምደባ የመሳሰሉት አሰራሮች ወቅታቸውን ጠብቀው በጥብቅ ተግባራዊ መደረጋቸው ይረጋገጣል። ውጤታማ ለሆኑ አደረጃጀቶች እውቅናና ሽልማት የመስጠት አሰራር ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል። ተልዕኳቸውን በማይፈጽሙ ላይ የተጠያቂነት አሰራርን በጥብቅ ተግባራዊ የማድረግ እንዲሁም ሽግሽግና መልሶ የማጠናከር ስራ ይሰራል።
- ❖ የአንቀሳቃሽ አባላት አደረጃጀቶችና አሰራሮች ውጤታማነትና ምርታማነት በሚያድግበት ደረጃ ማጠናከር።
- ✓ እንደ ሲቪል ሰርቪሱ ሁሉ አንቀሳቃሽ አባላት የአስተሳሰብ ግንባታ የሚያካሂዱባቸው የህዋስና የመሰረታዊ ድርጅት አደረጃጀቶች ያሏቸው በመሆኑ፣ አደረጃጀቶቹ ወቅታቸውን ጠብቀው ውጤታማና ምርታማ በሚያደርጉ ጭብጦች ላይ ውይይት እንዲሁም የተደራጀ ንቅናቄ ያካሂዳሉ።

- ✓ አንቀሳቃሾቹ በስራ ስምሪት ውጤታማ የሚሆኑባቸው የስራ አደረጃጀቶች አሏቸው፡፡ የቡድኑ አባላት የግልና የጋራ ኃላፊነታቸውን በብቃት ተወጥተው ምርታማና ውጤታማ የሚሆኑበትን የስራ አደረጃጀቶችን በቀጣይነት ማጠናከር፡፡
- ✓ ውጤታማ የሆኑትን በመለየት የእውቅናና የሽልማት አሰራርን ማጠናከር፣ ውጤታማ በማይሆኑት ችግሮቹን መሰረት ያደረገ የተሞክሮ ልውውጥ ማካሄድና ማሻሻል እንዲሁም መንግስታዊና ድርጅታዊ ተጠያቂነት የራሱ ውስንነት ቢኖረውም፣ በውስጥ አሰራራቸው የማስተካከያ ርምጃዎች እንዲወሰዱ ግፊት በማካሄድ አፈፃፀሙን መከታተል፡፡
- ✓ የአርሶ አደር አባላትን ውጤታማነትና ምርታማነት በአደረጃጀቶች ማጠናከር፡፡ አባላት የአስተሳሰብ አድማሳቸውንና ግንዛቤያቸውን ማሳደግ የሚችሉት የህዋስና የመሰረታዊ ድርጅት አደረጃጀቶች እንዳሏቸው ግልጽ ነው፡፡ በአደረጃጀቶቹ ፋይዳ ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን በማስተካከል፣ ውጤታማ ሆነው በመወያያ ጽሁፎችና በተሞክሮዎች ልውውጥ አቅም የሚፈጥሩና ፖለቲካዊ ብቃታቸውን የሚያሳድጉ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በዚህ ሂደት መሰረታዊ ጥቅሞቻቸውን የሚጋፉ የፀረ-ህዝብ አፍራሽ ቅስቀሳዎችንና የጥቃት እንቅስቃሴዎችን ያከሽፋሉ፡፡ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ የአስተሳሰብ ልዕልና እያሳደጉ ይሄዳሉ፡፡
- ✓ አርሶ አደር አባላት የወል ልማት እንቅስቃሴ የሚያካሂዱባቸው ተሞክሮዎችን የሚለዋወጡባቸው የልማት ቡድንና የአንድ ለአምስት አደረጃጀቶች አሉ፡፡ እነዚህ አደረጃጀቶች ውጤታማ ስራ የሚሰራባቸውና ምርታማነት የሚሻሻልባቸው በሚሆኑበት ደረጃ ይጠናከራሉ፡፡ አባላት በነዚህ አደረጃጀቶች የመሪነት ሚና ሊጫወቱ ይገባል፡፡

✓ አባላት በአርሶ አደር ማህበር ተደራጅተው በመሰረታዊ በኢኮኖሚ በማህበራዊና በፖለቲካዊ ጥቅሞቻቸው ዙሪያ መታገል እንዲችሉ፣ በአርሶ አደር ማህበር እንዲደራጁ ግፊት ያደርጋሉ፡፡ በአደረጃጀቱ ሂደት የድጋፍና የግንባር ቀደም ሚና ይኖራቸዋል፡፡

✓ የተቀመጠውን አደረጃጀትና አሰራር በአግባቡ በማይፈጽሙት ላይ ድርጅታዊ ተጠያቂነትን ማጠናቀርና የውድድር መንፈስን ማጎልበት ውጤታማ ለሆኑት ደግሞ እውቅናና ሽልማት መስጠቱ ተግባር በትኩረት ይሰራበታል፡፡

  - በሁሉም ዘርፍ የሚገኙ አባላት በቀጣይነት ግንባታ ተደርጎላቸው ለውጥ የሚያመጡና ውጤታማ የማይሆኑትን ማጣራትና ማሰናበት፡፡

**መ/ አባላትን ውጤታማ የሚያደርጉ አቅርቦቶችንና ግብዓቶችን ማሟላት**

አባላት ራሳቸው ግንባር ቀደምና ውጤታማ ሆነው ሌሎቹን ማንቀሳቀስ የሚችሉት፣ ከበላይ አካል የሚጠበቁት ግብዓቶች በወቅቱና በጥራት ሲቀርቡና በራሳቸው በአባላት መቅረብ የሚገባቸው ደግሞ ተለይተው በራሳቸው መቅረባቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡

❖ **ከበላይ አካላት መቅረብ የሚገባቸው**

- ✓ መነሻ እቅድ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ መነሻ እቅዱን አባላት በየተሰማሩበት ሁኔታ አዛምደው በግልና በጋራ የሚተገብሩት እንጂ፣ እንዳለ ከላይ የወረደው እቅድ ሊሆን አይገባም፡፡ በመሆኑም የ2010 መነሻ እቅድ ለአባላት ይቀርባል፡፡
- ✓ የሲቪል ሰርቪሱ አባላት ተሞክሮዎችን የሚወስዱባቸው የምርጥና የግንባር ቀደም ሲቪል ሰርቪስ አባላት በራሳቸው ተቀምረው ከእቅድ እስከ አፈፃፀም በሚያስተምር አግባብ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በጥቃቅን አባላትም ስኬታማ ከሆኑ አንቀሳቃሾችና ግለሰቦች የተገኙ የምርጥ አፈፃፀምና ሞዴሎች ተቀምረው ይቀርባሉ፡፡

- ✓ በአርሶ አደር አባላትም ምርታማነትን በማሳደግም ሆነ በጠቅላላው ውጤታማ በመሆን ትልልቅ የአፈፃፀም ውጤቶችን ያሳዩት ተመርጠው ልምዳቸው ይቀመራል፤ ተሞክሮዎቹን በማስፋፋት ለሌሎች ግብዓት ይሆናሉ።
- ✓ የአባላትን የአስተሳሰብ አድማስ የሚያሳድጉና ፖለቲካዊ ብቃትን የሚያጎለብቱ ጽሁፎች በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መጽሄት ለሲቪል ሰርቢስ አባላት፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋዜጣ የትኩረት አምድ ለአንቀሳቀሾችና ለአርሶ አደር አባላት ወቅቱንና ጥራታቸውን ጠብቀው ይቀርባሉ። ሌሎች ወቅታዊ ጽሁፎችና ግብረ መልሶችም እየተተነተኑ በግብዓት መልኩ ይቀርባሉ።
- ✓ ለአርሶ አደሩ የግብርና፣ የእንስሳትና የደን ልማት ተግባራት፣ የተሻሻሉ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች ወቅታቸውንና ጥራታቸውን ጠብቀው እንደሚቀርቡ ታሳቢ ተደርጎ፣ ሁሉም አባላት በምክረ ሀሳቡ መሰረት ግንባር ቀደም ሆነው ይወሰዳሉ።
- ✓ ከበላይ የማይቀርቡና በአካባቢው በአባላት፣ በራሳቸውና በቅርብ አመራር የሚቀርቡትን መጠባበቅ ሳይኖር ግልጽ የስራ ክፍፍል ተቀምጦ ይፈፀማሉ።
- ✓ በአጠቃላይ በሁሉም የስራ መስኮች፣ ተቋማትና በተዋረድ የሚገኙ አባላት በሁኔታ ግምገማችን የተለዩ የውጤታማነትና የጥራት ችግሮችን በሚፈታ አግባብ ተግባርን ማዕከል ያደረገ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ግንባታን በማጠናከር፣ ግንባር ቀደም ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይጠበቃል። አባላቱ በተሰማሩበት ቦታ ሁሉ ውጤታማነት ሰፍኖ፣ የህዝቡ የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲፈቱ መረባረብ ይጠበቅባቸዋል።

**ግብ 4 የወጣቶች ሊግ አመራሮችንና አባላትን ውጤታማነት በተሰማሩበት መስክ ማረጋገጥ**

- ✓ የወጣት የሊግ አመራሮችም ሆኑ አባላቱ፤ የእናት ድርጅታቸውን ተልዕኮ የሚፈጽሙ በመሆናቸው፣ከላይ በአመራሩና በአባላት የተቀመጡት ተግባራት በሊግ አመራሩና በአባላት ውስጥ ከሁኔታው ጋር ተዛምደው ተግባራዊ ስለሚሆኑ ይህንኑ ተልዕኮ ደግሞ መፃፍ ከድግግሞሽ በስተቀር የተለየ ውጤት የለውም። የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከሊጉ ተልዕኮ አንፃር ለየት ያሉት የአስተሳሰብ፣ የክህሎት፣ የእውቀት፣ የአደረጃጀትና የአሰራር ጉዳዮች ለሊጉ እቅድ መነሻ በሚሆኑ ደረጃ ቀርበዋል።

**ሀ/ ለሌሎችም ወጣቶች ምሳሌ የሚሆን የውጤታማነትና የስኬት አስተሳሰብ መገንባት**

- ✓ የሊግ አመራሩም ሆነ አባላት በአደረጃጀቶቻቸው ለጠቅላላ ወጣቱ ኮር የለውጥ ማዕከልና አብነት በሚሆኑበት ደረጃ ውጤታማ የሚያደርጉ አስተሳሰቦችን ማዕከል በማድረግ፣ የ2009 ዓ.ም እቅድ አፈፃፀም ግምገማና የ2010 እቅድ ዝግጅት ይካሄዳል።
- ✓ የራሳቸውን ሁኔታ የተመለከቱ የመወያያ ሰነዶችና የውጤታማነትና የስኬት ምርጥ ተሞክሮዎች እየተዘጋጁ በብስለት ይወያያሉ። ስራ የያዙት በየተሰማሩበት መስክ ምርታማና ውጤታማ መሆናቸው ይረጋገጣል። እስካሁን ቋሚ ስራ የሌላቸው በተፈጠረው እድል ግንባር ቀደም ሆነው የራሳቸውን ተነሳሽነትና ቁጭት ሰንቀው አብነታዊ ስራ የሚሰሩት ሁኔታ ይረጋገጣል።
- ✓ ከጠባቂነት፣ከአልችልም ባይነት እንዲሁም የራስን ተልዕኮ ሳይወጡ ስርዓቱን ከማማረር ጋር የተያያዙ ችግሮችን በመሻገር፣በተሻሻሉ አሰራሮችና ምርታማነትን በሚያሳድጉ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ላይ በመተማመን በእቅዱ መሰረት ወደ ስራ ይገባሉ። በቀጣይ ከችግሩ እየወጣን መሆኑ ይረጋገጣል።

- ✓ አደረጃጀቶቻቸው ትልቅ የመታገያ ማዕከል ሆነው ሳለ፣ እነሱን በመተው እንደ መሸጋገሪያ የመመልከትና ከስልጣን አተያይ ጋር የተያያዙ ችግሮች በታዩበት ገጽታ ሁሉ እየታገሉ፣ ሁሉም የተሰማሩበትን ሥራ ውጤታማ እንዲያደርጉ ማስቻል።
- ✓ ወጣቱ ውስጥ የሚታዩ መጤ አስተሳሰቦችና የወጣቱን ህይወትና የወደፊት ተስፋ አደጋ ላይ የሚጥሉ ደባል ሱሶች እንዲፀየፉና በችግሩ ውስጥ ያሉም ከችግሩ እንዲላቀቁ አቅዶ ይንቀሳቀሳሉ።
- ✓ ፀረ-ህዝብ ኃይሎች በየወቅቱ የሚካሂዱት የጥፋት ቅስቀሳ በቀላሉ ሰላባ የመሆን ሁኔታን በቀጣይነት በሚቀይር አስተሳሰብ መቀልበስና ልማታዊነትን ማሳደግ። የዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነትና ዴሞክራሲያዊ አንድነት አስተሳሰብ ላይ መተማመን።

**ለ/ የወጣት ሊግ አመራሮችንና አባላትን የውጤታማነት ክህሎት ማሳደግ**

- ✓ ውጤታማ እቅድን የማዘጋጀት እውቀትንና ክህሎትን እንዲያሳድጉ ይሰራል። ውጤታማ እቅድ ከእቅድ ዝግጅት እንደሚጀምር ግልጽ ነው። የውጤታማ የሊግ አመራሮችና አባላት ወይም ደግሞ የሌሎች ወጣቶች ተሞክሮዎች ተቀምረው ለእቅድ መነሻ ይሆናሉ። ሁሉም በምርጥ እቅዶች ሞዴል መሰረት ያቅዳሉ።
- ✓ በእቅዱ ተፈፃሚነት ላይ ጊዜ ወስዶ መተማመን ይገባል። የእቅዱ ጭብጦች፣ በየተሰማሩበት መስክ ምርታማነትንና ውጤታማነትን በማሳደግ ላይ ያተኮሩ ይሆናሉ። አፈፃፀሙን በተመለከተ በሊጉ መዋቅር አማካኝነት ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ይካሄዳል። ከሂደቱ የሚገኙ ምርጥ ተሞክሮዎች፣ ሂደቱና ውጤቱ እየተቀመረ ሌሎች የሊግ አባላት እንዲወስዱትና ተግባራዊ እንዲያደርጉት ይሆናል። በሰርቶ መማርና በቀጣይነትም በማዳበር ውጤታማ እቅድና ውጤታማ አፈፃፀም ይረጋገጣል።

**ሐ/ ጠንካራና ውጤታማ የወጣቶች አደረጃጀትና አሰራር ይረጋገጣል**

- ✓ አደረጃጀቶቹ የፖለቲካዊና ድርጅታዊ አስተሳሰብ የሚገነባባቸውና በተግባር ቁሳዊና ህይወታዊ ለውጥ ለማምጣት ስምሪት የሚካሄድባቸው ሊሆኑ ይገባል።
- ✓ የሊግ አመራሮችና አባሎች በአደረጃጀታቸው ፖለቲካዊ ብቃታቸውንና አደረጃጀታቸውን የሚያጠናክሩ የውይይት አደረጃጀቶችንና አሰራሮችን በጥብቅ ተግባራዊ ያደርጋሉ።
- ✓ ቁሳዊና ህይወታዊ የኑሮ መሻሻል ለማምጣት ደግሞ በጥቃቅንና አነስተኛ፣ በገጠርና በከተሞች የግል የስራ ስምሪት ራሳቸው ውጤታማ ሆነው፣ ለሌሎች ተሞክሮዎች የሚያስተላልፉባቸው የልማት ቡድንና የአንድ ለአምስት አደረጃጀቶችን የማጠናከር ተግባር በትኩረት ይከናወናል።
- ✓ በግልና በወል የስራ ስምሪቱ ውጤታማ ያልሆኑት የሚጠየቁበት አሰራር ተግባራዊ የሚሆን ሲሆን፣ ውጤታማ የሆኑት ደግሞ ደረጃው እየተለየ እውቅናና ሽልማት የሚያገኙበት አሰራር እንደ አንድ የውጤታማነት መንገድ ተግባራዊ መሆን መቻል ይኖርበታል።

**መ/ ለወጣቶች ሊግ አመራሮችና አባላት ውጤታማነት የአቅርቦት ጉዳዮችን ማሟላት**

- ✓ በእናት ድርጅታቸው ለሁሉም አባላት የሚቀርቡና ከላይ የተዘረዘሩት ግብዓቶች ለወጣት ሊግ አባላቱም እንዲደርሷቸው ይደረጋል።

- ✓ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በልዩ ሁኔታ የሊግ አመራሮችንና አባላቱን የአስተሳሰብ አድማስ የሚያሰፉ፣ በተግባር ውጤታማ ሆነው ህይወታዊና ቁሳዊ መሻሻል የሚያመጡና ለሌሎች ወጣቶች ምሳሌ መሆን የሚያስችሉ የሰነድና የቁሳቁስ ድጋፎች በሊግ ጽ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ጋር ተሳስሮ የሚቀርብበት ሁኔታ ይታያል፡፡
- ✓ በየአካባቢው ራሳቸው የሊግ አባላቱም በተነሳሽነትና ፈጠራን ጨምረው ለውጥ ለማስመዝገብ መረባረብ ይገባቸዋል፡፡

**ግብ 4 የሴቶች ሊግ አመራሮችን አባላትን ውጤታማነትና ስኬታማነት የማረጋገጥ ተልዕኮ**

እንደ ወጣቶች ሊግ ሁሉ፣ የሴቶች ሊግ አመራሮችና አባላት በ2010 የእቅድ ዘመን በየተሰማሩባቸው መስኮች ውጤታማ የሚሆኑበት አግባብ፣ በእናት ድርጅታቸው የአመራርና የአባላት ተግባራት ላይ ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሴቶች ሊግን የተመለከቱ ተጨማሪ የእቅድ ጭብጦች ቀርበዋል፡፡

**ሀ/ የሴቶች ሊግ አመራሮችንና አባላትን አስተሳሰብ በ2010 እቅድ ውጤታማ በሚሆኑበት ሁኔታ ማሳደግ**

- ✓ የሴቶች ሊግ የአመራሮችና የአባላት ጥራትና ቁጥር አዳዲስ ጠንካራና ተኪ ኃይሎችን ጨምሮ፣ ኮር የሊግ አመራሮችና ኮር አባላትን መፍጠርና መገንባት፡፡
- ✓ የሴቶች አደረጃጀቶች መሪዎች ወደ ሌላ መዋቅር መሸጋገሪያ አድርገው የመመልከት ሁኔታን በመስበር፣ የአደረጃጀት መሪ መሆን ትልቅ ፀጋና ሁነኛ የመታገያ መድረክ በመሆኑ ጉዳይ ላይ መተማመን፡፡ የሊግ አመራሩን አምነው በመስኩ ለውጥ የሚያመጡ አመራሮችን ማበራከት፤
- ✓ ለሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ትክክለኛው ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ነው፡፡ አፍራሽ ኃይሎችን የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት የሚጎዱ እንቅስቃሴዎችን ተደራጅተው የሚታገሉበትና ጥቅሞቻቸውን የሚያስጠብቁበት ማዕከል የሚሆኑበትን አስተሳሰብና ዝግጁነት ማጎልበት፡፡
- ✓ የሴቶችን ዘርፈ ብዙ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች በሚፈታ አግባብ ውጤታማ የአመራርና የአባላት ንቅናቄ ይካሄዳል፡፡ በትምህርትና በጤና ልማት መስኮች፣ በግብርናና በአነስተኛና ጥቃቅን የስራ ዘርፎች፣ በፖለቲካው መስክ የቀበሌና የወረዳ ምክር ቤቶች ምርጫ ብቃት ያላቸውን የሴት እጩዎች በማቅረብና በሌሎችም የሊግ አባላቱ ግንባር ቀደምና ውጤታማ እንቅስቃሴ በማካሄድ በመላ ሴቶች ላይ አወንታዊ ተጽዕኖ እንዲኖራቸው ማስቻል፡፡

**ለ/ የሴቶችን የእቅድና የአፈፃፀም የእውቀትና ክህሎት ማሻሻልና ውጤታማነትን ማሳደግ**

- ✓ የሴቶች ሊግ መነሻ እቅድ የሚመለከታቸው ተሳትፈውበት ይዘጋጃል፡፡ በእቅዱ ላይ በየደረጃው ውይይት በማካሄድ ከምርጥ አስተቃቀዶች፣ በአንፃሩ ከሚታዩ ድክመቶች ትምህርት ይወሰዳል፡፡
- ✓ ምርጥ አስተቃቀድና ውጤታማ ስራ የተሰራበት እቅድ በሞዴልነት ተመርጦና በዛ ላይ ተመስርቶ የወልና የግል እቅዶች ይዘጋጃሉ፡፡
- ✓ በየደረጃው በእቅዱና አግባቦቹ ላይ መላ የሊጉ አባላት ግልጽነት እንዲይዙ ይደረጋል፡፡
- ✓ በቀጣይነትም ክትትልና ድጋፍ ይካሄዳል፡፡ የክትትልና ድጋፉ ማዕከላዊ ነጥብ የአፈፃፀም ውጤታማነትን ማረጋገጥ፣ ምርጥ ተሞክሮን ቀምሮ ማስፋፋትና ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም ውጤታማ የሴቶች አደረጃጀቶችንና የተሳካላቸውን ሴቶች አባላትና አመራሮች ሞዴልና ኮር እንቅስቃሴ በአግባቡ ተቀምሮ፣ ወደ ሌሎች በማስፋፋት አፈፃጸሙን መከታተልና መደገፍ አንድ የግንባታ መስክ መሆን ይኖርበታል፡፡

**ሐ/ የሴቶችን ሊግ አደረጃጀትና አሰራር ጥንካሬና ውጤታማነት ማረጋገጥ**

- ✓ አደረጃጀቶቹ እቅድን የመፈፀምና ውጤታማ የመሆን የአደረጃጀት የብቃት ደረጃ ላይ መድረስ ይኖርባቸዋል። በተለይም በወረዳና በቀበሌ እንዲሁም የልማት ቡድን አደረጃጀቶቹ፣ በአንፃራዊነት ጥሩ እንቅስቃሴ ያላቸውን ሞዴሎች በመውሰድ፣ ሌሎቹ ወደ ምርጦቹ የአደረጃጀት ደረጃ እንዲደርሱ ጥረት ይካሄዳል።
- ✓ ኮር የሴቶች አመራርና አደረጃጀት መገንባት፣ ይህንኑ ወደ ሌሎች ማስፋት፣

**መ/ በየአደረጃጀቶቹ የሚቀርቡ ግብዓቶችን በውጤታማነትና የሴቶችን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጡበት አግባብ መፈፀም**

- ✓ ለጠቅላላ አመራርና አባላት የሚቀርቡ ግብዓቶች፣ የሴቶች ሊግ አባላትም የሚጠቀሙባቸው ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ በሊጉ በኩል የሚቀርቡ ግብዓቶች ተለይተው፣ራሳቸውን የቻሉ ግብዓቶች በታቀደ መንገድና ወቅቱን ጠብቀው መቅረባቸውና በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸው ይረጋገጣል።

**ግብ5. የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤቶችን የተደራጀ ንቅናቄና ውጤታማነት በማሳደግ የሚከናወኑ ተግባራት**

- ✓ ምክር ቤት አባላቱ የህዝቡን የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ አጀንዳዎች ይዘው ተቋሙን የሚታገሉበትና ውጤታማ የሚሆኑበት አስተሳሰብ ይፈጠራል።
- ✓ የምክር ቤት አባላቱ ተልዕኳቸውን ተገንዝበውና የምክር ቤት አባላት እንዲይዙት የሚገባው እውቀት ይዘው፣ በግል የስራ ስምሪታቸውና በምክር ቤቶቹ አወንታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩበት እቅድ ያዘጋጃል። በእቅዱ መሰረት የስምሪት፣የክትትልና ድጋፍ እንዲሁም ተሞክሮዎችን የማለዋወጥ ስራ ይሰራል።
- ✓ የቀበሌና የወረዳ ምክር ቤቶች እጩዎች ዝግጅት፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሁም ህዝባዊ አመኔታን ያተረፈ የምክር ቤቶች አባላት ምርጫ በሚካሄድበት ሁኔታ፣ ራሱን የቻለ እቅድ፣ ግልጽ ኦረንቴሽንና ፈፃሚን የማብቃት ስራ፣ ከዛም የክትትልና ድጋፍ ተግባራት ራሳቸውን ችለው ያዘጋጃሉ፤ የዴሞክራሲ ግንባታን በሚያሳልጥ አግባብም ይተገበራል።
- ✓ የምክር ቤቶችን አደረጃጀቶች ማጠናከር፤ ምክር ቤት አባላት ከእናት ድርጅታቸው ጋር ያላቸው የመሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ አደረጃጀት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በራሳቸው በምክር ቤቶቹ ውስጥ ያሉ አደረጃጀቶች ወቅታቸውን ጠብቀው ተልዕኳቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ማስቻልና ውጤታማ አደረጃጀትን የማረጋገጥ ሥራ ይከናወናል።
- ✓ የግብዓት አቅርቦትን በተመለከተ፤ በተወካዮችና በዋናነት ደግሞ በክልል ምክር ቤት መቅረብ ያለባቸው መመሪያዎችና አሰራሮች በሚመለከታቸው መቅረባቸውን ማረጋገጥ።
- ✓ ለወረዳና ለቀበሌ ምክር ቤቶች አባላት ከእጩ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ምርጫ ቅስቀሳ እንዲሁም የምርጫ ሂደትና ውጤት ድረስ መቅረብ የሚገባቸው ግብዓቶች እንዲቀርቡ ራሱን በቻለ እቅድ እንዲመለስ ይደረጋል።

**ግብ 6 የተከለ ኢህዴን ራስ አገዝ አባላትን በአስተሳሰብና በአደረጃጀት ማጠናከርና በተግባር ውጤታማ ማድረግ**

- ✓ የማህበሩ አባላት ከጠባቂነትና ከተረጅነት አስተሳሰብ ተላቀው ከማህበሩ የሚያገኙትን መነሻ ምክርና ድጋፍ ይዘው፣ በራሳቸው ጥረት የሚሻሻሉበትን አስተሳሰብ ማስያዝ፣ ውጤታማ ከሆኑት ምርጥ ተሞክሮዎችን ወስዶና ቀምሮ በማስፋፋት የተግባር መመሪያ በሚሆኑበት ደረጃ ማጠናከር።

- ✓ ማህበሩ እንደማህበርና አባላቱ ውጤታማ በሚሆኑበት ደረጃ እቅድ ይዘጋጃል፡፡ እቅዱ ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን አባላትንና የተጠናከሩ አደረጃጀቶችን ለይቶ፣ ከነዛ ትምህርት በሚወሰድበት አግባብ የሚደራጅ ይሆናል፡፡ የአፈፃጸም ክትትልና ድጋፍ እንዲሁም ምርጥ ተሞክሮዎችን የመቀመርና የማስፋፋት ሥራ በትኩረት ይሰራል፡፡
- ✓ ማህበሩና ቅርንጫፍ አደረጃጀቶቹ ተጠናክረው አባላት ምዝገባን፣ የተግባቦትና የአደረጃጀት ስራን በሚያከናውኑበት ሁኔታ ይጠናከራሉ፡፡
- ✓ የሰማዕታት ኃውልትና ሌሎች የትግሉ ስፍራዎች ጥበቃና እንክብካቤ በሚያገኙበት ሁኔታ መስራት፡፡
- ✓ በብአዴን መዋቅር ከሚቀርቡት የሰነድና ሌሎች የአቅም ግንባታ ግብዓቶች ባሻገር፣ በማህበሩ በኩል የሚቀርቡ ግብዓቶች አስቀድመው በእቅድ ውስጥ ተይዘው በወቅቱ መቅረባቸው ይረጋገጣል፡፡
- ✓ ከሁሉ በፊት ማህበሩ አባላቱን ማንቀሳቀስ እንዲችሉ፣ በየተቋማቱ የሚገኙ የብአዴን አደረጃጀቶች መደገፍ ይኖርባቸዋል፡፡
  - የተመላሽ ሰራዊት አደረጃጀቶችን በማጠናከር በሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች እንደሚካሄደው ሁሉ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት እንዲሁም የታቀደ የለምና ንቅናቄ ማካሄድ፡፡

**ግብ 7 የሲቪል ሰርቪሱን ችግር ፈችነትና ውጤታማነት ማሳደግ**

**ሀ/ በአስተሳሰብ ችግር ፈችነትንና ውጤታማነትን ማሳደግ**

- ✓ የኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም ጠቅላላ የትምህርት ተቋማት መምህራንን ጨምሮ፣ ሲቪል ሰርቪሱ በሁኔታ ግምገማው የተለዩ ችግሮችን ውጫዊ የማድረግ፣ከዴሞክራሲያዊ አንድነት አብሮነትን የሚፈታተኑ የተዛቡ አስተሳሰቦችን የሚያስተካክሉና ዴሞክራሲያዊ አንድነትን የሚያጎለብቱ የውይይት መድረኮችን ማደራጀትና ቀጣይነታቸውን ማረጋገጥ፡፡ ሙያዊ አገልግሎት መስጠት የክብሩና የእርካታ ምንጭ ያልሆነበትን ሁኔታ የሚይቀሩና የለውጥ ኃይል መሆን የሚያስችሉትን የግምገማ፣በእቅድ ዝግጅት የማሳተፍ እንዲሁም በአፈፃፀሙ ላይ ግልጽ የስራ ክፍፍል በማካሄድ ለውጥ እንዲያመጡ የማድረግ ተግባራት በሁሉም ተቋማትና በየደረጃው ይከናወናሉ፡፡
- ✓ ሲቪል ሰርቩሱ ከዋናው ተልዕኮ መውጣት ሳይሆን፣ የራሱንና  የህብረተሰቡ ዋነኛ ጠላት የሆኑትን ድህነትንና ኋላቀርነትን በመዋጋት ላይ በማተኮር፣ ሙያዊ ችሎታውን ተጠቅሞ የህዝቡን ችግሮች እንዲፈታ መተማመንን ማጎልበት፡፡ ግልጽ የስራ ክፍፍልን፣ የውድድር መንፈስና እምነት በማጎልበት ወደ እድገትና ለውጥ ሒደት ማስገባት፡፡
- ✓ በ2010 ዓ.ም ቁልፍና አበይት ተግባራት ዙሪያ ከአመራሩና ከህዝቡ ጋር ግንባር በመፍጠር እንዲሁም ሙያዊ አገልግሎቱን በኃላፊነት መንፈስ በማበርከት ምርታማነትንና የአገልግሎት ጥራትን የማረጋገጥ ዝግጁነት ቀጣይ ታታሪነትን እንዲሁም ውጤታማነትን ማሳደግ፡፡

**ለ/ የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኛውን በእቅድ የመምራት እውቀትንና ክህሎትን ማጎልበት**

- ✓ እውቀት (ሙያዊ አገልግሎት)፣ ጊዜና ገንዘብ እንዲሁም ሌሎች ግብዓቶች በአግባቡ ታቅደው፣ የላቀ ውጤታማነትን በሚያረጋግጡበት መልኩ ስራ ላይ መዋል እንዳለባቸው ይታወቃል፡፡ የ2010 ዓ.ም በየተቋማቱና በየደረጃው የሚከናወኑ የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲ ተግባራት ባለሙያዎች በቂ ተሳትፎ አካሂደውበት የሚታቀድና ጥረት የተደረገበት እንዲሆን ይጠበቃል፡፡

- ✓ በእቅድ ዝግጅት ብቻ ሳይሆን፣ በእቅዱ ላይ መግባባትንና እምነትን ማሳደግ፣ በአፈፃፀም ሂደትም ሙያዊ ክትትልና ድጋፍ እንዲሁም የተሞክሮዎች ልውውጥ መረጋገጥ ይኖርበታል። በሂደቱ ምርጥ አፈፃፀም ያሳዩ ተሞክሮዎቻቸው የሚስፋፋበትን አሰራር አጠናክሮ መቀጠል ይገባል። በሂደቱ የተሻሉትን መርጦ እውቅናና ሽልማት በመስጠት ውድድርን ማበረታታት።

**ሐ/ የሲቪል ሰርቪሱን አደረጃጀትና አሰራር የላቀ ውጤታማነትን በሚያረጋግጥ አግባብ ማጠናከር**

- ✓ በርካታ የለውጥ ፕሮግራሞችና አሰራሮች በትምህርት ቤቶችም ሆነ በቢሮዎች ተግባራዊ እየሆኑ እንደሆነ ይታወቃል። የለውጥ ፕሮግራሞቹና አሰራሮቹ በውጤታማነት ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት፣ የተቀመጡት አደረጃጀቶች በትክክል ተግባራዊ ሲሆኑ ብቻ ነው።
- ✓ በተለይም ደግሞ የልማት ቡድንንና የአንድ ለአምስት አደረጃጀቶችን በማጠናከር የአፈፃፀም ግምገማ፣ የደረጃ ልየታና ጥሩ አፈፃፀም ያላቸው የደከሙትን በሚያጠናክሩበትና ልምዳቸውን ሊያስተላልፉ በሚችሉበት አግባብ ማጠናከር ጉዳይ በትኩረት መስራት ይኖርበታል።

**መ/ የግብዓት አቅርቦት ውጤታማነት**

- ✓ የሲቪል ሰርቪሱን የአስተሳሰብ አድማስና ዝግጁነት የሚያጠናክሩ መወያያ ጽሁፎች፣ የእቅድ መነሻዎችና የአፈፃፀም ግምገማ መነሻ ሰነዶች፣ የስራ ማስፈፀሚያ ቁሶች በየደረጃውና በየተቋማቱ ወቅታቸውንና አቅም በፈቀደ መጠንም ጥራታቸውን ጠብቀው እየቀረቡ መሆናቸው መረጋገጥ ይኖርበታል።

**ግብ 8 የከተማውን ህዝብ ምርታማነት የሚያሻሽሉና ሰላማዊና ልማታዊ አቅጣጫን የሚያጠናክሩ ንቅናቄዎችን ማረጋገጥ**

- ✓ በከተሞች በመንግስትና በግል ድርጅቶች ተቀጥሮ ከሚሰራው የህብረተሰብ ክፍል ውጭ የጥቃቅን አንቀሳቃሾችን፣ መካከለኛ ባለሀብቶችን፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚያካትት እንደሆነ ይታወቃል።

ሀ/ ጥቃቅን መካከለኛ አንቀሳቃሾችን በአስተሳሰብ ደረጃ በየተሰማሩበት መስክ ውጤታማ ማድረግ። አንቀሳቃሾች ከጠባቂነትና ችግሮቹን ውጫዊ እያደረጉ ስርዓቱን ከማማረር ተላቀው፣ ውጤታማና ምርታማ እንቅስቃሴ እንዲያካሂዱ ማስቻል።

- ✓ ከ2009 ዓ.ም የአንቀሳቃሾች እቅድ አፈፃፀም አወንታዊና አሉታዊ ውጤታማነት የሚወሰዱ ትምህርቶችን መውሰድ። በአስተሳሰብ ደረጃ ከመንግስትና ከቤተሰብ የሚገኝ ድጋፍ በተወሰነ ደረጃ መነሻ አቅም ካልሆነ በስተቀር ወሳኙ አቅም በራሳቸው በአንቀሳቃሾች ውስጥ የሚገኝ መሆኑን በማስያዝ፣ ለቀጣይ ውጤታማነት የአስተሳሰብ አድማሳቸው የሚያድግበትንና በተነሳሽነት ወደ ስራ የሚገቡበትን ሁኔታ መፍጠር።
- ✓ አንቀሳቃሾች ጥቅሞቻቸው ሊረጋገጡ የሚችሉት በልማታዊ ዴሞክራሲ አማራጮች እንጂ፣ በጥገኛ አማራጭ ሊረጋገጡላቸው አይችሉም። በመሆኑም ከጥፋት ኃይሎች አፍራሽ ቅስቀሳ ራሳቸውን ጠብቀው፣ በተያያዘ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ የለውጥ ጎዳና እንዲደግፉ የአስተሳሰብ ግልጽነትንና መተማመንን መገንባት።
- ✓ አንቀሳቃሾቹ በየተሰማሩበት መስክ ሁሉ፣ ማዕከላዊ ርብርባቸው ምርታማነትንና ውጤታማነትን ማሳደግ ላይ መሆን ይኖርበታል። ለዚህም ደግሞ የጊዜና የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን የሚያሻሽሉ አሰራሮችንና

ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡና በውጤታማነት መጠቀም እንዲኖርባቸው መተማመን ላይ መድረስ። በዚህ ሂደት አባላት ግንባር ቀደም አመራር በሚሰጡበት ሁኔታ ድጋፍ ማስረገጥ።

- ✓ ነባር አንቀሳቃሾች ከደረጃ ወደ ደረጃ በሚሸጋገሩበት አግባብ ከዩኒቨርሲቲ፣ ከኮሌጆች እንዲሁም ከታችኞቹ የትምህርት ተቋማትና በጥቃቅንና አነስተኛ መስክ ለሚሰማሩት፣ የሚሰማሩባቸው መስኮች ተለይተው የግንዛቤ ፈጠራ፣ እንደየ ዝንባሌያቸው አጫጭር ስልጠናዎችና ስምሪቶች በመደበኛነት ታቅደው የሚፈፀሙ ይሆናሉ (ዝርዝሩ በሚመለከተው መስሪያ ቤት ይዘጋጃል።)

ለ/ የአንቀሳቃሾች የወልና የግል እቅድ ዝግጅት ምርታማነትን፣ ውጤታማነትንና ቀጣይ ታዳጊነትን የሚያረጋግጥ ይሆናል።

- ✓ የ2010 የአንቀሳቃሾች እቅድ ዝግጅት፣ ምርጥ አፈፃፀም ያላቸውና ምርታማ የሆኑትን አንቀሳቀሾች ሞዴል በመውሰድና ይህንኑ በአግባቡ በመቀመር ላይ የተመሰረተ ይሆናል።
- ✓ በሞዴል እቅዱ ላይ ተመስርቶ፣ ምርታማነትንና ውጤታማነትን ማዕከል ያደረገ የተግባቦትና የመተማመን ስራ ይካሄዳል።
- ✓ በተፈጠረው መነሻ መግባባት ላይ ተመስርቶ፣ ሁሉም አንቀሳቃሾች ኢንተርፕራይዞቻቸውን የተመለከተ የወል እቅድና እያንዳንዱ አንቀሳቃሽ ደግሞ የግል እቅድ እንዲያዘጋጅ ይጠበቃል። በእቅድ ዝግጅቱ ሂደት ከመካከላቸው ሞዴል እቅድ እየቀረበ አንቀሳቃሾቹ አስተያየት እየሰጡበት ይጎለብታል።
- ✓ አፈፃፀሙ በቀጣይነት ክትትልና ድጋፍ ይደረግለታል። የክትትልና ድጋፍ ስርዓቱ ሶስት ውጤቶች የሚጠበቁበት ይሆናል። የመጀመሪያው የአንቀሳቃሾቹ የወልም ሆነ የግል እቅድ ምርታማነትንና ውጤታማነትን እያመጣ መሆንና አለመሆኑ፣ ካልሆነ ለምን? የሚሉትን እየመለሰ የሚያጠናክር ይሆናል። ሁለተኛው ውጤት ምርጥ ተሞክሮዎችን ከየአንቀሳቀሾቹ በመውሰድ ወደ ሌሎች በአግባቡ የማስፋፋት (Scaling-up) የሚባለው ይሆናል። ሦስተኛ በአፈፃፀሙ የተሳካላቸውንና ምሳሌ የሆኑትን አንቀሳቃሾች ለይቶ እውቅና መስጠትና ማበረታታት ይሆናል።
- ✓ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ከኮሌጆችና ከታችኞቹ የትምህርት ተቋማት የሚወጡትን ምሩቃኑንና እየተደራጁ በአንቀሳቃሽነት የሚሰማሩ ኃይሎችን በተዘረጋው የአንቀሳቃሾች የስምሪት መስክና የእድገት መሰላል መሰረት የግንዛቤ፣ አስተሳሰብ ስራ በመስራት ማደራጀት። የተደራጁት አንቀሳቃሾችደ እንደ የአግባቡ የክህሎትና የእውቀት ስልጠና በመስጠት አደራጅቶ የማሰማራት ሂደቱ በትኩረት ይከናወናል። (ዝርዝሩን በተመለከተ የሚመለከተው መስሪያ ቤት በሚዘጋጀው እቅድ የሚመለስ ይሆናል።)

### ሐ/ የአንቀሳቀሶችን አደረጃጀት ማጠናከር

- ✓ የአንቀሳቃሾች አደረጃጀቶች ከሚያንቀሳቅሷቸው የምርት ወይም የአገልግሎት ተቋማት ጋር የተያያዙ የስራ አደረጃጀቶች ናቸው። አደረጃጀቶቹ ሰላማዊና ምርታማነትንና ውጤታማነትን የሚያሳድጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ። በአንቀሳቃሾቹ ሙሉ ፈቃድ የአደረጃጀቶቹ ጉድለቶች በድርጅት አባላት ግንባር ቀደም እንቅስቃሴ፣ ሙያዊና የአመራር ምክረ ሀሳብ መሰረት መስጠት የሚታረሙበትና የሚጠናከሩበት ሁኔታ በትኩረት የሚፈፀም ይሆናል።

### መ/ አንቀሳቃሾችን ውጤታማና ምርታማ የሚያደርግ የአቅርቦትና የገበያ ትስስር

በ2010 እቅድ በመንግስት ሊቀርብ የሚችል ድጋፍ ካለ፣ በጥቅል ሳይሆን ለየአንቀሳቃሶቹ አንድ በአንድ ሊቀርብ የሚችለውን አስቀድሞ በግልጽ ማቅረብና ከመንግስት ሊቀርብ የማይችለውን አንቀሳቃሾቹ እንደማይቀርብ አውቀው በራሳቸው አቅም እንዲንቀሳቀሱ ግልጽነት መያዝ። (ዝርዝሩ በሚመለከተው ተቋምና በየደረጃው የሚፈፀም ይሆናል)

የገበያ ትስስር፤ አንድ ቁልፍ ግብዓትና ለውጤታማነትና ለምርታማነት ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህንኑ ታሳቢ ያደረጉ ግልጽነትንና መተማመንን መፍጠር ይጠይቃል። የአንቀሳቃሾች የምርት እንቅስቃሴ፣ የገበያ ትስስር በሌለበት ለእድል የሚተው ሊሆን አይገባውም።

## 6.2 የመካከለኛና በተወሰነ ደረጃን የከፍተኛ ባለሀብቶች የአስተሳሰብ ግልጽነትና ውጤታማነት በሚሻሻልበት ሁኔታ መደገፍ

### ሀ/ በአስተሳሰብ ደረጃ ባለሀብቶች በልማታዊነት ጎዳና ተንቀሳቅሰው ውጤታማ እንዲሆኑ ማስገንዘብ

- ✓ ባለሀብቶች ምርታማና ትርፋማ የመሆን አስተሳሰብና ህልም እንዳላቸው ግልጽ ነው። ይሁንና በዘላቂነት ምርታማና ትርፋማ በሚያደርጓቸው መስኮች ላይ የሚስተዋሉ ግራ መጋባት፣ ህጋዊነትና ህገ ወጥነት ተደማምረው የሚታዩበት ዝንባሌ እንዳለ ይታወቃል። ባለሀብቶቹ ችግሮችን ውጫዊ ከማድረግ፣ ስርዓቱን ከማማረርና በሁሉም መስኮች ፍትሃዊ እድልና የተመቾ የስራ ሁኔታ እንደሌለ አድርጎ ከማሰብ ወጥተው፣ በልማታዊና ህጋዊ ጎዳና ራሳቸውንና አገራቸውን እንዲጠቅሙ ችግሮችን ተቀራርቦ በመወያየት እንዲፈቱ በሚያስችል አስተሳሰብ ላይ መተማመን።
- ✓ በ2009 ዓ.ም የእቅድ አፈፃፀምና በ2010 እቅድ መነሻ ሀሳቦች ላይ ተመስርቶ፣ ከመካከለኛና ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም ከከፍተኛ ባለሀብቶች ጋር የጋራና በየዘርፉ አደረጃጀቶች እንዲሁም በቅርቡ ከተቋቋመው አባይ አክሲዮን ማህበር ጋር መግባባትና የጋራ ስምምነት መያዝ።
- ✓ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ባለሀብቶች አሁንም ህጋዊና ህገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች ተጣምረው የሚታዩባቸው ናቸው። መሬት አጥረው የተቀመጡ፣ በተወሰነ ደረጃ ግንባታ ጀምረው ያቆሙ፣ የተወሰኑና መጠነኛ ግንባታ ካካሄዱ በኋላ ላልተገባ ዓላማ ያዋሉ፣ የተወሰኑት ምርታማ በሆኑ መስኮች ላይ ከመሰማራት ይልቅ በአቋራጭ ብር ስለሚያስገኝቸው ብቻ አሸዋና ድንጋይ እንዲሁም አፈር እየሸጡ ባለሀብት የሚባሉ ግለሰቦች እንዳሉ ይታወቃል። በ2010 እቅድ እነዚህ ችግሮች ከመሰረታቸው ዝንባሌያቸው ተስተካክሎ ሁሉም ምርታማ በሆኑ መስኮች እንዲሰማሩ መተማመን።
- ✓ በአባይ አክሲዮ ማህበር አማካኝነት መፈጠር የጀመረው የባለሀብቶችና የመንግስት ጥምረት፣ ለዓመታት በድርጅታችን ውስጥ ሲነሳ የነበረው ፖለቲካዊ አስተሳሰብ በተግባር እውን መሆን የጀመረበት ተደርጎ ይወሰዳል። ይሁንና ማህበሩ ውጤታማ እንዲሆንና ቶሎ ወደ ስራ ገብቶ ህልሙ እውን እንዲሆን፣ የተጠናከረ የአስተሳሰብና የቅንነት ግንባታ መካሄድ ይኖርበታል።
- ✓ የአባይ አክሲዮን ማህበር አይነት ብዙ አክሲዮኖች ያስፈልጉናል። ይህ ክልላዊ ምሳሌ ሆኖ ቢያንስ በዞንና በወረዳ ማዕከላት ሀብታም አርሶ አደሮችንም የሚያሳትፉ ማህበራት ተባዝተው፣ በርካታ መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የሚስፋፋበትን ሁኔታ ማረጋገጥን በአስተሳሰብ ይዘን የምንሰራበት ሊሆን ይገባል።
- ✓ በባለሀብቱ ውስጥ ልማታዊነትና ህጋዊነት እንዲሰፍኑ፣ በአንፃሩ ደግሞ ኪራይ ሰብሳቢነትና ህገ-ወጥ ተጠቃሚነት እንዲከስሙ በቀጣይነት መስራት።

### ለ/ የባለሀብቱን ምርታማና ውጤታማ የማቀድ እውቀትና ክህሎት መገንባት

- ✓ መንግስት ባለሀብቶችን ሊደግፍ የሚችለው የተሻሻሉ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅሞ ጥራት ያላቸውና፣ ምርታማ የሚያደርጉ ስርዓቶች ላይ እውቀትንና ክህሎትን በማስፋፋትና በመደገፍ ነው። የተሞክሮ ልውውጥ መድረኮችን በማደራጀት ነው። በመሆኑም ከባለሙያዎች ጋር በመነጋገር ምርታማነትን የሚያሻሽሉ የእቅድ ሀሳቦች ላይ መግባባት። በምርታማነታቸው የተሳካላቸውን ኩባንያዎች ተሞክሮዎች መቀመርና ማስፋፋት፣ ውጤታማ የሆኑትን እውቅና መስጠት ውድድርን ማሳደግ።

### ሐ/ የባለሀብቱ አደረጃጀትና አሰራር ምርታማና ውጤታማ እንዲሆን ማስቻል

- ✓ ባለሀብቶች በተሰማሩባቸው የንግድና ዘርፍ ማህበራት፣ በአክሲዮኖች እንዲሁም በፋብሪካዎች ውስጥ ባሉ አደረጃጀቶች ሰላማዊ፣ምርታማነትን የሚያሻሽሉ አዳዲስ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን በማስፋፋት አደረጃጀቶችን ማጠናከር።
- ✓ ከምርታማነት መሻሻል አንፃር፣ አስተዋጽኦና ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን አደረጃጀቶች በመቀመር፣ተሞክሮዎቻቸውን ወደ ሌሎች ተቋማት እንዲሁም ወደ የንግድና ዘርፉ ማህበራት ማሸጋገር።
- ✓ የገበያ ትስስር አደረጃጀቶችን በተመለከተም አምራቾች፣ አከፋፋዮች ቸርቻሪዎችና የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት ከሚመለከታቸው ጋር ጤናማና የሰመረ የገበያ ትስስርና አደረጃጀት በመፍጠር ማጠናከር።

## 6.3 ሌሎች ከከተማ ኗሪዎች ጋር የሚሰሩ የሰላም፣የልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ ተግባራት

- ✓ ከአንቀሳቃሾችና ከባለሀብቶች ባሻገር፤ በከተሞች በልዩ ልዩ መስኮች ተሰማርተውና በግል ድርጅቶች ተቀጥረው የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች አሉ። ከተቋም ሰራተኛነትና ከግል ስምሪቶች ባሻገር፣ በከተማ ኗሪነታቸው የከተማው ሰላም፣ የመሰረተ ልማት፣ የማህበራዊ አገልግሎት፣ የመልካም አስተዳደር ጉዳዮችና ሌሎችም ያሳስቧቸዋል። እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች በኗሪነት የአደረጃጀት መስኮች የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ በሚያካሂዱበት አግባብ አቅደን መንቀሳቀስ ይገባናል።

### ሀ/ በሰላም፣ በልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ ላይ ተሳታፊነትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ

- ✓ በግልና በአካባቢ እንዲሁም በከተሞች ሰላማዊ ሁኔታ ላይ ተሳታፊነትን በማረጋገጥ ሰላማቸውንና ደንነታቸውን በጋራ የመንከባከብ እምነትን ማሳደግ። በተሳሳተ መረጃ ላይ ተመስርቶ የሚፈጠርን ግራ መጋባት የሚፈታ ግንኙነት በመገናኛ ብዙሃንና በገጽ ለገጽ ውይይት በየእርከኑ ይፈጠራል።
- ✓ በመሰረተ ልማት፣ በመንገድ፣ በአካባቢ ንጽህና፣ በትምህርትና በጤና ልማት ዙሪያ ልዩ ልዩ በማዘጋጀት አቅሙን መገንባት፣ በማካሄድ በፀረ-ሙስና ንቅናቄው ላይም ንቁ ተሳትፊ በመሆን የተበላሹ አሰራሮችን የሚያስወግድበትን ሁኔታ መፍጠርና በቀጣይነት ማረጋገጥ።
- ✓ ህብረተሰቡን በዓመታዊ እቅዱ ላይ እውቀት ማስያዝና ድርሻቸውንም እንዲወጣ ማስቻል።

### ለ/ በዓመቱ የእቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም ላይ የኗሪዎችን ተሳታፊነት ማረጋገጥ

- ✓ ኗሪዎቹ የ2009 አፈፃፀም ግምገማን ያካሂዳሉ። በ2010 እቅድ ላይ በተቋማት እቅድና በተሳትፏቸው ሂደት ግልጽ አስተሳሰብ ይይዛሉ።

- ✓ የኑሮ ውድነት ችግሮች፣ ከመሸመት አቅም ማነስ ጋር የተያያዘውን ገጽታ የህብረተሰቡ የኑሮ መሻሻል ከግልና ከወል ጥረት ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ፣ ተሞክሮዎች እየቀረቡና ውይይት እየተካሄደባቸው ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት የሚያዝበት ሁሉም ህገ-ወጥነትን እየታገለ በግልና በወል ጥረቶች ኑሮውን የሚያሻሽልበትን የዝግጁነትንና የተሞክሮዎችን ልውውጥ ማስፋፋት።
- ✓ በ2010 የወረዳና የቀበሌ ምርጫ፤ የልማትና ለመልካም አስተዳደር አገልግሎት አስተዋጽኦ ያላቸው የምክር ቤት አባላት ምርጫ በነቃ ተሳትፎ ይረጋገጣል።
  - ✓ ዓመታዊ የእቅድ ሀሳቦች ይቀርባሉ፤ በህብረተሰብ የወልና የግል ጥረቶች ላይ በቀበሌው ወይም በየከተማው የተሻሉ ተሞክሮዎች ተቀምረው ይቀርባሉ።
  - ✓ ምርጥ ተሞክሮዎች ተቀምረው በቀረቡበት ሁኔታ፣ ህብረተሰቡ ተሞክሮዎችን እንዲወስድና በግል ህይወታዊ ለውጥም ሆነ በወል ልማት ላይ ተሳትፎና ጥረት እንዲኖረው የሚያስችል እቅድ ይዘጋጃል፤ ስምሪትም ይካሄዳል። የኑሮ ውድነትን መቋቋም የሚያስችሉ የገቢ ማሻሻያ ተሞክሮዎች ተቀምረው ህብረተሰቡ በአማራጮች ላይ ውይይት አድርጎ፣ የራሱን ጥረትና ፈጠራ የሚጨምርበት አካሄድም መታየት አለበት። በቀጣይነት አፈፃፀሙ በየአደረጃጀቶች እየተገመገመ የማጠናከር ስራ ይሰራል።

### ሐ/ ከአደረጃጀትና ከአሰራር አኳያ

- ✓ ከከተማው ህብረተሰብ መካከል የሴቶችና የወጣቶች እንዲሁም የሸማቾች ማህበራት እንዳሉ ይታወቃል። የአደረጃጀቶቹ አባላት በቁጥር ጥቂትና ጥንካሬያቸውም ዝቅተኛ እንደሆነ ይታወቃል። የእነዚህ አደረጃጀቶች በጋራ ጉዳዮች ላይ ማለትም በልማትና፣ በዴሞክራሲ ግንባታና በሰላም ማስከበር በጋራ ተቀራርቦ መስራት፣ የ2010 የእቅድ ትኩረት ነው።
- ✓ በቅርቡ የተጀማመሩ የልማት ቡድን አደረጃጀቶች አሉ። የቡድን አደረጃጀቶቹ በሰፈር ደረጃ ያሉ ችግሮችን ዘርዝረው ከለዩ በኋላ፣ በራሱ በህብረተሰቡ የየአካባቢው አመራር ጣምራ ጥረት የመፍታት እንቅስቃሴ ይካሄዳል፤እነዚህን የቡድን አደረጃጀቶች በማጠናከር በህብረተሰብ አደረጃጀት ሊፈቱ የሚችሉና በየሰፈሩ ህዝቡን የሚያበሳጩ የፀጥታ፣ የመሰረተ ልማትና ተጓዳኝ ችግሮችን መፍታት ይሆናል። ማዕከላዊ ትኩረቱ በተግባር ላይ የተመሰረተ የአደረጃጀትቶች ግንባታ ይሆናል።

### መ/ ከግብዓት አቅርቦት አኳያ

በየከተሞቹና በየክፍለ ከተሞቹ እንዲከናወኑ የተያዙ የወል ፕሮጀክቶችንና ከህዝቡ የሚጠበቀውን ለይቶ አስቀምጦ፣ ሁሉም የድርሻቸውን አስተዋጽኦ በማድረግ የህዝቡ የተደራጀ ንቅናቄ በተጨባጭ ግብዓት ተደፍፎ እንዲንቀሳቀስ በታችኞቹ መዋቅሮች በዝርዝር ይታቀዳለሉ። ክልልና ዞን አፈፃፀሙን ተከታትለው መደገፍ ይኖርባቸዋል።

## ግብ 9 የአርሶ አደሩን ምርታማነትና የኑሮ መሻሻል ማሳደግ

### ሀ/ የአስተሳሰብ ግንባታ ተግባራት

- ✓ አርሶ አደሩ በጀመረው የለውጥ ጎዳና ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ የልማታዊነትን አስተሳሰብ ማሳደግ። ልማታዊ ያልሆኑ ኋላቀር ልምዶችንና አሰራሮችን እንዲዋጋ የሚያስችል ግንዛቤንና ዝግጁነትን መገንባት። አፍራሽ ኃይሎች አርሶ አደሩን

ከያዘው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ጎዳና ሊያስወጡት ብዙ ተጽዕኖዎችን ለመፍጠር እየሰሩ እንደሆነ ይታወቃል። በዓመታዊ እቅድና ኦረንቴሽን እንዲሁም በወቅታዊና በመደበኛ የግንኙነት መድረኮች አርሶ አደሩ ድሎቹን እንዳይቀማና ለላቀ የለውጥ ጉዞ እንዲተጋ ተከታታይ የአስተሳሰብ ስራ ይሰራል።

- ✓ በምርታማነት ኑሮ የማሻሻል አስተሳሰብን መገንባት፤ በ2009 የበጋና የክረምት ወቅቶች የግል ምርታማነትን የማሻሻልና በወል ልማት የጋራ ጥረት የተመዘገቡ ለውጦች ላይ መነሻ ሰነድ ቀርቦ ግምገማ ይካሄዳል። በግምገማው በትልቁ አቅዶ ሰፊ ምርትንና ከፍተኛ ምርታማነትን ለማግኘት የተካሄደው ጥረት፣ በሂደቱ የነበሩ ጥንካሬዎችና ድክመቶች በዝርዝር ተፈትሸው ትምህርት ይወሰዳል።
- ✓ ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ አሳድገው ውጤታማ የሆኑ ምርጥ ተሞክሮዎች ተቀምረው በየአካባቢው ይቀርባሉ። በ2010 ምርታማነትን ከማሳደግና ውጤታማ ከመሆን አኳያ የበላይ አካል እቅድና በአካባቢው የተቀመሩ ምርጥ ተሞክሮዎች ይቀርባሉ።
- ✓ የእቅዱ ማዕከላዊ ነጥብ፣ እያንዳንዱ አርሶ አደር በሰብል ልማት፣ በደንና በእንስሳት ሀብት ልማት በትልቁ አቅዶ ምርታማነቱን በከፍተኛ ደረጃ የሚያሻሽልበትና ከዚህ በመነሳት የራሱንና የቤተሰቡን ኑሮ የሚለውጥበት የገቢ ምርጥ ተሞክሮዎች የሚቀመሩበት ይሆናል። በመነሻ እቅዱና በምርጥ ተሞክሮዎቹ ላይ ተመስርቶ እያንዳንዱ አርሶ አደር ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ የሚችሉ ግቦችን አስቀምጦ ዝርዝር የግል እቅድ ይዘጋጃል።
- ✓ በርካታ የጉልበትና የእውቀት አቅም ያላቸው ወጣቶች በገጠር እንዳሉ ይታወቃል። እነዚህ ኃይሎች ተኩል ጉልበት ያላቸው እንደመሆናቸው ራሳቸውንም ጠቅመው ህብረተሰቡን በሚጠቅሙበት፣ ደረጃ የላቀ ምርታማነትን በሚያረጋግጥ በመስኖ ልማት፣ በተራራ ላይ ልማት፣ ከደን፣ ከእንስሳት እርባታና ማድለብ ተግባራት ጋር ተያይዞ በስፋትና በዘርፈ ብዙ መስኮች መሰማራት እንዲችሉ፣ የጠቅላላ አርሶ አደሩን ይሁንታና መተማመን መፍጠር፤ ወጣቶችም ጊዜያቸውን በአልባሌ ተግባር ላይ ከማዋል ተቆጥበው፣ ትኩስ ጉልበታቸውንና ፈጠራቸውን አስተባብረው የሚገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማስፋፋት ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት እንዲኖራቸው መተማመንን መገንባት
- ✓ በቀጣይነት የወጣቶች የስራ ፈጠራና ስምሪት የሚገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ማስፋፋት፣ በሂደቱም የላቀ አፈፃፀም ላላቸው እውቅና በመስጠት ለሌሎች አስተማሪ በሚሆኑበት ደረጃ ማዘጋጀት።

### ለ/ የአርሶ አደሩን አደረጃጀቶች ማጠናከርና አዳዲስ አደረጃጀቶችን ማበረታታት

አርሶ አደሩ የስራ አደረጃጀቶች አሉት። የልማት ቡድንና የአንድ ለአምስት አደረጃጀቶቹ የወል ልማት የሚያካሂድባቸውና ለግል ጥረቱ የተሞክሮ ልውውጥ የሚያካሂድባቸው ናቸው። እነዚህ አደረጃቶች የበለጠ ተጠናክረው ምርታማነትንና ውጤታማነትን በሚያሳድጉበት አግባብ ይመራሉ፤ አርሶ አደሩ መሰረታዊ ጥቅሞቹን ታግለው የሚያስከብሩለት ተጨማሪ አደረጃጀቶች ያስፈልጉታል። ህብረት ስራ ማህበር አደረጃጀቶች እንዲጠናከሩ ጥረት ይደረጋል። አደረጃጀቶቹ ከሀብት ብክነትና ሙስና ችግሮች ተላቅቀው የግብዓትና የግብይት ማዕከላት እንዲሆኑ መላ ህብረተሰቡና ለአደረጃጀቶቹ መሪዎች ጋር በጋራ እንሰራለን።

አርሶ አደሩ በአርሶ አደሮች ማህበር ተደራጅቶ መሰረታዊ ጥቅሞችን ለማስከበር እንዲንቀሳቀስ ማነሳሳት፣ በዚህ ዓመት ልንፈጽመው የሚገባ ፖለቲካዊ ስራ ነው። አደረጃጀቶችን የመፍጠርና የመገንባት ጉዳይ በአርሶ አደሩ ነፃ ፍላጎት የሚወሰን ቢሆንም፣ በአባላት ግንባር ቀደም አነሳሽነት ከቀበሌ እስከ ክልል ደረጃ የአርሶ አደሮች ማህበር ተመስርቶ ተጨማሪ የመወያያ

መድረክ ሊሆን ይገባል። ማህበሩ በምርት ግብይት፣ በግብዓትና አቅርቦት እንዲሁም በአርሶ አደሩ የፖለቲካ ተሳትፎ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ መታገያ መድረኮች ሆነው ማገልገል ይኖርባቸዋል።

**ሐ/ ለአርሶ አደሩ የሚቀርቡ ግብዓቶች**

በዋነኛነት በግብርና ቢሮና በሚመለከታቸው አካላት መቅረብ የሚገባቸው ግብዓቶች በወቅቱ ይቀርባሉ፤ በድርጅት ደረጃ የአርሶ አደሩን የአስተሳሰብ አድማስ የሚያሳድጉ ሰነዶች፣ መወያያ አጀንዳዎችና የአፈፃፀም ግምገማ ነጥቦች እንዲሁ በወቅቱ ይቀርባሉ።

**ግብ 10 የሴቶችና ወጣቶች እንዲሁም የሙያ ማህበራት ጋር በጋራ መስራት**

ከክልል ጽ/ቤት ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉትን የሴቶችና የወጣቶች ማህበራት ራሳቸው የውስጥ ነፃነታቸው ተጠብቆ ራሳቸውን በአስተሳሰብ ተጠናክረው ጥቅሞቻቸውን የሚያስጠብቁበት ሁኔታ ላይ መግባባት። አደረጃጀቶቹ ውስጥ የሚታዩ የውጤታማነት ችግሮች ባልተፈቱበት ሁኔታ ችግሮችን ውጫዊ አድርጎ መመልከት፣ በአደረጃጀቶቹ ላይ ውጤት እንዲያመጣና አመራሩ ተጠናክሮ የአባላቱን ሙብትና ጥቅም በራሱ በአባላቱ ጠንካራ ተሳትፎ እንዲረጋገጥ መተማመን መገንባት።

- የወጣት አደረጃጀቶች ቢኖሩም የጥንካሬ ደረጃቸው ወጣ ገባ መሆኑን ገምግሞ ማጠናከርና ማቀራረብ፤ የወጣት አመራሩና ኮር ግንባር ቀደሞች ተጠናክረው መላ ወጣቱን በመሰረታዊ የኢኮኖሚ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ላይ ንቅናቄ ማጠናከር፣ወጣቱ ውስጥ የሚታዩ በአጉል ሱሶች የመጠመድ፣ለአፍራሽ ቅስቀሳዎች ሰለባና መሳሪያ የመሆን አዝማሚያን በመቀየርና በማስተካከል መልካም ስነ-ምግባርና ምክንያታዊ የወጣት ሐይል ግንባታ ላይ ሚናቸውን እንዲወጡ መተማመን።
- ከመምህራንና ከጤና ባለሙያዎች ማህበራት ጋር የጋራ ጉዳዮቻችን በሆኑት የጥራትና የተደራሽነት ችግሮች ላይ በጋራ ለመንቀሳቀስ የሚያስችለንን ፎረም በማቋቋም በመደበኛነት እየተገናኘን ውይይቶችና የቀጣይ ስምሪት የትኩረት ጉዳዮች እየተለዩ ተግባራዊ ይሆናሉ።
- የህብረተሰቡን አደረጃጀቶች ማጠናከርና በህግ የበላይነትና የሰላም ማስከበር ተግባራት እንዲሁም በወንጀል መከላከልና በፍትህ ማስፈን ስራዎች ላይ ተሳትፎውን ማጎልበት።

**ግብ 11 የህብረት ሥራንና የሸማቾች ማህበራትን አደረጃጀቶች ማጠናከር**

- ከመሠረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራትና ከዩኒዬኖች ጋር የሚታዩ የአደረጃጀት ችግሮችን ለማስወገድ የተሰሩ ስራዎችንና የተገኙ ውጤቶችን ገምግሞ ትምህርት መውሰድና ማጠናከር፣ በየወቅቱ እየተገናኙ የማጠናከሪያ አሠራሮችን መቀየስና የሚታዩ ክፍተቶችን ተከታትሎ ማረም ።
- ከ2009 በጀት ዓመት አፈጻጸም ጋር በማያያዝ ግምገማ ማካሄድ። ከግምገማው ተነስቶ በየደረጃው ችግሮችን የማስተካከልና ማህበራቱ የአባሎቻቸውን የገበያና የግብዓት ሁኔታ በሚያጠናክሩበትና እንቅፋቶች በሚወገዱበት ሁኔታ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ማጎልበት።

## ግብ 12 ከህዝብ ግንኙነትና መገናኛ ብዙኃን ተቋማት ጋር መስራት

የሚዲያ ኮሚቴ ጀምር እንቅስቃሴን አጠናክሮ መቀጠል፤ በህዝብ ግንኙነትና ሚዲያ ፎረም፣ የአማራ መገናኛ ብዙኃንን ጨምሮ ከአገር ውስጥ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ጋር እንዲሁም የብአዴን ልሳናትና ማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎቶች ጋር፤ በህዝብ የልማትና የመልካም አስተዳደር እንዲሁም የዴሞክራሲ ግንባታ አጀንዳዎች ወቅታቸውንና ጥራታቸውን ጠብቀው በሚተላለፍበትና የህዝቡም ተሳትፎ በሚጠናከርበት ሁኔታ ላይ በጋራ ይሰራል። ተቋማቱ በአስተሳሰብ ግንባታ፣ በዕውቀትና ክህሎት ማስፋፋት፣ በአደረጃጀት ማጠናከር፣ በተሻሻለ አሰራርና ቴክኖሎጂ ልማት፣ እንዲሁም በየመስኮቹ ጠቃሚ በሚባሉ ምርታማነትን የሚያሻሽሉ፣ የስራ እድል ፈጠራን የሚያበረታቱ፣ የጥራትና የተደራሽነት እንዲሁም የልምድ ልውውጥ ማካሄድ። ችግሮችን የሚያቃልሉ የአስተሳሰብ ግንባታዎችን ማካሄድ በትኩረት የምንቀሳቀስባቸው ይሆናሉ።

## ግብ 13 ከተቃዋሚ ኃይሎች አኳያ የሚሰሩ ስራዎች

ተቃዋሚ ኃይሎች በሁለት ተከፍለው እንደሚታዩ በሁኔታ ትንተናው ላይ ተጠቅሷል።

### 1, ህጋዊና ሰላማዊ ሁኔታን ለመረጡ ኃይሎች የሚሰሩ ስራዎች

ሰላማዊና ህጋዊ ሁኔታ የመረጡ ኃይሎች ምርጫቸው ህገ-መንግስታዊ ስለሆነ በስርዓቱ መሰረት ሀሳባቸውን ለህዝቡ በሚያቀርቡት ሁኔታ የተመቾ ሊሆን ይገባል። ህገ-መንግስቱና ስርዓቱ ህዝቡ ግራና ቀኝ አማራጮች ቀርበውለት የተሻለውን እንዲመርጥ እድል የሚሰጥ ነው። በዚህ አይነት የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ የብአዴን አመራርና አባላት አማራጭ አስተሳሰቦቻችንና ተግባራዊ ጥረቶቻችን ለህዝቡ በማቅረብ ህዝቡ ግራና ቀኙን አገናዝቦ የራሱን አማራጭ እንዲወስን የሚያስችል ስራ መስራት ይኖርብናል። ከህጋዊና ሰላማዊ ተቃዋሚዎች ጋር በ2010 ዓ.ም የወረዳና የቀበሌ ምርጫና በሌሎችም የሰላምና ልማት ጉዳዮች ላይ የጋራ ኮሚቴ አዋቅረን በየወቅቱ እየተገናኘን ህጋዊና ሰላማዊ ሁኔታን ማበረታትና ለተጀመረው የለውጥ ጉዞ ማጠናከርን ማዕከል ያደረገ ይሆናል።

### 2, የጥፋት ኃይሎችን አፍራሽ ቅስቀሳ ተከታትሎ ማጋለጥና ከህዝብ መነጠል

- የጥፋት ኃይሎቹ የሚጠቀሙት የልማታዊ ዴሞክራሲ ኃይሎችን ድክመት በመሆኑ ድክመትን መቀነስ፣ ማረምና ማስተካከል፣የጥፋት ኃይሎቹ ችግሮችን አጋነው፣ አዛብተው የፈጠራ ወሬና አሉባልታ ጨምረው የሚሰሩ እንደመሆናቸው ተከታትሎ በገፅ ለገጽ ውይይት፣ በከባቢያዊና ክልላዊ የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች፣ በማህበራዊ ሚዲያ ዘርፎች አማካኝነት ለህዝብ ማጋለጥና ህዝቡ ሁኔታውን እያየ የራሱን ትክክለኛ አቋም እንዲወስድ የሚያስችል ስራ መስራት፣
- ፀረ-ሰላምና የህግ የበላይነትን በመጣስ የሚሰሩትን ስራ ተከታትሎ ማጋለጥና ወንጀለኞችን ለህግ ማቅረብ፣ በግርግርና በኀዳና ላይ ነውጥ እንዲሁም በሽብር እንቅስቃሴ ህገ-መንግስትና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን ማፍረስ እንደማይችሉ የሚያረጋግጥ ስራ መስራት፣ ሰላም የማስከበርና የህግ የበላይነት አስተሳሰብ ህብረተሰቡ ውስጥ መገንባት በትኩረት ይሰራል።

## 4. የ2010 ዓ.ም የፖለቲካና ድርጅት ስራ ተግባራትና የምዕራፎች ክፍፍል

### 4.1. የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት

- በ2009 ዓ.ም የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ድርጅት ስራ ግምገማዎችና ድምዳሜዎች፣ በ2010 የእቅድ መነሻ ሁኔታዎችና በቀጣይ የትኩረት ጉዳዮች ላይ ተመስርቶ ግምገማዎችንና በእቅዱ ላይ የመተማመን ስራ ይካሄዳል።
- የሚካሄዱ ግምገማዎች፣ የእቅድ መነሻ ሀሳቦችና የ2009 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ተመስርቶ የአመራርና የአባላት የአካል ግምገማ፣ ግለሂስና ሂስ ማካሄድ መነሳሳት ዝግጁነትና ጥልቅ እምነት የተግባር ቁርጠኝነት ይፈጠራል።
- ሞዴል የአፈፃፀም ተሞክሮዎች ላይ ተመስርቶና ምርጥ አፈፃፀም መሰረት የእቅድ ዝግጅትና እቅዱን አንብቦ ማዳበር ግብረ-መልስ መስጠት እንደ ዝግጅት ምዕራፍ ተግባር የሚታይ ይሆናል።
- ከዕውቀትና ክህሎት ጋር የተያያዙ ስልጠናዎችን በየደረጃው እስከ ህብረተሰቡ ድረስ ማደራጀት።
- የአስተባባሪ፣የኮማንድ ፖስት፣የፖለቲካና የተቋም ሥራ አመራር ኮሚቴዎችን አደረጃጀት ማጠናከር፣ የጐደሉትን ማሟላት፣ የመሠረታዊ ድርጅት፣ የህዋሣት፣ የልማት ቡድኖችንና 1ለ5 አደረጃጀቶችን ማጠናከር። ወደ ተግባር የሚያስገባ የዝግጁነትና የተነሳሽነት እንዲሁም የቁርጠኝነት ሁኔታ ማረጋገጥ።

### 4.2. በተግባር ምዕራፍ የሚከናወኑ ሥራዎች

- በተደራጀ የለውጥ ኃይልና ንቅናቄ አማካኝነት የክልላችንን አስተማማኝ ሰላምና የህግ የበላይነት በቀጣይነት ማረጋገጥ፣የልማት ሠራዊቶች በገጠር በመስኖና በእንስሣት ሀብት ልማት፣ በከተሞች በሁሉም መስኮች መጀመራቸውን ማረጋገጥ።
- የድርጅት አመራርና አባላት ኮር የለውጥ ኃይልና የሠራዊት መሪ መሆናቸውን በየደረጃውና በተቋማት ማረጋገጥ።
- በተቋማትና በየደረጃው በአመራሩና በአባላት ዘንድ የሚስተዋሉ የውጤታማነት ችግሮች፣ የራስን ተልዕኮ ሳይወጡ አሻግሮ መመልከትና ማማረር የመሳሰሉ የራስ ድክመት መሸፈኛ ችግሮች በተግባር መወገዳቸውን እያረጋገጡ መሄድ። የኪራይ ሰብሳቢነት፣ ህገ ወጥ ተጠቃሚነት፣ የህዝብ አንገብጋቢ ችግሮችን በህዝብ ተሳትፎ ያለመፍታት፣ የፀረ-ዴሞክራሲና የአድርባይነት ችግሮችን በፅናት እየታገሉ በቀጣይነት ማስተካከል። ከብሔርና ከኃይማኖት ማንነት ጋር የተያያዘ የትምክህት፣ የጠባብነትና የኃይማኖት አክራሪነት ችግሮች እየተቃለሉ መሆኑን ማረጋገጥ፤የዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነትና ዴሞክራሲያዊ አንድነት አስተሳሰብ ለውጥ መምጣቱን ማረጋገጥ።
- የአስተሣሠብ፣ የክህሎት፣ የአሰራርና የአደረጃጀት እንዲሁም የአቅርቦት ችግሮችን መለየትና በወቅቱ ጠንካራ የአስተሳሰብ ትግል ማቀጣጠል፤ የአቅርቦት ጉዳዮችን በእቅዱ መሰረት ማሟላት።
- በተግባር አፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ ሂደት ምርጥ ተሞክሮን በታቀደ መልኩ መቀመር፣ ማስፋፋት፣ በሁሉም አካባቢዎች ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ። ሠራዊቱ በሁሉም ግንባሮች፣ ከአንደኛው ምዕራፍ ወደ ሁለተኛው ተግባር ንዑስ ምዕራፍ ያለውን ሽግግር በመገምገም አቅም እየፈጠረ መሆኑን የሚያረጋግጡ ተግባራትን ማከናወን።

- በአፈፃፀም ሂደት ግንባር ቀደምና ታታሪ የሆኑ ወጣቶች፣ ሴቶችና ምሁራን ላይ በማተኮር መመልመልና ወደ ድርጅታችን የድርጅት አሰራሩንና መርህን ተከትሎ መቀላቀል፤ በቀጣይነት ግንባታ ማካሄድ፤ ተግባራት በቅደም ተከተል፣ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ፣ በተቀናጀ መልኩ ስለመፈፀማቸው ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ ማካሄድ። በዚህ የአፈፃፀም ሂደት ምርጥ ፈፃሚዎችን የለየና እውቅና የሚሰጥ፣ ደካማ አፈፃፀም ያሳዩትን ከችግር የሚያወጣና ክፍተት የሚሞላ ተሞክሮ ማስፋፋት።

### 4.3 የማጠቃለያ ምዕራፍ ተግባራት

- በዓመታዊ እቅድ ግቦችና ተግባራት በተለዩት የአቅም ግንባታ መስኮች የአፈፃፀም ግምገማ መካሄድና ተሞክሮዎችን መቅሰም። ኮር የድርጅት አመራርና አባላት መገንባቱን ማረጋገጥ። ውጤታማነት በተግባር ለውጥ ማምጣት የመሳሰሉት የትኩረት ጉዳዮች ምን ያክል ተሳክተዋል? የሚለውን ወስዶ ማረጋገጥ።
- በዓመቱ መጨረሻ ደግሞ የተከናወኑ ተግባራት ተገምግመው የላቀ አፈፃፀም ያላቸውን የመሸለምና የማሣደግ፣ በአንፃሩ የደከመ አፈፃፀም ያሣዩትን የማብቃትና እንደአስፈላጊነቱ የማሸጋሸግ ሥራ ይሠራል።

## 5. መሰረታዊ አቅጣጫዎች

### 5.1 የ2010 ዓ.ም የፖለቲካና ድርጅት ስራ እቅድ መሰረታዊ የአፈፃፀም አቅጣጫዎች

### 1, ተግባርንና ውጤታማነትን ማዕከል ያደረገ የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ግንባታ ይሆናል።

የተግባር ውጤታማነትን ማዕከል ባደረገው የአስተሳሰብና የአደረጃጀት ግንባታ የቅድሚያ ትኩረቱ ኮር የአመራርና ኮር የአባላት ውጤታማነትን ማረጋገጥ ላይ ያነጣጠረ ይሆናል። የኮር ኃይሉ ውጤታማነት በተረጋገጠበት ሁኔታ በኮር ኃይል አማካኝነት መላ አባላትን፣ መላ የመንግስትና የህዝብ አደረጃጀትና ጠቅላላ ህዝቡን ማነቃነቅና በልማት ሰራዊቱ አማካኝነት የህዝቡን አንገብጋቢ የምርታማነት፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮች መፍታት ይሆናል። ትልቅና ፈጣን ውጤት የማምጣት መሰረታዊ አካሄድ ይጠበቃል።

### 5.2 ምርጥ ተሞክሮዎችንና ሞዴል ፈፃሚዎችን ቀምሮ ማስፋፋት

በተግባር ውጤታማነት እንዴት ሊረጋገጥ ይችላል? የሚለው ጥያቄም ከላይ በየህብረተሰብ ክፍሉ በተዘረዘሩ የአቅም ግንባታ መስኮች አፈፃፀሙ ሊሳካ እንደሚችል የተጠቀሰ ቢሆንም አንኳር ጉዳዮችን ለማመላከት ዋነኛ የአፈፃፀም አግባቦቹ ምርጥ ተሞክሮዎችና ሞዴል ፈፃሚዎችን በአግባቡ ቀምሮ በማስፋፋትና በጥብቅ ዲስፕሊንና በውጤታማነት በማከናወን ሊሳካ የሚችል ነው። ዋናው የማስፈፀሚያ ስልት ምርጥ ተሞክሮ ማስፋፋትና በሞዴሎች አማካኝነት ወደ ሌሎች የማስፋፋት ጉዳይ ባለፉት ዓመታት ያልተሞከረና ያልተነገረ ጉዳይ ስለሆነ አይደለም። ባለፉት ዓመታት አንድም በሙሉ ተግባራዊ አልሆኑም ወይም ደግሞ ሙሉ በሙሉ ቢተገበሩም ምርጥ ተሞክሮ ማስፋፋት በሞዴሎች አማካኝነት ወደ ሌሎች ማስፋፋትና የአንድ ወቅት ጉዳይ ሳይሆን በቀጣይ የሚተገበርና አለም እየተገበረው ያለ አዋጭ መንገድ በመሆኑ ነው።

### 5.3 ህዝባዊ ተቀባይነትን የማረጋገጥ አቅጣጫ

የብአዴን-ኢህአዴግ ህዝባዊ ተቀባይነት ሊረጋገጥ የሚችለው ምርጥ ፖሊሲዎች ሲያዝ ብቻ አይደለም። ምርጥ ፖሊሲዎች ተተግብረው በተግባር ለውጥ ሲረጋገጥ ነው። ካልሆነ የወረቀት ላይ ጌጦች ብቻ ሆነው ይቀራሉ። ህዝቡ ሊደግፈን

የሚችለው በተግባር ለውጥ መጥቶ ሲመለከትና በለውጡ ሲመሰጥና ሲነሸጥ ብቻ ነው። ይህን ማዕከል ያደረገ ተግባራዊ ለወጥ ጀምሮ አለመተው እንዲሁም በቆራጥነትና በጥልቅ ህዝባዊ እምነት ብሎም ጽናት የታቀደውን መፈፀምና ውጤታማ መሆን ማዕከላዊ የማስፈፀሚያ ትኩረታችን ይሆናል።

5.4 በተግባር ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ክትትልና ድጋፍ ማካሄድ በትኩረት የሚሰራበት ይሆናል። የክትልና ድጋፍ ስርዓቱ የታቀደውን በጥራትና በውጤታማነት ለመፈፀም እንዲሁም ከአፈፃፀሙ ምርጥ ተሞክሮ ለመቀመርና መልሶ ለማስፋፋት ታሳቢ ያደረገ ይሆናል።

### 5.5 የሚዲያና ህዝብ ግንኙነት ተግባቦት ስራን አጠናክሮ መቀጠል

የሚዲያና ህዝብ ግንኙነት ስራችን በእቅድ መነሻ ሀሳቦች ውይይት ወቅትም ሆነ በጠቅላላ የዝግጅት ምዕራፍና በዋነኛነት ደግሞ በተግባር ምዕራፍ ወቅት ቁልፍ የተግባቦትና የተሞክሮ ማስፋፋት መንገድ ሆኖ እንዲያገለግል በጥብቅ ይሰራበታል። ለዚህም መደበኛ የመገናኛ ብዙሃንና የህዝቡ ግንኙነት አውታሮች፣ የገጽ ለገጽ የውይይት መድረኮች እንዲሁም ማህበራዊ ሚዲያ አውታሮች እንደየ አግባባቸው ስራ ላይ ይውላሉ። በውስጠ ድርጅትና በህብረተሰቡ ውስጥ የሚሰራው የህዝብ ግንኙነት ስራ በይዘት ተመሳሳይ ሊሆን ቢችልም በአቀራረብ ግን መለየት ይኖርበታል። በውስጠ ድርጅት የተገመገመውንና መታረም ያለበትን ያለቅጥ እያወጡ መዘርገፍና መልሶ ለጠላት ዱላ የማቀበል የህዝብ ግንኙነት አግባብ ፍፁም መስተካከልና መታረም ይኖርበታል።

## 6. በ2010 እቅድ አፈፃፀም የሚያጋጥሙ ችግሮችና መፍትሄዎች

### 6.1 የሚያጋጥሙ ችግሮች

1. በቂ ዝግጅት ሳያደርጉ ወደ ስራ መግባት ችግር ፈች እቅድና በቂ ተግባቦትና መተማመን ሳይፈጥሩ ወደ ስራ መግባት ተግባርና ውጤታማነትን ማዕከል ያደረገ እንቅስቃሴ ተግባር ከተጨባጭ ችግር ላይ የተመሰረተ እቅድና አስተማማኝ የመፍትሄ ቀመር የያዘ መሆን አለበት። እቅዱ ችግር ፈች እንዲሆን በተጨባጭ ተሞክረው ውጤት ያመጡ ምርጥ ተሞክሮዎችንና ሞዴሎችን አነፍንፎ መቀመርና፣ በዚህ ላይ የተመሰረተ እቅድና በእቅድ ላይ ተግባቦት እና መተማመን መረጋገጥ ይኖርበታል። በዚህ ረገድ እንደነገሩ ማቀድ፣ እንደነገሩ ተግባቦት ማካሄድና በቂ መተማመን ሳይያዝ ወደ ስራ መግባት የሚያጋጥም ችግር መሆኑ አይቀርም።
2. ተግባርንና ውጤታማነት ማዕከል ያደረገ ወጥ መስፈርት አለመኖርና ቢኖርም እንኳ በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ አለመፈለግ።

   ጀምሮ በመተው፣ በዚህ ላይ የተገነባ አመራር ያለማብቃት ሁኔታ ባለበት፤ በተግባር ውጤታማነት እንዴት ይለካል? መስፈርቶች አሉን? በመስፈርቶቹ እንድንመዘን እንፈልጋለን? እነዚህ ጥያቄዎች በአግባቡ ባልተዘጋጁበት ሁኔታ በተግባር ውጤታማነት ማረጋገጥ የሚለው እቅድ መፎክር ሆኖ የመቅረት እድል አለው። ችግሩን ለመቋቋም ከተንዛዛ የወረቀት ስራ በመወጣት የተመረጡ የውጤታማነት አመልካቾች አዘጋጅተን በነዚህ መስፈርቶች እንድንመዘን ተስማምተን ወደ ተግባር መግባት ይጠይቃል። አፈፃፀሙን በተመለከተ በቀጣይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ እያዳበሩ

መሄድ ይጠይቃል። በተግባር ውጤታማነትን ማዕከል ያደረገ ኮር የአመራርና የአባላት መዋቅር ለመገንባት እምነትና ቁርጠኝነት ያለማሳደር ሁኔታ ያጋጥማል።

3. **እቅዱን በተደራጀ የለውጥ ሰራዊት አለመፈፀም።**

   የግብር ይውጣ በሆነ አግባብ የልማት ኃይሎችን የመምራት ሁኔታ ያጋጥማል። በተግባር ውጤታማነት ሊረጋገጥ የሚችልበት ዋናው መንገድ የተደራጁ የልማት ሰራዊት እንደሆነ ግልጽ ነው። እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ተግባሩን በለውጥ ሰራዊት አግባብ አለመፈፀም። ለልማት ሰራዊት የሚያበቃ በቂ ስራ ሳይሰሩ ላይ በላይ ሰራዊት ተገንብቷል በማለት ሳያሳምኑ መንቀሳቀስ ሁኔታ ይኖራል። ይህ ደግሞ ውጤት አያመጣም።

4. በአፈፃፀም ሂደት ውጤታማ የሆኑትን በአግባቡ አለመለየት። ከለዩም በኋላ ለሚገባው የአመራር ደረጃ ያለማብቃት ችግሮች ያጋጥማሉ።

## 6.2 ለችግሩ የቀረቡ መነሻ መፍትሄዎች

### 1. ለውጤት የሚያበቃ በቂ ዝግጅት ማካሄድ

እቅድ ዝግጅት፣ ፈፃሚ ማዘጋጀትና በቂ መተማመን መፍጠር ከዛም ወደ ስራ መግባት በተግባር ውጤታማ መሆን አለብን ብለን ከተነሳን ለውጤት የሚያበቃን እቅድ በየደረጃውና በየተቋማት መኖሩ መረጋገጥ ይኖርበታል። ለውጤት የሚያበቃ እቅድ በተጨባጭ ተሞክሮ ስኬታማ ከሆኑት ሞዴሎች ሊገኝ የሚችል ነው። የሞዴሎችን ተሞክሮ በአግባቡ በመቀመር የእቅድ መነሻ (ቤንች ማርክ) ማድረግ ይጠይቃል። በዚህ አግባብ የግልና የወል እቅድ ተዘጋጅቶ ስምምነት ከተደረሰበት በኋላ በእቅድ አፈፃፀም ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቂ መተማመን መረጋገጥ ይኖርበታል። መተማመን ሲባል ፈፃሚ ኃይሎቹ እቅድ ውጤታማ እንደሚያደርጋቸው እምነትና ከእምነት የሚቀዳው ቁርጠኝነት መረጋገጥ አለበት። ይህ ጉዳይ በእቅድ ኦረንቴሽን ወቅት ብቻ የሚፈፀም ባይሆንም መነሻ አቅም ይዞ ወደ ተግባር መግባት ይኖርበታል።

### 2, የውጤታማነት መለኪያዎች ማዘጋጀትና በነዚህ መስፈርቶች

ለመመዘን እምነትና ቁርጠኝነት ማሳደር ይኖርብናል። በተሰማራንበት መስክ ሁሉ ውጤታማ የሚያደርጉን አውራ መስፈርቶች ይዘጋጃሉ። እነዚህ መስፈርቶች በእርግጥም ሊለኩን እንደሚችሉ ተግባብቶ መነሳት ወሳኝ ነው። በመስፈርቶቹ ከተማመን በኋላ በቁርጠኝነት ልንመዘንባቸው ይገባል። ጀምሮና አቅዶ መተው ውድቀትና ውርደት መሆኑን አይቶና ተፀይፎ የውጤታማነትና የስኬትን መንገድ በመምረጥ መነቃነቅ ይገባል። በዚህ መስፈርት አልፈው ውጤት ያስመዘገቡና ለላቀ አመራርና ለላቀ ተልዕኮ በሚዘጋጁበት ሁኔታ መከታተልና መደገፍ በትኩረት ሊሰራበት ይገባል።

### 3, በለውጥ ሰራዊት አማካኝነት መፈፀም፤

ውጤታማ የሆኑ ኮር አመራሮችና ኮር አባላት መፍጠር፣ መነሻ አቅም ይሆን ካልሆነ በስተቀር ሁሉን አቀፍ ህብረተሰባዊ ለውጥ ሊመጣ አይችልም። ሁሉንም አቀፍ ህብረተሰባዊ ለውጥ ሊመጣ የሚችለው ሁሉም የልማት ኃይሎች ተደራጅተው ለላቀ ውጤት ሲሰማሩና ውጤታማ ሲሆኑ ነው። በመሆኑም እንቅስቃሴያችን ጥቂት ምርጦችን ከማነቃነቅና ውጤታማ ከማድረግ በላይ አልፎ የልማት ኃይሎቹ በግል የምርታማነትና የኑሮ መሻሻል ላይ እንዲሁም በወል ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ተግባራት ላይ ውጤታማ መሆን የሚያስችሉ ንቅናቄዎች መካሄድ ይኖርባቸዋል።

### 4, ቀጣይ ኮር አመራር እየገነባን እንሂድ

የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን ቀጣይነት ሊረጋገጥ የሚችለው ምርጥ ፖሊሲዎችና ምርጥ አፈፃፀም በማሳየት ብቻ አይደሉም። የስርዓቱ ቀጣይነት ሊረጋገጥ የሚችለው ምርጥ ፖሊሲዎችና ምርጥ አፈፃፀሞችን ሊያስቀጥል የሚችል ኮር

አመራር በየደረጃውና በየተቋማት መገንባት ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም በየስራ መስኮች ሁሉ ውጤታማ የሆኑ ግንባር ቀደሞችን መለየት፣ መመልመል፣ ማነጽና ማብቃት በእምነት ይዘን ልንረባረብ የሚገባ ይሆናል፡፡

## 7. የእቅዱ ፈፃሚ አካላት

- ✓ የብአዴን ስራ አስፈፃሚና ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት፣
- ✓ በየደረጃው የአስተባባሪ፣ የተቋም ስራ አመራር፣
- ✓ የፖለቲካና ጠቅላላ ስራ አመራር ኮሚቴ በየደረጃው የሚገኝ የብአዴን ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ፣
- ✓ የገጠርና የከተማ ፖለቲካና ድርጅት ዘርፎች
- ✓ የውጣቶችና ሴቶች ሊጎች፣
- ✓ የመሰረታዊ ድርጅትና ህዋሳት አደረጃጀቶችና አባላት፣
- ✓ የልማት ቡድን የአንድ ለአምስት አደረጃጀቶችና አባላት፣

## 8. ተግባራት የሚፈፀሙበት ጊዜ ሰሌዳ

- ✓ እቅድ ዝግጅት እስከ ነሀሴ 30/2009 ዓ.ም
- ✓ በመነሻ እቅዱ ላይ የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ውይይት ከመስከረም 4-8/2010 እቅዱ ቀድሞ ይላካል፡፡
- ✓ መስከረም አጋማሽ ላይ የዞንና የወረዳ ኮር አመራሩ በሚሳተፍበት ሁኔታ በክልል ደረጃ ይካሄዳል፡፡
- ✓ የዝግጅት ምዕራፍ እስከ ጥቅምት መጨረሻ ይጠናቀቃል፡፡
- ✓ የተግባር ምዕራፍ ከህዳር 2010 ጀምሮ ይሆናል፡፡

***መሪ ሀሳብ***

***ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ተግባርንና ውጤታማነትን ማዕከል ያደረገ ድርጅት እንገነባለን!!***

***ሌሎች መልዕክቶች***

- ✓ የሙስናና የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባርን በመታገል ልማታዊነት ይሰፍናል!
- ✓ ብአዴን- የዴሞክራቲዎችና የተራማጅ ማዕከል ይሆናል!
- ✓ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አድርባይነትን እንዋጋለን!
- ✓ ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነትንና ዴሞክራሲ አንድነትን እንገነባለን!
- ✓ የብአዴን አባላት አስተሳሰብበተግባር ምሳሌና የለውጥ ሀይል ይሆናሉ!
- ✓ የአሙቱን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በመፈጸም የህዝባችንን ተጠቃሚነትና ህዳሴያችንን እናፈጥናለን!